አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል

አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል



ክፍለ ሀገሬ ካሣሁን ገሠሠ

8ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

የጥንቃቄ መልዕክት

ተማሪዎች!

ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ሥዕሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

<u>ማሳሰቢያ</u>፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

8ኛ ክፍል

አዘጋጆች

እናትነሽ በዛብህ ምህረቱ

አምባው ደምሴ ቀኜ

አርታኢዎች

ትንሳኤ ብርሃኔ ላቀው

ተሻገር አስማረ ደምሴ

ሰዓሊ

ከበደ አለሙ

ዲዛይነር

ገነት አባተ መኮንን

የቡድን መሪ

ዶር. ማረው አለሙ ተሰማ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

የምሁራን መማክርት ጉባዔ

ማውጫ

ጠቃሚ ምክር ለተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ iv

ምዕራፍ 1 የሥራ ሥነምግባር 1

ምዕራፍ 2 ባህላዊ ቅርሶች 15

ምዕራፍ 3 ሰብዓዊ እሴቶች 32

ምዕራፍ 4 አጭር ልቦለድ 47

ምዕራፍ 5 ሥነሕዝብ 61

ምዕራፍ 6 በረሃማነት 77

ምዕራፍ 7 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ 92

ምዕራፍ 8 ሰላም 109

ምዕራፍ 9 የአየር ንብረት 124

ምዕራፍ 10 ድራማ 142

ዋቢ ምች 164

ጠቃሚ ምክር ለተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ

ይህ የተማሪ መጽሐፍ በፍኖተካርታውና በሀገርአቀፍ ምዘናዎች ምክረሐሳቦች መሠረት በ2013 ዓ.ም በተደረገው የሥርዐተትምህርት ለውጥ መነሻነት የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም በመጽሐፉ ዝግጅት የሚከተሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፤

1. የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ፣ የመተንተን፣ የማጠቃለል፣ የመጠየቅ፣ ችግር የመፍታት፣ የመወሰን፣ የመግባባትና የመገምገም ክህሎት የሚያሳድጉ ዓይነተብዙ ተግባራት ተካትተዋል፤

2. የተማሪዎችን አቀላጥፎ የማንበብ፣ የማዳመጥ፣ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ የሚያጎለብቱ ታሪኮችና ተዛማጅ ተግባራት እንዲኖሩ ተደርጓል፤

3. የትምህርቱ አቀራረብ ከይዘትተኮር ይልቅ ወደተግባርተኮር እንዲያመዝን ሆኗል፤

4. ሀገርበቀል እውቀቶች እንደአስፈላጊነታቸው በታሪኮች፣ በምንባቦችና በተዛማጅ ተግባራት ውስጥ ተካትተዋል፤

5. የባሕላዊ ማንነትንና የአርበኝነትን ፋይዳዎች የሚያስገነዝቡ ታሪኮች፣ ምንባቦች፣ ሥነግጥሞችና ሥዕሎች እንደአስፈላጊነታቸው ተካትተዋል፤

6. ተማሪዎች በአብዛኛው በትብብር የሚማሩባቸው እድሎች ተመቻችተዋል፤

7. ለመማር የመማር ክህሎትን ለማጎልበት ሲባል፣ ተማሪዎች በየምዕራፎቹ አራቱን ክሂሎችና ሰዋስዋዊ ይዘቶች የሚማሩባቸው ዓይነተብዙ ብልሀቶች ተካትተዋል፤

8. የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት ሲባል ቋንቋውን ፈጥረው የሚጠቀሙባቸው በርካታ እድሎች ተመቻችተዋል፤

9. ሥርዐተፆታንና አካቶ ትምህርትን ከግምት ለማስገባት በታሪኮች፣ በምንባቦች፣ በሥዕሎችና በተዛማጅ ተግባራት እንዲሁም በቋንቋው ትምህርት የይዘት አቀራረቦች ላይ ጥንቃቄ ተደርጓል።

የተማሪ መጽሐፉ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በጥልቀት ማሰብን፣ ማንበብን፣ መጻፍን፣ ማዳመጥንና መናገርን እንዲማሩበት የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ዝግጅት፣ ተማሪዎች እንዴት ማሰብ፣ ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር እንዴት ፈጠራዊና አስደሳች እንደሚሆን፣ የትምህርትቤትና የቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ የምርምር ግኝቶች ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ተማሪዎችና የተማሪ ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ይበልጥ ለማዳበር በቤት ውስጥ በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የትምህርት ይዘቶቹ በአስር ምዕራፎች የተደራጁ ናቸው፤ የመጀመሪያዎቹ ዐምስት ምዕራፎች የትምህርት ይዘቶች በመጀመሪያው መንፈቀዓመት፣ ቀሪዎቹ ዐምስት ምዕራፎች ደግሞ በኹለተኛው መንፈቀዓመት እንዲጠናቀቁ ሆነው የቀረቡ ናቸው። የአንድ ምዕራፍ የትምህርት ይዘቶች ደግሞ በሦስት ሳምንታት እንዲጠናቀቁ ታስበው ነው የተደራጁት። የየምዕራፎቹ የትምህርት ይዘቶች በአንድ ነጥብ በተለዩ ሦስት ቁጥሮች የተወከሉ ናቸው፤ የመጀመሪያው ቁጥር ምዕራፍን፣ ኹለተኛው ቁጥር ሳምንትንና ሦስተኛው ቁጥር ቀንን የሚወክሉ ናቸው። ለምሳሌ፣ 1.1.1 የሚሉ ቁጥሮች ምዕራፍ አንድን፣ ሳምንት አንድንና ቀን አንድን በቅደምተከተል ይወክላሉ፤ እንዲሁም 10.2.3 የሚሉ ቁጥሮች ምዕራፍ አስርን፣ ሳምንት ኹለትንና ቀን ሦስትን በቅደምተከተል ይወክላሉ።

የመጽሐፉ መሠረታዊ መርሖች የሚከተሉት ናቸው፤

- ተማሪዎች ለማኅበረሰብ አስፈላጊ ስለሆኑ ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ፤ እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ ዋና የምንባብ ጭብጥንና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል፤
- ተማሪዎች ስለእያንዳንዱ ምንባብ ጭብጥና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡና ካነበቡ በኋላ፣ ባዳመጡትና ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመስርተው ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም፤
- የእያንዳንዱ ምዕራፍ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምዕራፉ ጭብጥና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች መሠረት ከተጻፉ ምንባቦች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፤
- ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በቋንቋው በትክክል ለመግለጽ እንዳይቸገሩ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ጋር በትብብር ይማራሉ፤

- ተማሪዎች በምዕራፎቹ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች ላይ ተመስርተው የቀረቡ ምንባቦችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች የበለጠ ለማጠናከር በቤታቸው ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጅ/አሳዳጊ ከነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆችዎ ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል፤

1. ወላጅ/አሳዳጊ የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆችዎን በመጠየቅ ይርዱ፤

2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤

3. ልጆችዎን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ስለምንባቡ ያወያዩ፤

    - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
    - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
    - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
    - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
    - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን

4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሚችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤

   - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
   - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
   - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?

5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ፤

6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ ያበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ይወያዩ፤

7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ፤

8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ፤

   - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
   - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
   - ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
   - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?

9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆችዎን ይጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋል? በዓረፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል? ወዘተ.

10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።

11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

የመጽሐፉ ይዘቶች አደረጃጀት

ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት ይዘቶች በአስር ምዕራፎች የተደራጁ ናቸው። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች የሚደመጡና የሚነበቡ ምንባቦች አሉት። የምንባብ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋው አቀላጥፈው ለመናገር፣ ለማዳመጥ፣ ለማንበብና ለመጻፍ እንዲረዷቸው ሆነው የተሰናዱ ናቸው።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር እንድትወያዩ ይጠበቃል።

ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ምንባብ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቁልፍ ቃላትን መማርና ስለነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- በማዳመጥ ምንባቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር በክፍል ውስጥ መወያየት፣

- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሐሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ምንባቦችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት አቀላጥፈው ያነባሉ።

አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። በተጨማሪም ባነበቡት ምንባብ ላይ ተመሥርተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። ተግባራቱም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንበብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- በምንባቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ጭብጦች ወይም በንኡሳን ርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን በትወና እንዲያቀርቡ ማድረግ።

ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፦

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።

መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነባባሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሀሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱና ለኅትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተለያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

ምዕራፍ 1 የሥራ ሥነምግባር

1.1.1 አንብቦ መረዳት

መታመን ለራስ ነው!

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ርዕሱን አስተውላችሁ የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ለ. ስለምታውቋቸው በሙያ የተመሰገኑ ሰዎች በአጭሩ ተነጋገሩ።

ሐ. የሙያ ትልቅና ትንሽ ያለው ይመስላችኋል?

መታመን ለራስ ነው!



አስረበብ በደቡብ ወሎ ዞን የሳይንት ወረዳ ነዋሪ ነች። ያለፍላጎቷ በልጅነቷ ስለተዳረች ደስተኛ አይደለችም። ከባለቤቷ ጋር በእድሜ አቻ አይደሉም፤ ፍቅርም አልነበራቸውም፤ በመሆኑም አንድ ቀን ከጎረቤቶቿ ጋር ገበያ እንደወጣች ሳትመለስ ቀረች። በጀርባዋ ተሸክማ ገበያ የወሰደችውን እህል ሸጣ ያገኘችውን ገንዘብ ቋጥራ ከነጋዴዎች ጋር ወደደሴ ኮበለለች።

ደሴን የምታውቃት በስም ነው። ደሴ ውስጥ በአካል የማታውቃቸው አክስት እንዳሏትም አጥንታለች። ከገጠር ወጥታ ስለማታውቅ ልቧ ቢሸበርም ወደቤቷ መመለስን እስርቤት የመውረድ ያህል ስለጠላችው ፍርሀቷ ከነጋዴዎች ጋር ከመጓዝ አላገዳትም።

ከነጋዴዎች ጋር ስትጓዝ አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰው ወዴት እንደምትሄድ ጠየቋት። ችግሯን ዘርዝራ ነገረቻቸው። ነጋዴው አክስቷን ፈልገው እንደሚያገናኟት ሀዘኔታ በተሞላበት ንግግር ቃል ገቡላት። ተስፋ ሰንቃ ደሴ ከተማ እንደደረሰች አዛውንቱ ነጋዴ ለጊዜው ከእሳቸው ቤት እንድታርፍ አደረጉ። ከሦስት ቀናት በኋላም ከአክስቷ ጋር አገናኟት። ቀና ልብ ያላት መሆኗን በረጅም እድሜያቸው ካካበቱት ልምድና እውቀት ስለተረዱ ከቤተሰቦቻቸው እንድትርቅ አልፈለጉም። በዚህ "ሰው በዝቶ ሰው በጠፋበት ዘመን" አስረበብን ማግኘት እንደእድል ስለቆጠሩት ከአክስቷ ጋር ትንሽ ከቆየች በኋላ ከንግድ ድርጅታቸው በጽዳት ሥራ እንደሚቀጥሯት ቃል ገቡላት። ከአንድ ወር በኋላም የምትሠራውን ሥራና የምትሠራበትን ጊዜ አስረድተው ሥራ አስጀመሯት። እየመከሩና ተጨማሪ ተስፋ እየሰጡ አለማመዷት።

አስረበብ አዛውንቱን ነጋዴ እንደአባት ቆጥራ በታማኝነት ከተመደበችበት ሥራ በተጨማሪ ሁለገብ ሆና ስትሠራ፣ አንድ ቀን ያልታሰበ ነገር ገጠማት። እንደልማዷ በጥዋት ገብታ ስታፀዳ በህይወቷ አይታው የማታውቅ ከፍተኛ ገንዘብ አንድ ክፍል ውስጥ ወድቆ አገኘች። ለጊዜው ብትደነግጥም ወደቀልቧ ስትመለስ ገንዘቡን ይዛ ባለቤቱ እስኪመጡ ለመጠበቅ ወሰነች።

ኹለት ሰዓት ሆኖ ሌሎች ሠራተኞች ለሥራ ሲገቡ ያለዱሮዋ ቁጭ ብላ ስላገኟት "የዛሬ ዕዳት ሙሉ ቀን ነው እንዴ?" በማለት ቀለዷት። እሷም "እንደእናንተ የሙሉ ቀን ሥራ ባገኝ ብዬ ነው" በማለት ቀልዳቸውን በቀልድ መለሰች። የድርጅቱ ባለቤትም ገርሟቸው "እስከአሁን አለሽ እንዴ?" በማለት ጠይቋት። አይን አይኗን እያዩ። "ላገኝዎት ፈልጌ ነው" ስትላቸው ሥራ ለቅቃ ልትሄድ መስሏቸው አልተደሰቱም ነበር። ወደቢሮው ሲገቡ ያገኘችውን ብር ደበቅ አድርጋ በማምጣት ስትዘረግፍላቸው ፈጠው ቀሩ። ከካዝና ዕቃ ሲያወጡ መልሰው ያላስገቡት ገንዘብ መሆኑን ሲያስታውሱ፣ ከገንዘቡ መገኘት ይበልጥ እሷን ቤተሰብ ለማድረግ በወሰኑት ውሳኔ እየተደሰቱ ምን ሊያደርጉላት እንደሚገባቸው ማሰብ ጀመሩ። ለጊዜው ለታማኝነቷ አመሰግነው ከአሰናበቷት በኋላ አንድ ሐሳብ መጣላቸው። ብትማር ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ እንደምትችል በማመን እንደልጆቻቸው ሊያስተምሯትና ለወግ ለማዕረግ ሊያበቋት ወሰኑ።

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

   ሀ. አስረበብ በልጅነቷ መዳሯ ምን አስከተለባት?

   ለ. አዛውንቱ ነጋዴ ስለአስረበብ ቀናነት "ከረጅም እድሜያቸው ካካበቱት ልምድ ወይም እውቀት ተረድተው" ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ከምንባቡ ይዘት ተነስታችሁ የምንባቡ ርዕስ ለምን “መታመን ለራስ ነው” እንደተባለ አስረዱ።

መ. ነጋደው ጠፍቶ ከተገኘው ገንዘብ ይበልጥ አስረበብን ቤተሰብ ለማድረግ የወሰኑት ውሳኔ ለምን ያስደሰታቸው ይመስላችኋል?

ሠ. እናንተ በአስረበብ ቦታ ብትሆኑ ገንዘቡን ምን ታደርጉት ነበር? ለምን?

ረ. ነጋደው በታማኝነቷ የተነሳ ለአስረበብ ባደረጉላት መልካም ነገር ደስተኛ ናችሁ? እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

ሰ. “ሰው በገዙ ሰው በጠፋበት ዘመን” የሚለውን ሐሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አስረዱ።

2. የሚከተሉትን ክዋኔዎች በምንባቡ መሠረት በቅደምተከተል አስተካክሉ።

ሀ. በልጅነት መዳር

ለ. ሥራ መቀጠር

ሐ. መኮብለል

መ. የተረሳ ገንዘብ ማግኘት

ሠ. የመማር እድል ማግኘት

ረ. የነጋደው ቤተሰብ መሆን

ሰ. ችግሯን መዘርዘር

ሸ. ደስተኛ አለመሆን

ቀ. ከነጋዴዎች መገናኘት

በ. ታማኝነት

ተ. ቀናነት

አቀላጥፎ ማንበብ

“መታመን ለራስ!” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

1.1.2 ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት “መታመን ለራስ ነው!” በሚለው ምንባብ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. አቻ

ለ. ኮበለለች

ሐ. ልቧ ተሰበረ

መ. ተስፋ ሰንቃ

ሠ. ወደቀልቧ ስትመለስ

ሠ. አስረድተው

ረ. ሁለገብ

ሸ. ላገኟት ፈልጌ

መጻፍ

በሚከተለው ቢጋር መሠረት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ቢጋር

- ሳልና ትኩሳት ያለበት በሽተኛ
- ሐኪምቤት መሄድ፣
- የደም፣ የሽንት፣ የሰገራ፣ የራጅ ምርመራ ማድረግ፣
- የምርመራ ውጤት ሳንባ ምች መሆን፣
- መድኃኒት መውሰድና ፈውስ አለማግኘት
- ሌላ ምርመራ ማካሄድ...

1.1.3 ማዳመጥ

የባለሙያ ምክር

ቅድመማዳመጥ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሥዕሉንና ርዕሱን አይታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ለ. በጥንካሬው/ዋ ተምሳሌት የሆነ/የሆነች ሰው ታውቃላችሁ?

ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

   ሀ. ሞላልኝ ምን ዓይነት ባሕርይ ያለው አርሶአደር ነው?

   ለ. ሞላልኝ የተበሳጨው በምን ምክንያት ነው?

   ሐ. የግብርና ባለሙያው የሞላልኝን መሬት በጎበኘ ቁጥር አይኑ ለምን ወንዙ ላይ ያርፋል?

   መ. የአርሶአደሩ ችግር የእርሻ መሬት ማነስ ነው፤ ለዚህ ችግር ባለሙያ ማናገር ለምን አስፈለገው?

ሠ. የግብርና ባለሙያውና ሞላልኝ የተወያዩበት ወቅት መቼ ነው?

ረ. የግብርና ባለሙያው ከሞላልኝ ጋር ለመሥራት ያቀዳቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ሰ. የግብርና ባለሙያው ከአቀዳቸው ተግባራት መካከል በዋና ሥራነት የያዘው የትኛውን ነው?

ሸ. የባለሙያው ምክር ያስገኛቸው ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

2. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



ሰዋስው

ዐምስት አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፡-

አወንታዊ ዓረፍተነገር	አሉታዊ ዓረፍተነገር
መስከረም ጥሩ መጽሐፍ ገዝታለች።	መስከረም ጥሩ መጽሐፍ አልገዛችም።

1.2.1 አንብቦ መረዳት

ሳትከፍለኝ አታብዳትም

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “ሳትከፍለኝ አታብዳትም” ከሚለው ርዕስ በመነሳት የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ተናገሩ።

ለ. ጤነኛ ሰው የአዕምሮ ችግር ያለበትን ሰው ባሕርይ የሚያሳይ ይመስላችኋል? ለምን?

“ሳትከፍለኝ አታብዳትም”

አንድ ባለፀጋ ነበሩ። ገንዘባቸው ሥራ እንዳይፈታና ሥራ ላይ እንዲውል ፍላጎት ነበራቸው። በዚህም ብዙ ወገኖቻቸውን ለመጥቀም እንዲያስችላቸው፣ በኢንዱስትሪዎቻቸው በማሰማራት ሰዎችን ጠቅመው እሳቸውም ይጠቀሙ ነበር። እኚህ ባለፀጋ መሬት በተገቢ ታርሶ እጥፍ ድርብ ምርት ካልሰጠ ዋጋ እንደሌለው ሁሉ፣ ገንዘብም በሳጥን ከተቀመጠ ኪሳራ እንጅ ትርፍ የለውም የሚል ብሂል አላቸው። ባለፀጋው ገንዘባቸው ትርፍ እንዲያስገኝና ለበርካታ ሕዝብ የሥራ እድል እንዲፈጥር ማድረግ የዘወትር ጥረታቸው ነበር። በዚህም በልዩ ልዩ ሥራዎች ውስጥ ብዙ ሠራተኞች እየቀጠሩ በማሠማራት ሰዎችንና ራሳቸውን ተጠቃሚ ያደርጉ ነበር።

ባለፀጋው በየሥራ ክፍሉ ውስጥ ገንዘብ ያዥና ሂሳብ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች አሏቸው። ነገር ግን አንዳንድ ሠራተኞች፣ከመጥፎ ምግባራቸው የተነሳ፣ የተሰጣቸውን እምነት በማጉደል፣ ክብራቸውን ከማጣትና ከመዋረድ ባለፈ የቤተሰብና የዘመድ ማፈሪያ ይሆኑ ነበር። በእኚህ ባለፀጋ አንድ የሥራ ክፍል ውስጥ፣ የዚህ ዓይነት መጥፎ ባሕርይ ያለው ሰው ነበር። ሰውየው የእጅ አመል ያለበትና ያለልክ በአጭር ጊዜ ሀብታም መሆን የሚመኝ ስለነበር የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ከሚቀመጥበት ካዝና ብር እያወጣ ለግሉ ይጠቀም ነበር። “አይነጋም መስሏት...” እንደሚባለው ዛሬ ኹለት፣ ነገ ሦስት እያለ በርካታ ገንዘብ እየመዘበ፣ በተለያየ ስፍራ ቦታ መግዛት፣ ሕንፃ መገንባት፣ በዘመድ አዝማድ ስም ቋሚ ንብረት ማፍራት የዘወትር ተግባሩ አደረገው።

ነገር ግን፣ የሠራተኛውን ደርሶ ባለብዙ ንብረትና ሀብታም መሆን የታዘቡ የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞችና የአካባቢው ነዋሪዎች “በዚህ ደመወዝ ይህን ሁሉ ቤት እንዴት ይሠራል?” የሚል ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ። ጉዳዩ የብዙ ሰው መነጋገሪያ

ሆነና ሹክሹክታው ከባለፀጋው ጆሮ ደረሰ። የጥርጣሬውን ወሬ ከብዙ ሰው የሰሙት ባለፀጋ፣ በሥራ ክፍሉ ላይ የሂሣብ ምርመራ አስደረጉ።

የሂሳብ ምርመራው ውጤት ለባለፀጋውና ለክፍሉ ሠራተኞች ይፋ ተደረገ። በዚህም የምርመራ ግኝት ገንዘብ ያገኙ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ጉደለት ተገኝበት። በዚህ ጊዜ ባለፀጋው ተበሳጭተው ገንዘቡን የት እንዳደረሰውና ለምን ተግባር እንዳዋለው ተመርምሮ በእምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ ወሰኑ። ወደፓሊስ ጣቢያም ሄደው አመለከቱ። ሠራተኛው ግን የሠራውን ስለሚያውቅ፣ የሚያመልጥበትን ዘዴ ያስብ ጀመር።

ሠራተኛው ከተጠያቂነት ለማምለጥ እንደአበደ ሰው መሆን ጀመረ። በፓሊስ ተይዞ በሚሄድበት ጊዜ ይዘላል፣ ይፈርጣል፣ ይቀባዥራል። በተጨማሪም የአእምሮ ህመምተኛ የሚያሳያቸውን ባህሪያት ልብስ መቅደድ፣ ልማታ ማለት፣ ማንራት፣ መጮህ ጀመረ። ባለፀጋው የሠራተኛውን ሁኔታ ሲመለከቱ ግራ ገባቸው። "ይህ ሰው አበድኩ የሚለው ገንዘቤን ላለመክፈል ነው?" ሲሉ ራሳቸውን ጠየቁ። ውሎ አድሮ በተደረገው የፓሊስ ምርመራ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ በማዋል ስለተጠረጠረ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ተደረገ። ሠራተኛውም በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የተለመደውን የእብደት ተግባራቱን በችሎት ላይ ማንፀባረቁን ተያያዘው።

ባለፀጋውና ሠራተኛው በችሎት በቀረቡበት ጊዜ፡-

ዳኛው፡- "ገንዘቡን የት ነው ያደረግኸው? ወዴትስ ነው ያስቀመጥከው? እስቲ እውነቱን ተናገር" ሲሉ እንዲያስረዳ ፈቀዱለት።

ሠራተኛው፣ ሥራውን ያውቃልና "ትናንት ነው የተወለድኩት፣ የገንዘብ ዓይነት ማየት አልፈልግም" እያለ የባጥ የቆጡን ይቀባጥር ጀመር።

ባለፀጋው፣ በጣም ተናደው "አቶ በትኔ እባክህ ያበድክ በመምሰል የምትሰጠውን መልስ ትተህ እውነተኛውን ተናገር!" አሉት።

ሠራተኛው፡- ባለፀጋው በተናገሩት ጉዳይ ይናደዳል ጮክ ብሎ "ራሴ ዞሯል፤ ምን እንደምትሉኝ አላውቅም" እያለ ለመማታት ይሞክር ጀመር።

ባለፀጋው፡- "እባክህ አትልፋ ወዳጄ! ምንም ቢደረግ ዛሬ ገንዘቤን ሳትከፍለኝ አታብዳትም" አሉት።

ዳኛው፡- የባለፀጋውን ሁኔታ ከግምት በማስገባት በወንጀል የተጠረጠረው ሠራተኛ አእምሮ ጤነኛ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የህክምና ማስረጃ እንዲመጣላቸው ቀጠሮ ሰጥተው የዕለቱ ችሎት አበቃ።

በቀጠሮው ቀን ዳኛው የምርመራ ውጤቱን አይተው ሠራተኛው ጤነኛ መሆኑ የተረጋገጠ ሆነ። ስለዚህ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ዳኛው ኹለት ዓይነት ፍርድ ሰጡ። አንደኛ፣ ሠራተኛው በተከሰሰበት ገንዘብ የማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ በመሆኑ በስሙ የነበሩ ንብረቶች ተሸጠው ለባለፀጋው እንዲከፈል; ኹለተኛ፣ ሠራተኛው ችሎቱን በማታለል ወንጀል ጥፋተኛ በመሆኑ በኹለት ዓመት የእስራት ቅጣት እንዲቀጣ ወሰኑ።

(ከበደ እንግዳሰው። ነገር በምሳሌ። ከገጽ 70-74 ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "ታርሶ ምርት ያልተመረተበት መሬትና ሳጥን ውስጥ ተቆልፎ የተቀመጠ ገንዘብ አንድ ናቸው" የሚለውን ሐሳብ አብራሩ።

ለ. የባለፀጋው መልካም ሐሳብ ምን እንደሆነ አስረዱ።

ሐ. "ወትሮ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ወጭት ጥዶ ማልቀስ" የሚለው አባባል እምነት ያጎደለውን ሠራተኛ እንዴት እንደሚገልጽ አስረዱ።

መ. የአካባቢው ሰዎች እምነት ያጎደለውን ሠራተኛ መጥፎ ተግባር ለባለፀጋው መንገራቸውን ትደግፋላችሁ ወይስ አትደግፉም? ለምን እንደደገፋችሁ ወይም እንዳልደገፋችሁ ምክንያት እየሰጣችሁ አስረዱ።

ሠ. ባለፀጋው "ሳትከፍለኝ አታብዳትም" ያሉበትን ምክንያት አብራሩ። ማበድ አለማበድ በፈቃድ የሚሆን ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

"ሳትከፍለኝ አታብዳታም" በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

1.2.2 ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፦

1. ፍላጎት፦ አንድ ነገር ለመስራት መነሳሳት

2. ወገን፡- የቅርብ ወይም የሩቅ ዘመድ፣ የአካባቢ ሰው፣ የሀገር ሰው?

ሀ. እምነተቢስ
መ. ባለፀጋ
ሰ. ቋሚ ንብረት
ለ. ካዝና
ሠ. ደመወዝ
ሸ. ማኅበራዊ ጉዳይ
ሐ. እየመዘዘ
ረ. ዘመድ አዝማድ

መጻፍ

“አውቆ አበድ” በሚል ርዕስ፣ በምክንያትና ውጤት ስልት የተዋቀረ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

1.2.3 መናገር

ሀ. አንድ ሰው ሆን ብሎ (ፈልጎ) ሊያብድ ይችላል?

ለ. “አውቆ አበድ” ማለት ምን ማለት ነው? አውቆ አበድነት ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል?

ሐ. በቡድን ውይይታችሁ የተስማማችሁባቸውን ነጥቦች፣ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሰዋስው

ሦስት ሐተታዊ ዓረፍተነገሮችን ጻፉና እያንዳንዳቸው በርካታ መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. “ዘነበች ትናንት ከእህቷ ጋር ከገጠር በፈረስ ለስራ ፈጥና መጣች።”

ሀ. ዘነበች መጣች?

ለ. ዘነበች መቼ መጣች?

ሐ. ዘነበች እንዴት መጣች?

መ. ዘነበች በምን መጣች?

ሠ. ዘነበች ለምን መጣች?

ረ. ዘነበች ከየት መጣች?

2. የተለያዩ መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም “ዞማ ከጓደኛዋ ጋር ትናንት በመኪና ወደደባርቅ ሄደች” የሚለውን ዓረፍተነገር መነሻ አድርጋችሁ የተለያዩ ጥያቄያዊ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፦ ወደደባርቅ የሄደችው ማን ናት?

1.3.1 አንብቦ መረዳት

ግን ምን ነካን!?

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች “ግን ምን ነካን!?” ሲሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ሲያጋጥማቸው ነው እንዲህ የሚሉት? እናንተ እንዲህ ብላችሁ ታውቃላችሁ?

ለ. ሥዕሉንና ርዕሱን አይታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ሐ. በድሮ ትውልድ ነበሩ፣ በአሁኑ ትውልድ ቀሩ፣ የሚባሉ ነገሮች ታውቃላችሁ? የምታውቋቸው ካሉ ጥቀሱ።

ግን ምን ነካን!?



አፍና እጅ ከተራራቁ ቆይተዋል፤ ቃልና ተግባር ከተፋቱ አመታት ተቆጠሩ፤ አንደበት ሌብነትን እያወገዘ እጅ በድብቅ ይመነትፋል፤ አፍ! እዚችው አፈር እንደተፈጠርኩ እዚችው እሞታለሁ ሲል፣ ልብ ባሕር ተሻግሮ ወደውጭ ይኮበልላል።

ግን ምን ነካን!? በራስ መኩራታችን የት ደረሰ!? የሀገርና የወገን ፍቅራችን ምን በላው? በሀገር ናፍቆት ትምህርታቸውን፣ ምቾታቸውን ትተው የሚመጡ ቆራጥ ዜጎች የት ደረሱ? በሀገር ሠርቶም፣ ተሹሞም፣ ተንገላቶም ከመኖር ይልቅ የሰው ሀገር የውርደት /የስደት/ ኑሮ የሚያልም ትውልድ ከየት መጣ? “የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም” ይባል ነበር፤ በማናውቀው ሀገር ናፍቆት ልንሞትኮ ነው? የሆነውስ ሆነና ማነው ተጠያቂው? ትውልድ ወይስ ትውልዱን ያፈራው...?

ከሰው ሀገርም እኮ ጥሩው ነገር ቢናፍቀን መልካም ነበር። የራሳችንን ታሪክና ባህል ጠንቅቀን በማወቅ ጎጂውን እንደገለባ አንጓለን፣ ጥሩውን እንደወርቅ አጥርተን፣ የጎደለንን ከሌላው ብንናፍቅ ያስመሰግነናል እንጂ አያሥነቅፈንም። የሌላውን

ጠንካራ የሥራ ባህል፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት አከባበር ልማድ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጅ እውቀት ወዘተ ብንሻማ፣ ለሀገር እድገት ይጠቅመናል። ችግሩ ያለንንና የሌለንን ለይተን ሳናውቅ ያገኘነውን በጭፍን ማግበስበሳችን ነው። አደጋው ከባህላችንና ከታሪካችን ውስጥ ጠቃሚውና በኩራት ልንጠብቀው የሚገባን የቱ ነው? በማለት ቆም ብለን ራሳችንን አንጠይቅም። በአንጻሩ እነሱ የሚፈፅሙትን ከሃይማኖትና ከሞራል እሴቶች የሚቃረን ልማድ ተቀብለን ለመተግበር ጊዜ አይወስድብንም፤ እንደስልጣኔም እንቆጥረዋለን። "በሬ ሆይ! በሬ ሆይ! ሳሩን አይህና ገደሉን ሳታይ" እንደሚባለው እዚያ ማዶ ያየነውን ሁሉ እየተመኘን፣ ዓይናችን በብልጭልጭ ነገሮች እየተጋረደ ገደል እየገባን ነው። ዛሬ ዛሬ ከአባቶች የተቀበልነውን ሃይማኖት፣ ትውፊት፣ ሥርዓትና ባህል በደምሳሳው ኋላቀር አድርገን እንድንቆጥር እየተደረገ ነው። የሚሠሩትን መጥፎም ይሁን መልካም መቀበል እንዳለብን እያመንን ነው።

ላልይበላን፣ አክሱምን፣ የፋሲል ግንብን፣ የሶፎ ኡመር ዋሻን ፣ ጢያን... ከማየት ይልቅ አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ የአርሶአደር መንደር መርገጥ፣ ስለሀገራችን ጀግኖች ከሚወራልን ይልቅ ስለሆሊዩድ የፊልም ተዋንያን መስማት እንወዳለን። ይህ ነው ዋና ችግራችን፣ የሌለውን የመመኘት አባዜ። ሁላችንም የእድላችንን መቃናት ውጭ ሀገር ከመሄድ አለመሄድ ጋር አስተሳስረነዋል። በጅ! ይሁን። መሄድ ቀናን እንበል፤ የቀሩትንስ እናቶችና አባቶች ማን ይንከባከብ፣ ይጡር? ለወንድምችና እህቶች ማን ድጋፍ ይሁን? ማን ይታደጋቸው? መስዋዕትነት ከፍሎ ወገንን ከችግር አረንቋ የሚያወጣ ጀግና ከየት ይምጣ? አቅምና ጉልበት ያለው ወጣቱ ነው፤ ጎልማሳው ነው። ግን ዝግጁ ነው? በብልጭልጭ ባህልና ወኔ በሚሰብር ሱስ ልቡ ተሰልቦ፣ ሳይደክም ማግኘትን፣ ሳይማር ማወቅን፣ ሳይሠራ ሀብትን ... የሚናፍቀውን ወጣት ትውልድ ማን ያቃናው? ማን ያስተምረው?

የችግራችን እምብርት ይህ ነው። ለሀገር መስዋዕትነት የሚሆን ጀግና መፍጠር አልቻልንም። በቃ! በአፋችን ሀገሬ ሀገሬ ስንል ቆይተን ችግር ሲመጣ እናት ሀገር አጣች ነጣች፣ አልደላችንም እያልን የዜግነት ግዴታችንን አሸቀንጥረን ጥለን ሌላ እናት ፍለጋ እንሄዳለን፤ የእንጀራ እናት። በቃ! እንዲህ ነው።

የሥራ ጀግና የአስተሳሰብ ጀግና መፍጠር አለብን። ቃልና ተግባሩ አንድ የሆነ፣ ሠርቶ የሚያሠራ፣ ከችግራችን መንጥቆ የሚያወጣን በርካታ ጀግና ያስፈልገናል። ይህ እድል ያለው ደግሞ በወጣቱ እጅ ውስጥ ነው። አንዳንዱ እየባነነ ነው። ሁላችንም ልንባንን ይገባል፤ ከማዕበሉ መውጣት አለብን። ምክንያቱም በሀገራችን ጉዳይ ሁላችንም ተጠያቂዎች ነንና።

(አማርኛ መማሪያ መጸሐፍ 8ኛ ክፍል፤ 1996። ገጽ 18-20 ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በምንባቡ የተጠቀሱትን የሀገርና የውጭ ሀገር መልካም ነገሮች በመጠቀም የሚከተለውን የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር አሟሉ።



ለ. በምንባቡ መሠረት ጀግና ምን ዓይነት ሰው ነው? ድሮና ዘንድሮ ወደውጭ ለትምህርት ይሄዱ የነበሩ ተማሪዎችን እያወዳደራችሁ ስለሀገርና ወገን ፍቅር ሐሳብ ስጡ።

ሐ. ትውልዱ ወይስ ትውልዱን ያፈራው ... በሚለው ሐረግ ክፍት የተተወው ቦታ ምን በሚል ሐሳብ ሊሟላ ይችላል?

መ. "በማናውቀው ሀገር ናፍቆት ልንሞት ነው" የሚለውን አገላለፅ "የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም" ከሚለው ብሂል ጋር እያነፃፀራችሁ አብራሩ።

ሠ. "በሬ ሆይ! በሬ ሆይ! ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ" የሚለውን አባባል የሰው ሀገር ከመናፈቅ ጋር እያገናዘባችሁ አስረዱ።

ረ. "የእድገታችንን መቃናት ከሀገር ማዶ ወርውረነዋል" የሚለውን ሐሳብ ከምታውቁት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘባችሁ አስረዱ።

አቀላጥፎ ማንበብ

"ግን ምን ነካን!?" በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

1.3.2 ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቺ ጻፉ።

   ሀ. ነጮች　　ሐ. ወግ　　ሠ. አንጓለለ

   ለ. ባህል　　መ. ሥርዓት　　ረ. ትውፊት

2. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ጻፉ።

   ሀ. ነጮች　　ሐ. በደምሳሳው　　ሠ. እምብርት

   ለ. ጀግና　　መ. እድላችን　　ረ. ሳይደክም ማረፍ

መጻፍ

በሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩ መሠረት "የራስ ሀገርና የሰው ሀገር" በሚል ርዕስ በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ድርሰት ጻፉ ።



1.3.3 መናገር

ሀ. በኹለት ቡድን ተከፍላችሁ አንደኛው ቡድን "በሀገራችን በጎ የሆኑና በጎ ያልሆኑ ባህሎች" በሚል ርዕስ ይወያይ። ኹለተኛው ቡድን "በውጭ ሀገራት በጎ የሆኑና በጎ ያልሆኑ ባህሎች" በሚል ርዕስ ይወያይ።

ለ. የውይይቱን ውጤት የቡድኖቹ ተወካዮች ለክፍሉ ተማሪዎች ያቅርቡ፤ የማትስማሙባቸው ነጥቦች ካሉ ተከራከሩባቸው።

ሰዋስው

1. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አወንታዊ ወይም አሉታዊ ወይም መጠይቃዊ መሆናቸውን ለዩ።

   ምሳሌ፡-

   አስቴር አገሯን ትወዳለች። (አወንታዊ)

   አስቴር ነገር አትወድም። (አሉታዊ)

   አስቴር አገሯን ትወዳለች? (መጠይቃዊ)

   ሀ. አፍና እጅ ከተራራቁ ቆይተዋል።

   ለ. ቃልና ተግባር አልተፋቱም።

   ሐ. በራስ መኩራታችን የት ደረሰ?

   መ. በሀገር ናፍቆት ምክንያት ትምህርቱን ትቶ መጣ።

   ሠ. በሰው ሀገር መኖር ቢደላም ክብር አይደለም።

2. የሚከተሉትን ግሶች በ2ኛና በ3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ቅርጽ ጻፉ።

   ምሳሌ፡-

ግስ	2ኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር	3ኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር
ሰነቀ	ሰነቃችሁ	ሰነቁ
ወሰደ	ወሰዳችሁ	ወሰዱ

   ሀ. ከፈተ

   ለ. መከረ

   ሐ. ፈለገ

   መ. ወደቀ

   ሠ. ዘፈነ

   ረ. ከበረ

ምዕራፍ 2

ባህላዊ ቅርሶች

2.1.1 አንብቦ መረዳት

ዘመን ያልሻረው ጥበብ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሥዕሉንና ርዕሱን አይታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ለ. የምታውቋቸውን የቱሪስት መስህቦች ዘርዝራችሁ ጻፉ።

ዘመን ያልሻረው ጥበብ



ታሪኩ እባላለሁ። የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ነኝ። በተለያዩ ቦታዎች በቅርስ አሰጎብኝነት አገልግያለሁ። በዚህም የተነሳ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቅርሶችን የማወቅ እድል አግኝቻለሁ። ኢትዮጵያ ዘመን ያልሻረው የኪነሕንፃ ጥበብ ያረፈባቸው ቅርሶች ባለቤት ናት። በዚህም ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ጎብኚዎች ይጎበኟታል። እኔም ዛሬ በኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ጥንታዊ ኪነሕንፃዎችን ላስቃኛችሁ ወደድሁ።

የኪነሕንፃ ቅርሶች የየዘመኑ የፈጠራ ጥበብ ውጤቶች ናቸው። ቅርሶቹ የየዘመኑን ስልጣኔ ጥበብ ጥልቀትና ደረጃ ያሳያሉ። በኢትዮጵያ ከታወቁ ባህላዊ ኪነሕንፃዎች መካከል የአክሱም ሐውልቶች፣ የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት፣ የፋሲል ግንብና የጀጎል ግንብ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ቅርሶች ባሉባቸው ቦታዎች ሄዶ ለተመለከታቸው የሀገሬውም ሆነ የውጪ ጎብኚ እርካታ፣ ሀሴትና አድናቆትን ይፈጥራሉ።

የአክሱም ሐውልቶች በትግራይ ክልል፣ በአክሱም ከተማ ይገኛሉ። የተሠሩትም ከ700- 200 ዓመተ ዓለም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሐውልቶቹ በጥበብ ደረጃቸው በዚህ ዘመን ከታነፁት ሐውልቶች ሁሉ የላቁ ናቸው። ተደጋግመው ቢታዩ አይጠገቡም። በጥንታዊነታቸውም ሆነ በቅርፃቸው ከሌሎች ኪነሕንፃዎች በእጅጉ ይለያሉ።

የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት የጥንቱን ዘመን የኪነሕንፃ አሠራር ጥበብን አጉልተው ያሳያሉ። ኢትዮጵያ የሺህ ዘመናት የስልጣኔ ታሪክ ያላት ለመሆኑ ምስክሮች ናቸው። አብያተክርስቲያናቱ የታነፁት በ12ኛው መቶ ክፈለ ዘመን መጀመሪያ በንጉስ ላልይበላ ነው። አብዛኞቹ አብያተክርስቲያናትም ከአንድ አለት ድንጋይ ተፈልፍለው የታነፁ በመሆናቸው ግርምትን ይፈጥራሉ። በዚያን ዘመን አንድን የተጠፈጠፈ አለት ፈልፍሎ ማነፅ ተችሏል። በአሁኑ ዘመን ግን ለመሥራት ሳይሆን ለማሰብ ያዳግታል። የአብያተክርስቲያናቱ ጥንታዊነትና የኪነሕንፃ ጥበባቸው የዓለምን ሕዝብ አድናቆትን በማትረፋቸው በተባበሩት መንግስታት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም ቅርሥነት ተመዝግበው የቱሪስቶች መዳረሻ ሆነዋል።



የፋሲል ቤተመንግስት ግንብም ሌላው ድንቅ የሥነሕንፃ ቅርሳችን ነው። ግንቡ የታነፀው በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩት ነገስታት ነው። የሕንፃዎቹ የአሠራር ጥበብ በዚያ ዘመን የነበረውን ስልጣኔ ያሳያል። የግቢው ስፋት፣ የሕንፃዎቹ ጥበባዊ አሠራርና በውስጡ ያሉ የነገስታቱ መዝናኛ ቦታዎች ያስገርማሉ። በ70,000 ካሬ ሜትር የተንጣለለ ቦታ ላይ ያረፈው የሕንፃው ግቢ፣ በውስጡ፣ በዘመኑ የነበሩ የስድስት ነገስታት ቤተመንግስቶችና በርካታ የሕንፃ ፍርስራሾች ይዟል። በጎንደር ከተማ የሚገኘው የፋሲል ቤተመንግስት ግቢ 12 በሮች ነበሩት።



እነሱም እንኮዬ በር፣ እቃግምጃቤት በር፣ ፊት በር /ጃንተክል በር/፣ ወንበር በር፣ ኪሊ በር፣ እምቢልታ በር፣ ፈረስ ባልደራስ በር፣ እርግብ በር፣ ቀጭን አሸዋ በር ይባላሉ። በአሁኑ ጊዜ ግን አገልግሎት የሚሰጡት በጣሊያን ጊዜ የተሠሩ ኹለት በሮች ብቻ ናቸው።

በኢትዮድያ በኪነሕንፃ ጥበብ ሌላው የሚጠቀሰው የሀረር ጀጎል ግንብ ነው። ግንቡ የታነፀው በታላቁ አሚር ኑራቢን መጀሂድ ከ1551-1552 ዓ.ም እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ግንቡ በ48 ሄክታር ስፋት ላይ ያረፈ ሲሆን 3334 ሜትር ርዝመትና 3.66 ሜትር ከፍታ አለው። አንደኛው አስገራሚው ነገር ግንቡ ዐምስት መግቢያና መውጫ በሮች ያሉት መሆኑ ነው። እንዲሁም በውስጡ ከ359 በላይ ጠባብ መንገዶች ርስበርሳቸው የሚገናኙና ጥልቅ የኪነሕንፃ ጥበብን የተላበሱ መሆናቸው ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ነው።



በአጠቃላይ ኢትዮድያ ረጅም ዘመናት ያስቆጠረ ረቂቅ የኪነሕንፃ ጥበብ ባለቤት ናት። ይህም የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የስልጣኔ ሂደቶች በግልፅ የሚታዩባት ሀገር አድርጓታል።

(አብክመ ባህልና ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። (1991።) ከገጽ 81-85 ተሸሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

ሀ. በምንባቡ ከተጠቀሱት የኪነሕንፃ ቅርሶች ሁሉ ቀደምቱ የትኛው ነው?

ለ. ከላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናትና ከፋሲል ቤተመንግሥት ግንብ ቀድሞ የተሠራው የትኛው ነው?

ሐ. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ዘመን ያልሻራቸው ቅርሶች መካከል ከሰሜን ኢትዮድያ ውጭ የሚገኘው የትኛው ነው?

መ. ጽሑፉ ውስጥ ከተጠቀሱት ቅርሶች ያስደነቃችሁ የትኛው ነው? ለምን?

በ“ሀ” ስር የቀረቡትን ሐሳቦች የሚገልጹ ከአንድ በላይ አማራጮችን ከ“ለ” ክፍል በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. የአክሱም ሐውልት	ሀ. በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ክፍለዘመን የተሠራ
2. የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት	ለ. በትግራይ ክልል የሚገኝ ከ700-200 ዓመተዓለም የተሠራ
3. የፋሲል ቤተመንግሥት ግቢ	ሐ. በውስጡ 3334 ሜትር ርዝመት 3.66ሜ. ከፍታ ያለው
4. የጀጎል ግንብ	መ. 12 በሮች ያሉት
	ሠ. በ12ኛው መቶ ክፍለዘመን የተሠራ
	ረ. በአማራ ክልል የሚገኝ
	ሰ. 70,000 ካሬ ሜትር፣ ቅጥር ግቢ ያለው
	ሸ. በትግራይ ክልል የሚገኝ
	ቀ. ከ1551 - 1552 ዓ.ም. የተሠራ
	በ. በውስጡ 359 ርስበርስ የሚገናኙ ጠባብ መንገዶች የሚገናኙበት
	ተ. የስድስት ነገሥታት ቤተመንግሥታት የሚገኙበት
	ቸ. በ48 ሄክታር ስፋት ላይ ያረፈ ግንብ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ዘመን ያልሻረው ጥበብ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

2.1.2 ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ጥበብ	ሠ. ሀሴት	ቀ. ድንቅ
ለ. ፈጠራ	ረ. ስልጣኔ	በ. ባልደራስ
ሐ. ውቅር	ሰ. አለት	
መ. እርካታ	ሸ. ግርምት	

2. ለተሰመረባቸው ቃላት/ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ኢትዮድያ ዘመን ያልሻረው ጥበብ ያረፈባቸው ቅርሶች ባለቤት ናት።

ለ. የአክሱም ሐውልቶች ድንቅ የኪነሕንፃ ጥበብ ያረፈባቸው ቅርሶች ናቸው።

ሐ. የጥንት ዘመን የኪነሕንፃ ጥበብ አጉልተው ከሚያሳዩ ቅርሶች መካከል የላልይበላ አብያተክርስቲያናት ለአብነት ይጠቀሳሉ።

መ. የፋሲል ቤተመንሥት ግንብ ተደጋግሞ ቢታይ አይጠገብም።

ሠ. የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት ከአንድ አለት የተሠሩ ፍልፍል ሕንፃዎች ናቸው።

ረ. የላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት የኪነሕንፃ ጥበብ ዓለምን ያስደመመ ነው።

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም "ዘመን ያልሻረው ጥበብ" ከሚለው ምንባብ አራተኛ፣ ዐምስተኛና ስድስተኛ አንቀጾችን አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።



2.1.3 ማዳመጥ

የጎዜ መስጊድ

ቅድመማዳመጥ



በአካባቢያችሁ መስጊዶች አሉ? አሠራራቸው ምን ይመስላል? ጥንታዊ ናቸው ወይስ ቅርብ ጊዜ የተሰሩ? ሥዕሉን በመመልከት ስለመስጊዱ አሠራር ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ስለጎዜ መስጊድ ተናገሩ።

ለ. መስጊዱ የተሠራው በየትኛው ክፍለዘመን ነው?

ሐ. በመስጊዱ ውስጥና በዙሪያው የሚገኙ ነገሮችን ዘርዝሩ።

መ. በጎዜ መስጊድ በዓላት የሚከበሩት መቼ መቼ ነው?

ሠ. ከጎዜ መስጊድ ጠቀሜታዎች ዉስጡን ተናገሩ።

ረ. የጎዜ መስጊድ ባለቤት ማነው?

ሰዋስው

1. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የስምና የግስ ገላጮችን ለይታችሁ አውጡ።

   ምሳሌ፡- ጎበዟ ልጅ ነገ ትመጣለች። (“ጎበዟ” የስም ገላጭ፣ “ነገ” የግስ ገላጭ)

   ሀ. ትንሹ ልጅ ክፋኛ ወደቀ።

   ለ. ቀዩ መኪና ነገ ይሠራል።

   ሐ. ብዙ እቃ ትናንት መጥቷል።

   መ. ጎበዝ ተማሪ ቶሎ ይሠራል።

   ሠ. ጥቁሯ ላም አምና ነጭ ጥጃ ወልዳለች።

   ረ. የአስቴርን መጽሐፍ በመቀስ ቀደደው።

2. የስምና የግስ ገላጭ ያላቸው ሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

2.2.1 አንብቦ መረዳት

አይዳሰሴ ቅርሶች

ቅድመንባብ

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



ለ. የማይዳሰሱ ቅርሶች ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እስቲ የምታውቋቸውን የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ጥቀሱ።

አይዳሰሴ ቅርሶች

ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል ቃላዊ ግጥሞች ይጠቀሳሉ። ቃላዊ ግጥሞች የተለያዩ አጋጣሚዎችን መሠረት አድርገው የሚገጠሙ፣ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች የሚያሳዩ የጠንካራ ስሜት መገለጫዎች ናቸው። ሰዎች እንደየባህላቸው የአኗኗር ስልታቸውን፣ ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ ምኞታቸውንና ፍላጎታቸውን ይገልፁባቸዋል። ከቃላዊ ግጥሞች መካከል የሐዘን፣ የሠርግ፣ የእርሻና የሙገሣ ግጥሞች ዋነኞቹ ናቸው። ግጥሞቹ ቃላዊ ቢሆኑም አይረሴ ሆነው የመቆየት አቅም አላቸው።

የሐዘን ግጥሞች ሰዎች ወገኖቻቸውን በሞት ሲነጠቁ፣ ስሜታቸው በሐዘን ሲዋጥ እንዲሁም በለቅሶ ጊዜ የቀብር ሥርዓቱን ለማድመቅ የሚከናወኑ ሲሆኑ እንደሚኞቹ ሰብዕና የሚዜሙ የሐዘን ግጥሞች የተለዩ ናቸው። ግጥሞቹ ሐዘንተኞቹ ራሮታቸው ከውስጣቸው ገንፍሎ እንዲወጣላቸው የማድረግ ሀይልና ፋይዳ አላቸው። ከነዚህም በተጨማሪ የሞትን ክፉ ሥራ ለመኮነንም ጭምር ያገለግላሉ።

ከሐዘን ግጥሞች መካከል ለአብነት ያህል፡-

ሀ. ሰው የማያውቀው ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣

ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ፣

ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ፣

ለ. ምነው እኔ በሞትኩ ድሀው ወንድምሽ፣

የምታበዪበት፣ የምታጠጪበት ከሚፈርስ ቤትሽ።

ሐ. ልላክልሽ እንዴ መቀስና ሚዶ፣

አልተጫነሽ እንደሁ አፈሩ ተንዶ።

መ. አንተ አለኸኝ ብዬ ስመካ ስመካ፣

አወይ የሰው ነገር ሞተህ ነወይ ለካ።

ሠ. ሲሠራው ዋለና ሲያንፀው ሲያንፀው፣

እንደመፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው።

የሠርግ ቃላዊ ግጥሞች ከማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ይካተታሉ። እነዚህም የተጋቢዎችን መልካም ተግባር የሚያሞግሱ ናቸው።

ከሠርግ ግጥሞች መካከል ለአብነት ያህል፡-

ሀ. ሙሽሪት ለምዳለች፣ (2 ጊዜ)

እንዝርቴን፣ ደጋኔን ላኩልኝ ብላለች፣

ለ. የኛ ሙሽራ ስሪ መደብ፣ (2 ጊዜ)

ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ።

ሐ. እንዳላይሽ እንዳላይሽ፣

ዳመናው ጥሏል በላይሽ።

መ. ጡረው ጡረው አማጭህን፣

ከዚች ቆንጆ ያጋባህን።

የእርሻ ቃላዊ ግጥሞች ከማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ይመደባሉ። እነዚህ ግጥሞች ከጥንት ጀምሮ አርሶ አደሮች በእርሻ ሥራ ወቅት ጉልበታቸው እንዲበረታና የሥራ ፍቅራቸው እንዲነሳሳ ይጠቀሙባቸዋል። በግጥሞቹ ራሳቸውን፣ አጋሮቻቸውን፣

መከታዎቻቸውንና በሬዎቻቸውን ያሞግሱባቸዋል። ከዚህም ባለፈ የሥራ ክቡርነትና ጠንክሮ መስራት ጥሩ ምግባር መሆኑን፣ እንዲሁም መቀመጥ የድህነት ምንጭ መሆኑን በግጥሞቹ ይገለፃሉ። ቤታቸው ሙሉ እንዲሆን ጠንክሮ ማረስ አማራጭ ሳይሆን ሕይወት መሆኑን በሥራ ቦታቸው እያስተጋቡ፣ የራሳቸውን ድምፅ እራሳቸው እየሰሙ ይከውኑታል።

ለምሳሌ ያህል፡-

ሀ. አሁን ማን ያውቃል የአርሶ አደሩን ለዛ፣

አሁን ማን ያውቃል የበሬን ለዛ፣

እህል ካልቀመሱ ከንፈርም አይወዛ።

ለ. ማረስ ነው እንጅ የጨባውን ሥር፣

ማረስ ነው እንጅ የግራሩን ሥር፣

ሥርቆት ምንድን ነው ውሻ ይመስል።

ሐ. ማረስ ነው እንጅ እርፍን ነቅንቆ፣

ርሃብ ክፉ ነው ይገላል አንቆ።

መ. በሬው ቀና በል ከጥጉ ድረስ፣

አርሶ የበላ አለው የደስደስ።

ሠ. ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እደሪ፣

አይላትም ሚስቱን ቆጥበሽ እዳሪ።

የሙገሣ ግጥሞች ሰዎች ክብራቸውን የሚገልፁባቸው ናቸው። በክብረ በዓል፣ በቡሄ፣ በሚሻምሾ፣ በመስቀል በዓል እንደየአካባቢው ባህል ወጣቶች፣ ልጃገረዶችና ሕፃናት ልጆች በየቤቱ ሲለምኑ አዋቂዎቹ ለህፃናቱ ስጦታ ከለገሷቸው በኋላ የሙገሣ ግጥሞችን ተጠቅመው አክብሮታቸውን ለአዋቂዎቹ ይገልፃሉ። አዋቂዎቹም ህፃናቱን ይመርቃሉ። እነዚህ ግጥሞች እንደሌሎች ባህላዊና ቃላዊ ግጥሞች ከትውልድ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ የማይዳሰሱ የማህበረሰብ ሀብቶች ናቸው።

ለአብነት ያህል፡-

ሀ. የኔማ ጌታ የሰጡኝ ሙክት፣

አንድ ዓመት ሞላኝ እሱን ሳነክት።

ለ. የኔማ እመቤት የፈተለችው፣

የሸረሪት ድር አስመሰለችው።

ሐ. አምላክ እሷን ሠራ ተጠቦ ተጨንቆ፣

አንገቷ ሚመስለው የእንግሊዝ ብርጭቆ።

መ. የኔ ሴት ወይዘሮ የእኔ ስመ መልካም፣

በእጇ ሥራን እንጅ አፏ ሰው አይካም።

ሠ. በራፉም ይከፈት ሁሉም ይሰናዳ፣

ልክ የለውም አሉ የዚህ ቤት እንግዳ።

በአጠቃላይ ባህላዊ የማይዳሰሱ ቅርሶች ቃላዊ በመሆናቸው እንዳይበረዙ ተፅፈው ሊቀመጡ ይገባል።

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።

   ሀ. ምንባቡ ውስጥ በምሳሌነት ከተሰጡት ግጥሞች ምጣኔው የተዛባ፣ ዜማ የሚሰብር ስንኝ አለ? ካለ አውጥታችሁ ጻፉ።

   ለ. ከቃላዊ የግጥም ዓይነቶች አራቱን ጥቀሱ።

   ሐ. የማህበረሰብ ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች የሚባሉት ምን ምን ናቸው።

   መ. የሐዘን ግጥሞች እንደሚቹ ስብዕና የሚዜሙ ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

   ሠ. “ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ” በሚለው ስንኝ ውስጥ “ሰው ነው ያልነውን ሰው “የሚለውን ሐረግ ሐሳብ አብራሩ።

ማስታወሻ

ምጣኔ፡- ሐረግ ሲነበብ የሚወስደው ጊዜ ነው። የስንኝ ሐረጎች እኩል ጊዜ የሚወስዱ ከሆነ ሲነበቡ የተስተካከለ ዜማ ይኖራቸዋል። የሐረጎቹ ምጣኔ የተዛባ ከሆነ ሲነበቡ ዜማ ይሰብራሉ።

2. በፊደል ተወክለው የቀረቡትን ስንኞች መሠረት በማድረግ የሐዘን፣ የሠርግ፣ የእርሻና የሙገሳ ቃላዊ ግጥሞችን አንድነትና ልዩነት አስረዳ። የግጥሞቹን አንድነትና ልዩነት ለማወዳደርና ለማነፃፀር “ዋይ” ቻርትን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ፦ የሐዘን ቃላዊ ግጥም “ሀ”ና የሠርግ ቃላዊ ግጥም “ሀ”



ሀ. የሐዘን ቃላዊ ግጥም “ለ”ና የሠርግ ቃላዊ ግጥም “ለ”

ለ. የእርሻ ቃላዊ ግጥም “ሀ”ና የሙገሳ ቃላዊ ግጥም “ለ”

ሐ. የእርሻ ቃላዊ ግጥም “ሀ” የሐዘን ቃላዊ ግጥም “ሀ”

አቀላጥፎ ማንበብ

“አይዳሰሴ ቅርሶች” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

2.2.2 ቃላት

በ2.2.1 ሥር “አይዳሰሴ ቅርሶች” በሚለው ምንባብ መሠረት ከዚህ በታች የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ምሳሌ፦

ሰው የማያውቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣

ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ።

(በግጥሙ የተሠመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺ “ሞት” ማለት ነው።)

ሀ. ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ።

ለ. የምትሰጪበት የምታበዪበት ከሚፈርስ ቤትሽ።

ሐ. አልተጫነሽ እንደሁ አፈሩ ተንዶ።

መ. አንተ አለኸኝ ብዬ ስመካ ስመካ።

ሠ. እንደመፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው።

ረ. ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ፣

ሰ. ያርሳል ያርሳል ያወጣል እዳሪ፣

ሰ. በእጇ ስራ እንጂ በአፏ ሰው አትነካም፣

በ. ዝንብ አይከለክል ርሀብ አይከላ፣

ተ. ማረስ ነው እንጂ የጨባውን ስር፣

ቸ. ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ፣

መጻፍ

1. የሚከተሉትን ግጥሞች ሐሳብ፣ በኹለት ወይም በሦስት ዓረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ።

ሀ. ከተጣጣምንማ እንደሰም ከፈትሉ፣

የትብትቡ መፍቻ ከእጃችን ነው ውሉ።

ለ. ሰንበሌጥ ሲከደን ባንድ እየታሰረ፣

አይደለም ለብቻው ሜዳ እንደበቀለ፣

ነው እንጅ ሣር ከሣር እየተዳበለ።

ሐ. በውኃ ተቦክቶ አሸዋ ስሚንቶ፣

ድንጋይ በድንጋይ ላይ በሥርዓት ተሞልቶ፣

ድልድይ ተሠርቶ ሕንፃ ተገንብቶ፣

ኅብረት ኃይልነቱን ያሳያል አጉልቶ።

2. ከአካባቢያችሁ ሰዎች ጠይቃችሁ የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን ጻፉ።

2.2.3 መናገር

ሀ. “የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች” በሚል ርዕስ ተዘጋጅታችሁ ተራ በተራ ንግግር አድርጉ።

ለ. በሹለት ቡድን ተመዳድባችሁ አንደኛው ቡድን የሚዳሰሱ ቅርሶችን ምንነት በምሳሌ እያስደገፈ ንግግር ያቅርብ፤ ሌላው ቡድን ደግሞ የማይዳሰሱ ቅርሶችን ምንነት በምሳሌ እያስደገፈ ንግግር ያድርግ።

ሰዋስው

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ወደጥገኛ ሐረግ ለውጣችሁ ጻፉ።

ዓረፍተነገር	ጥገኛ ሐረግ
መስጊዶች ኮረብታማ ቦታዎች ላይ ይገነባሉ።	መስጊዶች ኮረብታማ ቦታ ላይ ሲገነቡ መስጊዶች ኮረብታማ ቦታ ላይ እየተገነቡ መስጊዶች ኮረብታማ ቦታ ላይ ሊገነቡ መስጊዶች ኮረብታማ ቦታ ላይ ከተገነቡ

ሀ. በባሕር ዳር ከተማ ዓመታዊ በዓል ይከበራል።

ለ. ቱሪስቶች ጎዜ መስጊድን ይጎበኛሉ።

ሐ. አዛውንቶች ታሪክ ይናገራሉ።

መ. ላልይበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት ለአካባቢው ሰዎች አገልግሎት ይሰጣሉ።

ሠ. አንዳንድ ሰዎች የዉኃ ጉድጓድ ይቆፍራሉ።

2.3.1 አንብቦ መረዳት

ጉብኝት

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በረፍት ጊዚያችሁ የማታውቋቸውን ቦታዎች ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ መቼ? የት ቦታ?

ለ. በአካባቢያችሁ ወይም በትምህርትቤታችሁ "ሀገርህን እወቅ" የሚባል ክበብ አለ? ካለ ዓላማው ምንድን ነው?

ሐ. ከነዚህ ጥያቄዎች አንድምታ (ዳርዳርታ) ተነስታችሁ "ጉብኝት" በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ ምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ጉብኝት

በማንኛውም ሀገር ትምህርትና እውቀት የሚጀመረው አካባቢን፣ ማህበረሰብን፣ ባህልን፣ ሀገርን ጠንቅቆ ከማወቅ ነው። የረፍት ጊዜ ስለሆነ ትምህርቤቶች ተዘግተዋል። ትምህርት ቤታችን የሀገርህን እውቅ ክበብ ባህላዊ ቅርሶችን ለማስጎብኘት እቅድ ይዟል። በዚህ መሠረት በረፍት ጊዜያችን በደብረማርቆስ ከተማ የሚገኘውን አንድ የባህል ማዕከል ለመጎብኘት ተነሳን። ከውቢቷ ባሕር ዳር ከተማ ተነስተን ወደምስራቅ አቅጣጫ ገሰገስን። የምዕራብ ጎጃምን መልክዓ ምድር እያየን ፈጣሪ ሰዎች በልተው እንዲያድሩ ሲል አመቻችቶ የፈጠረው ቀያቴ አፈር፣ ለእርሻ ምቹ መሆኑን እያደነቅን ጉዟችን ቀጠልን። ምዕራብ ጎጃምን አልፈን የተምጫን ድልድይ ተሻገርን ነፋሻ አየሩን እያጣጣምን ረፋድ ላይ ደብረማርቆስ ከተማ ገባን።

ጉብኝት ያደረግንበት የባህል ማዕከል በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስር የተቋቋመው "የባህልና የምርምር ተቋም" ነው። ተቋሙ የተሰየመው በኢትዮጵያ የሥነጽሑፍ ታሪክ ከፍተኛ ክብር በሚሰጣቸው በክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ስም ነው። የጉብኝታችን ዓላማም በማዕከሉ ባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ለማወቅ ነበር። በቅድሚያ ተቋሙ በሥነጽሑፍ አስተዋፅኦዋቸውና በሀገር አስተዳደርና አርበኝነት ተጋድሏቸው የሀገር ባለውለታ በሆኑት በክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ስም መሰየሙን አድንቀናል።

አስጎብኛችን የባህል ማዕከሉን አመሠራረትና የተቋቋመበትን ዓላማ በተመለከተ ባደረጉልን ገለጻ ማዕከሉ ኢትዮጵያ ያላት የታሪክ፣ የሥነጥበብ፣ የእምነት፣ የስልጣኔ፣ የጽሑፍ፣ የሀገር በቀል እውቀት፣ የሥነጽሑፍና ሥነዜማ ቅርስ

እንዲጠና ለማድረግ እንደሚያስችል ተረዳን። በተጨማሪም የህዝቡ ማኅበራዊ አኗኗር በአግባቡ እንዲጠና፣ በሀገር ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ፣ እንዲደነቅና ከዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ በትምህርትነት እንዲሰጥ የማድረግ ዓላማ እንዳለው አስጎብኝው ገልጸውልናል።

በመጨረሻም ተቋሙ ባህላችንን ታሪካችንንና ቅርሶቻችንን ለመጠበቅ፣ ለማወቅና ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ እያደረገ ባለው እንቅስቃሴ ያለንን አድናቆት ገልጸን ጉብኝታችንን አጠናቀናል።

እኛ ወጣቶች በተለይም ወንዶች ፀጉራቸውን የተሠሩ አውሮፓውያንን እያየን፣ ሎቲ በጆሯቸው ላይ ያንጠለጠሉትን፣ በክንዳቸው፣ በደረታቸው ወይም በጡታቸው ንቅሳት ያላቸውን ታዋቂ ሰዎች እየተመለክትን ነው። በእርግጥ የዘመኑ ሉላዊነት /ግሎባላይዜሽን/ ያመጣው ውጤት ነው። ይህም ከጥንት ጀምሮ የአፍሪካዊያን ወይም የኢትዮጵያዊያን የውበት፣ የማንነት ቅርስ ያለን መሆኑን ልናውቅ ይገባል። የፈረንጆችም ዘመናዊ የራፕ ዘፈኖች የሀገራችን ልዩ የፉከራና የሽለላ ዜማዊ ስልት ተፅዕኖ ውጤት መሆናቸውን ማወቅ ይኖርብናል። እነዚህን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ነባር የጥበብ ቅርሶችና የጥበብ ሐውልቶች ልናጠናቸው፣ ልንጠብቃቸውና ልንኮራባቸው ይገባል መልዕክታችን ነው።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ባሕር ዳር ከደብረማርቆስ በየትኛው አቅጣጫ ትገኛለች?

ለ. ምዕራብ ጎጃም ምን ዓይነት ተፈጥሮ አለው?

ሐ. በምንባቡ መሠረት "ተምጫ" ምንድን ነው?

መ. ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ማን ናቸው?

ሠ. በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ሥር የተቋቋመው የባህልና ምርምር ተቋም ዓላማ ምንድን ነው?

ረ. የጉብኝትን ጠቀሜታ አጠር አድርጋችሁ አስረዱ።

ሰ. የጉብኝቱ ሪፖርቱ አቅራቢ የጠበቃችሁትን ዋና ዋና ወይም ዝርዝር ጉዳዮች አቅርቧል/አቅርባለች ብላችሁ ታምናላችሁ? ምን ምን የጎደለ ይመስላችኋል?

አቀላጥፎ ማንበብ

“ጉብኝት” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

2.3.2 ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ባህላዊ ቅርሶችን ለማስጎብኘት እቅድ ተይዟል።

ለ. በደብረማርቆስ ከተማ የሚገኘውን የባህል ማዕከል ጎበኘን።

ሐ. የተጎበኘው የደብረማርቆስ ዩንቨርሲቲ የባህልና ምርምር ተቋም ነው።

መ. ተቋሙ ባህላችንን፣ ታሪካችንና ቅርሳችን ለመጠበቅ ያደረገውን ጥረት አደነቅን።

ሠ. ፀጉር መሠራት፣ ንቅሳት፣ የዘመኑ ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ያመጣው ቢመስልም የአፍሪካውያን ቅርስ ነው።

መጻፍ

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም በዋናና በዝርዝር ስልት አንቀጽ ጻፉ።



ለ. “የሀገርህን እወቅ ክበብ በባሕር ዳር ከተማ የተለያዩ ቦታዎችንና ተቋማትን ጎብኝቷል።” የሚለውን ጥቅል ሐሳብ የያዘ ዓረፍተነገር፣ ዝርዝር ሐሳብ በያዙ ዓረፍተነገሮች በማስፋፋት አንቀጽ ጻፉ።

2.3.3 መናገር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ስለመንግሥት መሥሪያቤቶችና መንግሥታዊ ስላልሆኑ ተቋማት ምንነትና አገልግሎት ንግግር አቅርቡ።

ሰዋስው

ስድስት ዓረፍተነገሮችን በሀላፊ፤ በአሁንና በወደፊት ጊዜ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ሀላፊ ጊዜ	→	ሸመክት ትናንት ወደጎንደር ሄደ።
የአሁን ጊዜ	→	ሸመክት አሁን ወደጎንደር ይሄዳል።
የወደፊት ጊዜ	→	ሸመክት ነገ ወደጎንደር ይሄዳል።

ምዕራፍ 3 ሰብዓዊ እሴቶች

3.1.1 አንብቦ መረዳት

ወይ አለማወቅ!

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች “ወይ አለማወቅ!” በሚል የሚገረሙት ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ወይ አለማወቅ!

አንድ ልጅ ብቻ የነበራት አንዲት እናት ነበረች። ፊቷ በእሳት የተለበለበ ስለነበር የሚያዩዋት ሁሉ ይገረማሉ። አንዳንዶችም ይሸሿታል። በተለይ ልጇ፣ በእናቱ የተጨማደደና የጠቆረ ፊት ስለሚያፍር አብሯት መታየትም ሆነ ወደትምህርት ቤት አብራው እንድትሄድ አይፈልግም ነበር። ለተወሰኑት ጓደኞቹ “እናቴ ሞታለች” እያለ ይዋሻቸው ነበር። እድሜው እየጨመረ፣ በትምህርቱም እየገፋ መጣ። በመጨረሻም ከኮሌጅ ተመርቆ ጥሩ ሥራ ያዘ። ከጥሩ ደረጃ ላይ በመድረሱ በሰዎች ዘንድ ክብር አገኘ። ነገር ግን ጓደኞቹንም ሆነ ሌሎች ወዳጆቹን ወደቤት ማምጣት አይፈልግም ነበር። ሳይጠራቸው በድንገት ወደቤቱ ከመጡበትም እናቱን “ሠራተኛዬ ናት” እያለ ያስተዋውቃቸዋል።

አንድ ቀን እናቱ ልታነጋግረው ጠራችው። እያንጎራጎረ መጣ፤ ከፊት ለፊቱ ተቀመጠች። “ለመሆኑ ለምን እንደዚህ እንደሆንክ ታውቃለህ?” አለችው። እሱም “ስትፈጠሪ እንደዚህ የሆንሽ ይመስለኛል” አላት። “አይደለም!” አለችው። ከዚያም አንድ ፎቶ አወጣችና አሳየችው። እጅግ የተዋበች ለግላጋ ወጣት ናት። “ማን ናት?” ብሎ ሲጠይቅ “ከጀርባው ያለውን ጽሑፍ ተመልከት” ስትል መለሰችለት፤ ፎቶውን ገልብጦ ጀርባውን ሲመለከተው የእናቱ ስም ተዕፏል። እናቱ ከ30 ዓመት በፊት ከትምህርትቤት ጓደኞቿ ጋር የተነሳችው ፎቶ ነበር። “አላምንም!” አላት

ደንግጦ፣ እንዲያረጋግጥ በማለት ሌሎች ፎቶዎችን ጨመረችለት። “ለምን እንዲህ ሆንሽ?” በማለት አጥብቆ ጠየቃት። እናቱም ታሪኳን በዝርዝር ገለፀችለት።

“አንድ ቀን አንተ የአሥር ወር ሕፃን እያለህ እንቅልፍ ወስዶህ አልጋ ላይ ተኝተህ ነበር። እኔ የዳቦ ስንዴ ፀሐይ ላይ ላሰጣ ከቤት ውጪ ነበርኩ። አባትህም እቤት አልነበረም። ስንዴውን አስጥቼ ዘወር ስል ቤታችን በእሳት ተያይዟል። ኡ... ኡ...! እያልኩ ጮህኩ፤ የሰፈራችን ሰዎች በሙሉ ተሰበሰቡ። ነገር ግን እሳቱን ለማጥፋት ከመሯሯጥ በስተቀር አንተን ለማዳን ያሰበ አልነበረም። እኔ ግን በእሳቱ መካከል ቀልቤን ስቼ ገባሁ። አንተን በብርድ ልብስ ሸፍኜ አምላኬን እየተማፀንኩ ይገፍህ ወጣሁ። ይገፍህ መውጣት ብችልም ልብሴ በእሳት በመያያዙ ከፊል አካሌ ተጎድቶ ነበር። አንተ ግን ጪሱ ቢያፍንህም እሳቱ አልነካህም ነበር። የአንተን እሳት እኔ ተቃጠልኩልህ። አየህ ልጄ! ያንተ ቃጠሎ ለእኔ ሆነ፤ የእኔ ጤናና ውበት ደግሞ ለአንተ ሆነ” አለችው።

ልጁ ራሱን ይዞ በመጮህ ከእናቱ እግር ሥር ወድቆ ይቅርታ እንድታደርግለት ተማፀናት። እናቱም ይቅርታውን ተቀብላ ከወደቀበት አነሳችው። ውበት ነገም በተለያዩ የሕይወት አጋጣሚዎች ሊጠፋ እንደሚችል አስረዳችው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልጇ፣ ወላጆች ቢከሱ፣ ቢጎሳቆሉ፣ አካላቸው ቢጎድል ልጅን ለማሳደግና ቤተሰብን ለመምራት እንደሆነ ተረዳ። ወላጆችን ስለማክበር ወጣቶችን የማስተማር ስራ የዕለት ከዕለት ተግባሩ አደረገ። በበጎ ሥራውም በርካታ ሰዎች ዘንድ ምስጋናን አተረፈ።

(አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል። (2007 ዓ.ም)። ገጽ 34 ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ቀበጡ ልጅ ጓደኞቹን ወደቤት ማምጣት ያልፈለገው ለምን ይመስላችኋል? በአስተሳሰቡ ላይ አስተያየት ስጡ፤

ለ. እናቱ በእሳት ስትቃጠል የቀበጡ ልጅ ዕድሜ ስንት ነበር?

ሐ. እናቲቱ ልጇን ለማነጋገር የጠራችው ምን አነሳስቷት ነው?

መ. ቀበጡን ልጅ ብታገኙት ምን ትሉት ነበር? ለምን?

ሠ. ቀበጡ ልጅ ለማመን የተቸገረው ለምን ይመስላችኋል?

ረ. ከምንባቡ ታሪክ ምን ተማራችሁ? ለምን?

ሰ. “የአንተን እሳት እኔ ተቃጠልኩልህ” የሚለውን ዓረፍተነገር ሐሳብ አብራሩ።

ሸ. “ፍቅር ቁልቁለት ነው” የሚለውን አነጋገር አብራሩ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ወይ አለማወቅ!” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

3.1.2 ቃላት

በ“ሀ” ረድፍ ለሚገኙት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. አፍጥጦ	ሀ. ቀለጠ
2. ይሸሻል	ለ. የተሸበሸበ
3. ቀበጥ	ሐ. እየዘፈነ
4. ለግላጋ	መ. ትኩር ብሎ
5. የተጨማደደ	ሠ. አወቀ
6. እያንጎራጎረ	ረ. ቀምበጥ
7. ላሰጣ	ሰ. ይርቃል
8. ተረዳ	ሸ. ፀሐይ ላስመታ
	ቀ. ይቀርባል

መጻፍ

የታሪኩን ባለቤት፣ “ቀበጡን ልጅ” የሚገመግም ባለአራት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ፍንጭ

- በመጀመሪያው አንቀጽ አጠቃላይ ስለልጆችና ወላጆች ግንኙነት
- በሹለተኛው አንቀጽ ከወላጆቻቸው መለየት ስለማይወዱ ልጆች
- በሦስተኛው አንቀጽ ከወላጆቻቸው ጋር መታየት ስለማይፈልጉ ልጆች
- በአራተኛው አንቀጽ በሹለቱም ላይ ያላችሁን ግምገማ መፃፍ ትችላላችሁ።

3.1.3 ማዳመጥ

ዕድር

ቅድመማዳመጥ

በአካባቢያችሁ የምታውቋቸው ዕድሮች ስለሚሰሯቸው ሥራዎች ተወያዩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ዕድር ሁሉን አሳታፊ ተቋም ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. ከዕድርተኛ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከል ቢያንስ ሦስቱን ጥቀሱ።

ሐ. የዕድር አባላት በሕይወት እያሉ በምን በምን ይረዳዳሉ?

መ. ዕድር ከሌሎች ማኅበራዊ ተቋማት በምን ይለያል?

ሠ. ከዕድሮች መስፈርት ውስጥ የማይካተቱ ምን ምን ናቸው?

ረ. ዕድር ባይኖር በማህበረሰቡ ማኅበራዊ ግንኙነት ምን ክፍተት ይፈጠራል?

ሰ. ወላጆቻችሁን በመጠየቅ በምትኖሩበት አካባቢ የሚገኘው ዕድር በህገ ደንቡ ያላካተታቸው ነጥቦች ናቸው የምትሏቸውን በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ አስፍሩ።

ሰዋስው

1. የሚከተሉትን ቃላት በብዙ ቁጥር ቅርፃቸው ጻፉ።

   ምሳሌ፡-



ሀ. ሴት	መ. ነገር	ሰ. ሰበርክ
ለ. በሬ	ሠ. መጣሁ	ሸ. ክፋ
ሐ. ጥቁር	ረ. ፈላጊ	ቀ. አንተ

2. የሚከተሉትን ቃላት በነጠላ ቁጥር ቅርፃቸው ጻፉ።

ሀ. ነገረኞች	መ. ጥበቦች	ሰ. ነጮች
ለ. ምሁራን	ሠ. መሰከራችሁ	ሸ. እነርሱ
ሐ. መስፈርቶች	ረ. መከርን	ቀ. እኛ

3.2.1 አንብቦ መረዳት

“ፍትህ ከሰው አልፎ...”

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ለ. “ፍትህ ከሰው አልፎ...” ከሚለው ርዕስ የሚገኘው ነጠብጣብ (...) ምን ይጠቁማል?

“ፍትህ ከሰው አልፎ...”

ህዝባቸው የአስተዳደር በደል እንዲደርስበት የማይፈልጉ ንጉሥ ነበሩ። ንጉሡ ማንም ሰው በደል ሲደርስበት በቀጥታ ወደቤተመንግስታቸው በመምጣት አቤቱታውን እንዲያሰማ ፈቀዱ። በዚህም መሠረት ማንኛውም በደል ደረሰብኝ የሚል ወይም አቤት ባይ ሰው ወደቤተመንግስት እየመጣ ደወል ይደውላል። ንጉሡም የደወል ድምጽ ሲሰሙ “አስገቡ!” ይሉና አቤት ባዩን ይሰማሉ፤ ፍርድም ይሰጣሉ።

በዚህ ዓይነት ብዙ ሕዝብ አቤቱታውን በቀጥታ ለንጉሡ ሲያሰማ ኖረ። በርግጥ የተፈረደለት መደሰቱ፣ የተፈረደበት ማዘኑ የማይቀር ክስተት ነበር። ያም ሆኖ ህዝቡ ሁሉ በደሉን በቀጥታ ለንጉሡ የሚያሰማበት፣ ብሶቱን የሚተነፍስበት መድረክ ስላገኘ ደስ ብሎት ይኖር ነበር። ንጉሡ ቅንና እውነተኛ ፍርድን እንዲፈርዱም በጸሎት ያግዛቸው ነበር ይባላል። ንጉሡ ትክክለኛ ፍርድ በመስጠታቸውና ፍትህን በማስፈናቸው የተነሳ ደወል ደዋዩ ቀነሰ፤ እያደረም ጠፋ።

ይሁንና ብዙ ቀናት ካለፈ በኋላ ድንገት አንድ ቀን የደወል ድምጽ ተሰማ። ቤተመንግስቱ አካባቢ ግርምታ ተፈጠረ። እንደተለመደው ንጉሡ አጋፍሪውን አስጠርተው ደዋዩን እንዲያሰገባ ትዕዛዝ ሰጡ።

አጋፍሪው ወደደወሉ ቦታ ሄዶ የደወለውን ሰው መፈለግ ጀመረ። ዙሪያውን ቢመለከት ምንም ሰው አጣ። ሆኖም አንድ አህያ ከደወሉ አጠገብ ሲግጥ አየ። በዚህም ደወሉን የደወለው አህያው መሆኑን አወቀ።

ለካስ አህያው ደወሉ የተሰቀለበትን ባላ ሲታከክ ኖሯል ደወሉ የጮኸው! አጋፋሪው ወደንጉሡ ተመልሶ በመሄድ “ጃንሆይ! ደወሉን የደወለው ሰው አይደለም፤ አህያ ነው” ብሎ ይነግራቸዋል። እሳቸውም “አስገቡት፤ እሱም ተበድሎ ይህናል” አሉ።

ከዚያም ያ አህያ እየተጎተተ ይገባና ከንጉሱ ፊት እንዲቆም ይደረጋል። ሲታይ ከጭነት ብዛት የተነሳ ጀርባው በጣም ቆስሏል። በጭነትና በመንገድ የተጎዳ የአንድ የጨው ነጋዴ አህያ ኖሯል። ንጉሡም ባዩት ሁኔታ በጣም ያዝናሉ “በል ከበቅሎዎቼ ጋር አብሮ ይታሰርና ይቀለብ” ብለው ያዝዛሉ። ከዚያም ስራዬ ብለው ራሳቸው ቆመው ጥሬ እያበሉና ጨው እያላሱ ከጉዳት እንዲያገግም ያደርጉታል።

በመጨረሻም የዚህ ዓይነት በደል የሚደርስባቸውን የጭነት ከብቶች ለመታደግ የሚከተለውን አዋጅ አሥነገሩ። “አዋጅ! አዋጅ! ያልሰማህ ስማ! የሰማህ አሰማ!... ማንኛውንም ፈረስ፣ በቅሎና አህያ የደበደበ፣ ያላግባብ የጫነና ቀለብ አሳንሶ ያጎሳቆለ ነጋዴም ሆነ ሌላ ሰው ከባድ ቅጣት ይቀጣል፤” ተባለ። በዚያ አህያ የተነሳ በወጣው አዋጅ፣ ሌሎች የጭነት ከብቶችም ያለአገባብ ከመበደል ነፃ ወጡ። ፍትህም ከሰዎች አልፎ በእንስሳት መንደር ሠፈነ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ንጉሡ በደል የደረሰበት ሰው ደወል እንዲደውል ያደረጉበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?

ለ. የደዋዮቹ ቁጥር መቀነስ ምንን ያመለክታል?

ሐ. ቤተመንግሥት አካባቢ ግርምት የፈጠረውን ክስተትና ምክንያቱን አብራሩ።

መ. የደወሉን ባላ የታከከበት ቅጽበት ለአህያው ወርቃማ ጊዜ ናት፤ ለምን?

ሠ. ንጉሡ "አስገቡት፤ እርሱም ተበድሎ ይሆናል" ማለታቸው አህያው ገብቶ ይናገራል ብለው ነው?

ረ. አህያው የተሟላ ፍትህ አግኝቷል ብላችሁ ታምናላችሁ? ንጉሡ አህያውን ከመንከባከብ አህያው ለደረሰበት በደል ተመጣጣኝና የተሟላ ፍርድ ሰጥተዋል ማለት ይቻላል?

ሰ. እውነተኛ ፍርድም ሰውን ያሳዝናል፤ ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ለምን?

አቀላጥፎ ማንበብ

"ፍትህ ከሰው አልፎ..." በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

3.2.2 ቃላት

1. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. በደል	ረ. ክስተት	ነ. አዋጅ
ለ. ቤተመንግሥት	ሰ. ቅን	ኘ. ቅጣት
ሐ. አቤቱታ	ሸ. ፀሎት	አ. ፍትህ
መ. አቤት ባይ	ቀ. ታከከ	
ሠ. ፍርድ	ተ. የጭነት ከብት	

2. በ“ሀ”ና በ“ለ” ሥር ያሉ ተዛማጅ ቃላትን አዛምዱና ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡-

የሚዛመዱ ቃላት፡-		የተዛመዱ ቃላት	ዐውዳዊ ፍቺ
“ሀ”	“ለ”		
1. ጥራዝ	ሀ. ነጋሪ	1. ጥራዝ ነጠቅ	1. ግልብ ዕውቀት ያለው
2. ወሬ	ለ. አዋቂ	2. ወሬ ነጋሪ	2. አዲስ ጉዳይን የሚያደርስ
3. ነገር	ሐ.ነጠቅ	3. ነገር አዋቂ	3. ተሟጋች

“ሀ”	“ለ”
1. አስተዳደራዊ	ሀ. ቅጣት
2. አቤቱታ	ለ. ነጋሪ
3. ደወል	ሐ. አገገመ
4. አቤት	መ. ወጣ
5. ፍርድ	ሠ. ላሰ
6. ጀርባውን	ረ. አሰማ
7. ጨው	ሸ. ጋጠ
8. አዋጅ	ቀ. በደል
9. ያልሰማህ	በ. አቅራቢ
10. የሰማህ	ተ. ደዋይ
11. ከባድ	ቸ. ሰጠ
12. ነፃ	ነ. ተላጠ
	ኘ. ባይ
	አ. ሰማ

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም “ጀግናው ነፃ አውጭ አህያ” በሚል ርዕስ ባለአራት አንቀጽ ተራኪ ድርሰት ጻፉ።



3.2.3 መናገር

ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ የንግግር ጽሑፍ አዘጋጁና በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ሀ. አሰገራሚዋ ወፍ

ለ. የማልረሳት ቀን

ሐ. ባለጋሪውና በቅሎው

መ. የትምህርትቤታችን ጥበቃ ስኬት

ሰዋስው

ማስታወሻ

ጊዜ የሀላፊ፣ የአሁን፣ የትንቢት ተብሎ በሦስት ሊከፈል ይችላል። ንግግር የሚደረግበት ጊዜ የአሁን፣ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ በፊት ያለው ሀላፊ፣ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ በኋላ ያለው የትንቢት ጊዜ ይባላል።



ቋንቋዎች ጊዜን የግድ በሦስት ላይከፍሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ አማርኛ የአሁንና የትንቢት ጊዜን እንደአንድ አድርጎ ኢሀላፊ ጊዜ ብሎ ነው የሚከፍለው። ስለሆነም አማርኛ ቋንቋ ጊዜን የሚከፈለው ሀላፊና ኢሀላፊ ብሎ ነው።

ምሳሌ፦ የሀላፊ ጊዜ	የኢሀላፊ ጊዜ
ትናንት እንጨት ሰበረ።	ዛሬ/ነገ እንጨት ይሰብራል።

1. በ“ሀ”ና በ“ለ” ረድፍ የቀረቡት ቃላት የሚለያዩባቸውን ቅርጾችና የቅርጾቹን ፍቺ ተናገሩ።





2. በተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ ጊዜ አመልካች ቅርጾችን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ሙሀመድ መጽሐፍ ይገዛል።
መ. መልካሙ ነገ ይመጣል።
ለ. መሠረት ሥራ ትሠራለች።
ሠ. ፈንታነሽ ታስተምራለች።
ሐ. ሃሊማ መጽሐፍ ትጽፋለች።
ረ. ዘይነባ ምሳ ትበላለች።

3.3.1 አንብቦ መረዳት

የሌሊትወፍ የመደበቅ ምስጢር

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ስለሌሊትወፍ የምታውቁትን ተናገሩ፤ ለምሳሌ፦ ምን ዓይነት ተፈጥሮ ነው ያላት? እንዴት ነው የምትኖረው?

ለ. "የሌሊትወፍ የመደበቅ ምስጢር" ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምንባቡን ይዘት ገምቱ።

የሌሊትወፍ የመደበቅ ምስጢር

ከዕለታት አንድ ቀን የሰማይ በራሪ ወፎችና የምድር አጥቢ እንስሳት ጦርነት ገጠሙ። አራት ቀን ሙሉ ተዋጉ። በዚህ ጦርነት የሌሊትወፍ ሳትሳተፍ ዳር ቆማ ስትመለከት ቆየች።

በመሀል ላይ የሌሊትወፍ በጦርነቱ አጥቢያ እንስሳት ድል ለማድረግ የተቃረቡ ሲመስላት፣ ወደእነሱ ትሄድና "እኔኮ የእናንተ ዘር ነኝ፤ ክንፌና በሰማይ ከመብረሬ በቀር ከወፎች ጋር የሚያዛምደኝ ምን ነገር አለ?" ትላቸዋለች። ከዚያም አልፋ "ወፎች ክፋዎች ስለሆኑ እንዲህ አድርጋችሁ፣ እንዲህ ዓይነት ዘዴ ተጠቅማችሁ፣ አንድ ሳታስቀሩ ፍጇቻው" እያለች ተንኮል ትመክራቸዋለች።

ሌላ ጊዜ ደግሞ በጦርነቱ የሰማይ ወፎች በርትተው የሚያሸንፉ ሲመስላት ወደእነሱ ትሄድና "እኔኮ የእናንተ ዘር ነኝ፤ እስኪ ከአጥቢ እንስሳት ክንፍ ያለውና እንደእኔ በሰማይ የሚበር ማን አለ? ጡቱ ነው እንጂ ከእነሱ ጋር እኮ የሚያዛምደኝ ነገር የለም። እነሱ እያሉ መሬት ላይ አርፈን በሰላም ጥራጥሬ መልቀም አንችልም። መጥፋት አለባቸው" እያለች ጦርነቱን ታባብሳለች።

የሌሊትወፍ ወዲያና ወዲህ እያለች ነገር ስታቀጣጥል ዶሮ በተቃራኒው አንዴ ወደወፎች ሌላ ጊዜ ወደአጥቢ እንስሳት እየሄደች ጠቡን ለማብረድ ትጥር ነበር። አንዴ ወደአጥቢ እንስሳቱ ሄዳ "በሰማይ ባልበርም በትንሹም ቢሆን የእነሱ ዝርያ

ስላለብኝ ጠባያቸውን አውቃለሁ፤ ከአንዳንዶቹ በቀር አብዛኞቹ ከእኛ ጋር በሰላም መኖር የሚሹ ናቸው፤ ጥሬያቸውን በሰላም ለቅመው ከመሄድ ውጭ እኛን አይተናኮሉም፤ ስለዚህ ጦርነቱ ለእኛ የሚበጀው ነገር ስለሌለ ቢቆም ይሻላል" እያለች ትመክራለች። ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደወፎቹ ሄዳ "ዘመዶቼ ሆይ ከአጥቢ እንስሳት ጋር ጦርነት መግጠማችሁ አስፈላጊ አይደለም። አጥቢ እንስሳትን አብሪያቸው ስለምኖር አሳምሬ አውቃቸዋለሁ። አንዳንድ የሚያጠቋቸውን የወፍ ዓይነቶች ከመፍራት በቀር ሌሎቻችሁን በመጥፎ አስበዋችሁ አያውቁም። ከእናንተ ጋር መዋጋትም አይፈልጉም። ስለዚህ ጦርነቱ ቢቆም ነው የሚሻለው" እያለች መከረቻቸው።

ከቀናት በኋላ የዶሮ ምክር ተቀባይነት አገኘና በወፎችና በአጥቢ እንስሳት መካከል እርቅ ወርዶ ጦርነቱ ቆመ። ለዚህም ደስታ፣ ዅሉቱ ወገኖች በጋራ ትልቅ ድግስ አዘጋጁ። በድግሱ ላይ ዶሮ ዅሉቱን ወገኖች በመምከር ሰላም በማውረዷ ምስጋና ጎረፈላት፤ ሽልማትም ተሰጣት። በዚህ መሀል የሌሊትወፍ ከድግሱ ልትበላ ድንገት ብቅ አለች። በዚህ ጊዜ ወፎች "ወደእኛ እንዳትጠጊ!" ብለው አባረሯት። ወደአጥቢዎች ስትሄድም "ዞር በይ ከዚህ!" ብለው አባረሯት። በዚህ የተነሳም የሌሊትወፍ በሥራዋ ስላፈረች ወፎችም አጥቢዎችም እንዳያዩዋት ቀን ቀን እየተደበቀች ማታ ማታ ብቻ ምግቧን መፈለግ ጀመረች።

(ውቢት ጎርፉ፤ "መጽሐፍ ለሁሉም"፤ ለንባብ እንዲመች ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሌሊትወፍን አኗኗር ከጽሑፉ ታሪክ ጋር እያገናዘባችሁ አስረዱ።

ለ. የሌሊትወፍን ባሕርይ ገምግሙ።

ሐ. የሌሊትወፍ ባሕርይ ምን መልዕክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?

መ. የሌሊትወፍ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ሰዎች አሉ? ካሉ በማህበረሰብ ሕይወትና በሀገር ደህንነት ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅእኖ አስረዱ።።

ሠ. የዶሮ ባሕርይን ከሰው ባሕርይ ጋር እያገናዘባችሁ አብራሩ።

ረ. የሌሊትወፍና ዶሮ ስለባሕርያቸው ለመወያየት ቢገናኙ ምን የሚባባሉ ይመስላችኋል?

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሌሊትወፍ የመደበቅ ምስጢር” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

3.3.2 ቃላት

1. ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

የሰማይ	እርቅ	አጥቢ	ቢቆም	ነገር
ዘር	ጥራጥሬ	ታቀጣጥል	ምስጋና	
በሰላም	የሚበጀው	ለማብረድ	ጠባችን	

ሀ. በጦርነቱ _____ ወፎች በርትተው ነበር።

ለ. እኔ እኮ የእናንተ _____ ነኝ።

ሐ. በጦርነቱ _____ እንስሳት ድል አደረጉ።

መ. ወፎች በሰላም _____ መልቀም ይፈልጋሉ።

ሠ. አንቺ ነሽ _____ እያመላለሽ _____ ያባባስሽው።

ረ. ዶሮ ጠቡን _____ ትጥር ነበር።

ሰ. የሌሊትወፍ ወዲያና ወዲህ እያለች ነገር _____ ነበር።

ሸ. ግራ ቀኙም ጠባቸውን ትተው _____ መኖር ፈለጉ።

ቀ. ጦርነቱ ለእኛ _____ ነገር ስለሌለ _____ ይሻላል።

በ. በእንስሳት መካከል _____ ወረደ።

ተ. ዶሮ ሰላም በማውረድ _____ ጎረፈላት።

2. በ“ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ“ለ” ረድፍ ተቃራኒ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ጦርነት	ሀ. ምሽት
2. ዳር	ለ. ምድር
3. ድል	ሐ. ጠብ
4. ሰማይ	መ. ቀጠለ
5. መጥፋት	ሠ. ወቀሰ
6. ማብረድ	ረ. ማባባስ
7. ቆመ	ሰ. አጣ
8. ፈራ	ሸ. ተመሳሳይ
9. እርቅ	ቀ. ሰላም
10. አገኘ	በ. ደፈረ
10. ምስጋና	ተ. መልማት
	ቸ. ሽንፈት
	ነ. መሀል
	ቸ. ቀን

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም “የሌሊትወፍና ዶሮ” በሚል ርዕስ በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።



3.3.3 መናገር

“አርበኞች የሚኖሩት ለሀገርና ለሕዝብ ነው።” በሚል ርዕስ ለጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

ሰዋስው

1. ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ እንደገና ጻፏቸው።

   ሀ. አስቴርና ካሣ በመኪና መጣች።

   ለ. ፊለቀ ከአበበ ጋር ነገ በመኪና ይመጣሉ።

   ሐ. የአበበ መጻሕፍት በጣም ቆንጆ ነው።

   መ. መስረቅ እንጅ መሥራት አያሥነውሩም።

   ሠ. ትናንት የመጣችው አስቴር፣ ካሳች አሊማ ናቸው።

2. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶችን አስተካክላችሁ ጻፉ።

   ሀ. ትናንት ያቋረጥናት ወንዝ በጣም ሞልቶ ነበር።

   ለ. ሰናይት ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ገበያ ትሄዳለች።

   ሐ. ለፍቶ ያጠራቀመው ገንዘብ ሌባ ወሰደበት።

   መ. ከዛፍ ላይ ቢወድቅም እግሩ ተሰበረ።

ምዕራፍ 4

አጭር ልቦለድ

4.1.1 አንብቦ መረዳት

ማሩ ፎርሳ (ክፍል አንድ)

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. ፋብሪካ
መ. ሞተር
ሰ. ጉልት
ለ. ታታሪ
ሠ. ጣጣ
ሸ. ዘንጋዳ
ሐ. ጉልበታም
ረ. ጭብጥ

ማሩ ፎርሳ (ክፍል አንድ)



ማሩ ፎርሳ ማን ነው? ማሩ ፎርሳን የማያውቀው ይኖር ይሆን? ማሩ ማለት ይሄ ማካሮኒ ፋብሪካ ውስጥ የሚሠራው እኮ ነው! ይኼ እንኳ ፋብሪካው ውስጥ እንደሱ ታታሪና ጉልበታም የለም የሚባለው! ጠንፌ የምትባል እንጀራ ሻጭ ሚስት ያለችው? አሁን ማሩ ፎርሳን አወቃችሁት?

ማሩ ፎርሳ ሲሏችሁ “ፎርሳ” የአባቱ ስም እንዳይመስላችሁ። የማካሮኒ ፋብሪካ ሥራ አታውቁም እንዴ? ስንዴ በጭነት መኪና ይመጣል። ከመኪና ወደመጋዘን ይጋዛል፤ ከመጋዘን ወደማበጠሪያው የወንፊት ሞተርቤት ይወስዳል። ይታጠባል፤ በሞተር ይደርቃል። ከስንት ጣጣ በኋላ ይፈጫል። እናላችሁ ይሄ ሁሉ ሲሆን ስንዴው የሚጓጓዘው በሰው ትክሻ ነው። ስንዴው በመኪና ሲመጣ ካቦው (የወፍጮ ክፍሉ ሠራተኞች ሀላፊ) ሠራተኞችን ይጠራል። ስንዴ እንዲያወርዱ “አንድ ኹለት ፎርሳ...” ከመኪናው ላይ ኩንታሉን እየተሸከሙ ወደመጋዘን መሮጥ ነው።

ኩንታሉን ለማውረድ በመጀመሪያ መሸከሚያ ፎጣ የሚያነሳው ደግሞ ማሩ ፎርሳ ነው። በስራው ማሩን የሚያህል የለም። ኩንታል ተሸክሞ ሲበር ጭብጥ ላባ የያዘም አይመስልም። ሁልጊዜ በጨኸት "አንድ፣ ኹለት ፎርሳ... ጎበዝ!" ማለት ይወዳል። ለዚህ ነው ማሩ ፎርሳ ተብሎ የቀረው እንጅ ፎርሳ የአባቱ ስም ሆኖ አይደለም።

የማሩ ሚስት ጠንፈ ነው የምትባለው። እንጀራ ለመግዛት ጉልት የሄደ ሁሉ ጠንፈን ያውቃታል። የፋብሪካው ሠራተኞች ማታ ከሥራ ሲመለሱ እግረመንገዳቸውን እንጀራ ይገዛሉ። የጠንፈ እንጀራ ወፍራም ስለሆነ አብዛኞቹ የሚገዙት ከእሷ ነው። አንዱ መጥቶ "እንጀራው የጤፍ ነው ወይስ ድብልቅ? ብሎ ሲጠይቅ ሻጮቹ "ኧረ ንፁህ ጤፍ ነው" ብለው ይዋሻሉ። ጠንፈን ግን አብዛኞቹ ደንበኞች እንዲያ ብለው ጠይቀዋት አያውቁም። ብዙዎቹ ስለሚያውቋት ዝም ብለው ነው የሚገዟት። አንዳንዶች "ጤፍ ነው?" ብለው ሲጠይቋት አትዋሻቸውም "አይ ትንሽ ዘንጋዳ አለበት" ትላቸዋለች። ከማሩ ፎርሳ ጋር የተዋወቁትም በእንጀራ ደንበኝነቱ ነው። ከደንበኝነት ወደባልና ሚስትነት ተሸጋገሩ።

የተጋቡት የዛሬ ኹለት ዓመት ገደማ ነው። ጠንፈ አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለታለች። ልጇ ግን ጤና የለውም። ጤና አጥቶ እሷንም ጤና ነሳት እቱ! የእንጀራ ንግዱም አላዋጣት አለ። የጤፍ ዋጋ ሰማይ ነክቷል፤ ማገዶም አይገኝም። በዚያ ላይ የልጇ ጤና ማጣት! ያም ሆኖ ትዳራቸው በፍቅር የተሞላ ነው። ማሩ እንደአንዳንድ ባሎች አይማታም፤ አይሰክርም፤ ከጠንፈ ምንም አይደብቅም። እሷም ቢሆን በጣም ትወደዋለች፤ ታከብረዋለች።

"ጠንፈ! ዛሬ ደመወዝ ተቀብዬ ከጓደኞቼ ጋር ጠላ ጠጣሁ" ሲላት ፈገግ ብላ ደግ አደረግክ ከማለት ውጭ ምንም አትለው። "ጠንፈ! ዛሬ ደመወዝ ተቀበልኩና ከአንድ ልኳንዳ ቤት ገብቼ ትንሽ ሥጋ ገዝቼ መጣሁ፤ አጠፋሁ እንዴ?" ይላታል። "ምንም አላጠፋህ ማሬ፤ ጥሩ አድርገሀል" ትለዋለች። ከዚያ ያችን ስጋ ጥሩ አድርጋ ትሠራና በፍቅር ራታቸውን ይበላሉ። ታዲያ ምን ዋጋ አለው ልጃቸው ጤና አጣ። ይሄን ኹለት ቀን ደግሞ እንደአዲስ ያተኩስ ይሏል ፤ማቃተትም ጀምሯል።

ሊጠይቅ የመጣው ጎረቤት ሁሉ "ኧረ ሐኪምቤት ውሰጂው" ይላታል። "እሺ" ትላለች፤ በሆዷ "ሐኪምቤት መውሰድ ጠፍቶኝ ነው! ብር አጥቼ እንጅ" ትላለች። ጠንፈ ልጇ እንደአዲስ እንዳመመው፣ ሐኪምቤት መውሰጃ ብርም እንደሌላት ለማሩ አልነገረችውም። ምን ብላ ትንገረው? ከየት ያመጣል? እሷ እንጀራ መሸጥ ካቆመች ወዲህ ሁሉንም የቤት ወጪ የሚሸፍነው እሱ ነው። ታዲያ ምን ብላ ትንገረው? "ልጁ ጠናበት" ብላ ነው? የሰው አፍ ደግሞ አይጣል ነው። "ኧረ

ባካችሁ ሐኪምቤት ውሰዱት” ይላል። አስር ብር ያበድር ያለ ይመስል። “በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ ጨው ላይገዙ ማለት’ኮ ይኼ ነው።” እማማ ዳሳሽ ናቸው። ጠንፈ የሚያበድረን ካገኘን ትንሽ ብር እንፈልግና ጤናጣቢያ እንውሰደው። ካርድ ማውጫው ኹለት ብር ብቻ ነው። የሚሰጡት መድኃኒት ውድ አይደለም” በማለት ችግሯን ለመረዳት የሞከሩት።

ማታ ላይ ማሩ መጣ። እንደመጣ “ማሩ ትንሽ ብር የሚያበድርህ ታገኝ ይሆን? ልጁን አሞታል” አለችው። “ትንሽ ብር ነው ያልሽኝ? ... እኔ ... አሁን...ማለቴ እስቲ ነገ መስሪያ ቤት ካገኘሁ እበደራለሁ፤ በጣም አመመው እንዴ?” አላት ያው የልጁን ማቃሰት ሰምቶ መጠርጠሩ ባይቀርም። ህፃኑ ማቃሰቱን ቀጥሏል፤ ይባስ ብሎ ማልቀስ እያቃተው ሄደ። ጠንፈ ለባሏ የሚበላውን ሰጠችውና ልጇን አቅፋ ቁጭ አለች። ማሩ “እንብላ እንጅ ጠንፈ!” ቢላትም “እኔ ስበላ ነው የዋልኩት። የሴት ነገር ስቀምስም ስጎርስም ጠገብኩ” አለች። ማሩ የቀረበለትን የእንጀራ ፍርፋሪ በደብዛዛው የአምፖል ብርሃን አስተዋለው። ትናንት ከፊቱ የተነሳው የሻገተ እንጀራ ነው። ጠንፈ ዋሽታለች፤ ጠንፈ ምንም አልቀመሰችም፤ ጠንፈ ጦሟን ልታድር ነው ለሱ ብላ። ጠንፈ ልጇን ታቅፋ በዓይኗ እንቅልፍ ሳይዞር ነጋላት። ማሩም ብር ለመበደር ወደፋብሪካ ሄደ።

ጎህ መጽሔት። (1968 ዓ.ም)። ቱሉ ፎራሳ፣ ደራሲው አይታወቅም

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ፋብሪካ ውስጥ ስንዴ ከመፈጨቱ በፊት የሚያልፍባቸውን ሂደቶች ዘርዝሩ።

ለ. የኩንታል መሸከሚያ ፎጣ መጀመሪያ ለማሩ ፎርሳ የሚሰጠው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የማሩ ፎርሳና የጠንፈ ጋብቻ “ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳል” ዓይነት ነው፤ ለምን?

መ. የማሩ ፎርሳ ሕይወት የብዝበዛን አስከፊነት ያሳያል፤ እንዴት?

ሠ. “በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ ጨው ላይገዙ” የሚለው ብሂል ከየትኛው አንቀጽ ሐሳብ ጋር ይስማማል?

ረ. አስከፊ የድህነት ኑሮ የሚኖሩ የአካባቢያችሁን ሰዎች ሕይወት ለማሻሻል ምን ማድረግ የምትችሉ ይመስላችኋል?

አቀላጥፎ ማንበብ

“ማሩ ፎርሳ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

4.1.2 ቃላት

ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት “ማሩ ፎርሳ” በሚለው ምንባብ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ስንዴ ከመጋዘን ወደየወንፊት ሞተር ቤት ይወሰዳል።

ለ. ስንዴው የሚጓጓዘው በሰው ትከሻ ነው።

ሐ. “አንድ ኹለት ፎርሳ....” ስለሚል ነው የአባቱ ስም ፎርሳ ተብሎ የቀረው።

መ. ሠራተኞች ከሥራ ሲመለሱ እግርመንገዳቸውን እንጀራ ይገዛሉ።

ሠ. ማሩ ፎርሳና ጠንፌ የተዋወቁት በእንጀራ ደንበኝነቱ ነው።

ረ. ልጇ ጤና አጥቶ እርሷንም ጤና ነሳት።

ሰ. የጤፍ ዋጋ ሰማይ ነክቷል።

ሸ. ልጇን ሀኪም ቤት መውሰጃ ብርም የላትም።

መጻፍ

አንድ አጭር ልቦለድ መርጣችሁ አንብቡ። ከአነበባችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ገፀባሕርያትን (ባለታሪኮችን) ዘርዝራችሁ በታሪኩ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ጻፉ።

4.1.3 ማዳመጥ

ሽልንጌን

ቅድመማዳመጥ

“ሽልንጌን” በሚል ርዕስ የሚቀርበው ምንባብ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ከርዕሱ ተነስታችሁ ገምቱ።



ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “ፓርኪንግ” የምትሠራው ልጅ እየበረረ የሚሄደውን መኪና የተከተለችው ለምንድን ነው?

ለ. መኪናውን እየተከተለች በጩኸት ስትናገር የነበረው ምን እያለች ይሆን?

ሐ. ለልጅቷ መጋጨት አንደኛ ደረጃ ተጠያቂ ማነው?

መ. በኹለተኛ ደረጃ ተጠያቂውስ ማን ነው?

ሠ. ልጅቷ ከተገጨችበት ክስተት ጋር እያገናኛችሁ የድህነትን አስከፊነት በአጭሩ ግለጹ።

ሰዋስው

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. አይደለም ወርቅ ብልጭልጭ ሁሉ።

ለ. በፍጥነት ሮጠ ትንሹ ጥጃ ወደእናቱ።

ሐ. በመኪና ጎበኟ ተማሪ ነገ ትሄዳለች ወደጎንደር።

መ. ጠላቱን ሊፋለም ጀግናው ወታደር ወደጦር ግንባር ተመመ።

ሠ. ትልልቅ ሰዎችን ይላሉ አንዳንድ ጊዜ ትንንሽ ስዎች ትልቅ ማሰብ ግን ሊጎዱ ይችላሉ ፈጽሞ አይችሉም።

4.2.1 አንብቦ መረዳት — “ማሩ ፎርሳ” (ክፍል ኹለት)

ቅድመንባብ

ከ“ማሩ ፎርሳ” ክፍል አንድ አጨራረስ ተነስታችሁ የ“ማሩ ፎርሳ” ክፍል ኹለት ታሪክ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ማሩ ፎርሳ (ክፍል ኹለት)

ማሩ ፋብሪካው ውስጥ እንደገባ በሥራ የሚጣደፉትን ጓደኞቹን እንደእንግዳ ቆሞ አስተዋላቸው። ፀጉራቸው፣ ፊታቸው፣ ቱታቸው ዱቄት ለብሷል፤ ላባቸው በግንባራቸውና በጀርባቸው ይንቆረቆራል፤ ጫንቃቸው ጎብጧል፤ ትንፋሻቸውም ቁርጥ ቁርጥ ይላል። ያም ሆኖ የፋብሪካው ባለቤት የሆኑት አቶ ካሌብ ሁሌ

አስተያየት ሲሰጡ፣ “አበሻ ሥራ አይወድም፤ ሰነፍ ነው፤ ለዚህ ነው እንደእኔ ሀብታም የማይሆነው” ይላሉ። ማሩ ይሄን ሲያስብና ገብጋባነታቸው ትዝ ሲለው እሳቸውን ብድር ለመጠየቅ የነበረውን ፍላጎት ሰረዘው። ሊኖራቸው ይችላል ብሎ ያሰባቸውን ዐምስት ስድስት ሠራተኞች እየጠራ ጠየቃቸው። አንዳቸውም የላቸውም፤ ከየት ያመጣሉ? ሁሉም ምስኪን ናቸው። ማሩ ተስፋ ቆርጦ፣ እጁን እያወናጨፈ ወደመውጫው በር አመራ። በኋላው የሠራተኛው ማህበር እድር ፀሐፊ “ማሩ! ማሩ! ምን ሆነህ ነው? እያለ ቢጠራውም አልሰማም። ማሩ በቃ ዓይኔ እያየ፣ በገንዘብ እጦት ልጄ ሞተ ማለት ነው?” እያለ መለፍለፍ ጀመረ።

ማሩ ጃኬቱን መሸጥ አሰበ። የእሱን አሮጌ ጃኬት ማን ይገዛል? ዐምስት ብርም አይሸጥ። ከጎማ የተሠራ ኮንጎ ሸበጡ ስሙኒም አያወጣ። ማሩ ሰማይ ምድሩ ዞረበት። አውራ ጎዳናውን ተከትሎ ወደቤቱ አመራ። መታሰቢያ ቡና ቤት ደረሰ። ቡና ቤቱ የወይዘሮ ፀሐይ ንብረት ነው። ገብቶ ብድር ሊጠይቃቸው አሰበ። ለጥበቃው ችግሩን ነግሮ ወ/ሮ ፀሐይን እንዲጠራለት ጠየቀው። ወ/ሮ ፀሐይ ተጠርተው እንደመጡ እግራቸው ላይ ወድቆ ጠየቃቸው። ሴትዮዋ የሰውነቱን ወጠምሻነት አይተው “ዞር በል! ምን ይላል ይኼ! ይሄን ሰውነት ይዘህ ብር ስትጠይቅ አታፍርም!? ብለው ከግቢያቸው አባረሩት።”

ማሩ በሀፍረት ተሸማቆ ከግቢው ወጣ። ወደቤቱ አቅጣጫ ትንሽ ተራመደና ቆመ። ቤት ቢሄድ ገና እንደገባ ጠንፈ “ብሩን አገኘህ?” ብላ እንደምትጠይቀው አሰበና ሀሞቱ ፍስስ አለ። እቆመበት አስፓልት ዳር ቁጭ አለ። አላፊ አግዳሚው “አሞት ይሆን እንዴ? በሚል” ምን ሆነህ ነው በማለት ከበው ይጠይቁት ጀመር። ለማንም መልስ አልሰጠም።

በመሀሉ “ማሩ! ምነው ምን ሆነሀል? አመመህ እንዴ? ወድቀህ ነው?” የሚል አንድ የሚያውቀው ሰው ድምፅ ሰማ። ማሩ ቀና ብሎ ሰውየውን ሲያይ የመስሪያ ቤቱ ዕድር ፀሐፊው አቶ ምትኩ ነው። “እኔ ነኝ ... አይ ... ደህና ነኝ” አለ። “ምን ሆነሃል?... ተነሳ ... በል ተነሳ! ያዝ ይሄን ብር!” አለው ማሩ ተነስቶ በመቆም “የምን ብር ነው ጋሽ ምትኩ? “ገንዘብ...? ልጄ ... ሞተ ...እንዴ! ቀብር ማስፈፀሚያ የእድር ገንዘብ ነው የምትሰጠኝ?” አለ። አቶ ምትኩ በቁጣ “ማሩ ምንድን ነው የምትቀባጥረው? የምን ሞት ነው? ብሩ የሠራተኛ ማህበሩ ለልጅህ ማሳከሚያ ያበደረህ ነው። ቀስ ብሎ የሚከፈል ነው። እንካ ያዝ!” ብሎ ብሩን አስጨበጠው። ማሩ ነፍሱን አያውቅም። ብሩን እንደያዘ ወደቤቱ በረረ።

ቤት እንደደረሰ ጠንፈን “ተነሽ ጠንፈ! እንሂድ ጤና ጣቢያ! ብሩ ተገኝቷል!” አለና ልጁን አፈፍ አድርጎ በማንሳት አቅፎ ወደበሩ አመራ። ጠንፈ “ኧረ ቆይ ከጎረቤት

ጃንጥላ ልዋስ” ብትለው መቸ ሰምቷት። እሱ ፊት፣ እሷ ኋላ እየበረሩ ጤና ጣቢያ ደረሱ። ካርድ አውጥተው ምርመራ ክፍል ሲገቡ ትንሽ ተንፈስ አሉ። ሐኪሟ አስፈላጊውን ምርመራ አድርጋ ስትጨርስ “አይዟችሁ! የጉሮሮ ህመም ነው” አለችና ያዘዘችለትን መድኃኒት ሀኖ እዚያው እንዲወስድ አደረገች። እነማሩ ቤት ሲደርሱ ልጁ ለውጥ አሳይቷል፤ ተሽሎታል። የጎረቤት ጠያቂ ይጎርፍ ጀመር። ማታ ላይ የፋብሪካ ሠራተኞች ስብስብ ብለው መጥተው “እንኳን ፈጣሪ ማረው!” እያሉ ደስታቸውን ገለፁ። በመሀል የዕድሩን ብር ያመጣለት አቶ ምትኩ “ማሩ ዛሬ ደስታህ ድርብ ነው! የልጅህ የምህረት ቀን ብቻ አይደለም፤ ሌላም ደስታ አለ። የፋብሪካው ሠራተኛ የማህበሩ ሊቀመንበር አድርጎ መርጦሃል! አለው። ማሩ ስላልገባው “እኔን ሊቀመንበር? ማለቴ እኔ እንዴት... ሊቀመንበር...?” አለ ግራ ተጋብቶ። “አዎ ሊቀመንበር ሆነሀል። ሠራተኛው ታታሪነትህን አይቶ መርጦሀል!” አለው። ማሩ የሰማውን ማመን አቃተው። ከጠንፌ ጋር በፈገግታ ተያዩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ማሩ ፎርሳ፣ ጓደኞቹን እንደእንግዳ ቆሞ እንዲያይ ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው?

ለ. “አበሻ ሥራ አይወድም፤ ሰነፍ ነው” የሚለው የአቶ ካሌብ አነጋገር ከማሩ ፎርሳና ጓደኞች ሥራ አንፃር ተገቢ ነው? ካልሆነ ለምን?

ሐ. የማሩ ፎርሳና ጓደኞቹ ድህነት ሥራ የማይወዱ ሰነፍ ስለሆኑ ነው? ወይስ ሌላ ምክንያት አለው?

መ. ማሩ ፎርሳ ስድስት ጓደኞቹን ብር ጠይቆ አለማግኘቱ ምን ይገልጻል?

ሠ. “ይህን ሰውነት ይዘህ ብር ስትጠይቅ አታፍርም!” ባሉት ሴት ሐሳብ ትስማማላችሁ? ከዚህ አባባል ምን ትማራላችሁ?

ረ. የማሩን የድህነት መጠን የሚገልጹ ሐሳቦችን አውጥታችሁ ጻፉ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ማሩ ፎርሳ ክፍል ኹለት” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

4.2.2 ቃላት

1. በ“ሀ” ረድፍ ላሉት ተዛማጅ የሚሆኑ ቃላትን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱና ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

“ሀ”	“ለ”
1. ላባቸው	ሀ. ፈሰሰ
2. ወገባቸው	ለ. ጎዳና
3. ተስፋ	ሐ. ተሸማቀቀ
4. ብድር	መ. ይንቆረቆራል
5. አውራ	ሠ. ቆረጠ
6. ሀሞቱ	ረ. ጎብጧል
	ሰ. ጠየቀ

2. ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ገብጋባ	ጫንቃ	ብድር	ቀባጠረ
ሰረዘ	ምስኪን	ወጠምሻነት	ድርብ

ሀ. ክፉ ንግግራቸውን አስታውሶ ብድር ለመጠየቅ የነበረውን ፍላጎት _____።

ለ. በሰው _____ መኖር የለመደ ሰው ራሱን አይችልም።

ሐ. _____ መሆናቸውን አውቆ ገንዘብ ሳይጠይቃቸው ቀረ።

መ. ጓደኞቹ በሙሉ _____ ናቸው፤ አንዳቸውም ገንዘብ ሊሰጡት አልቻሉም።

ሠ. ልጁን ለማሳከም _____ ቢጠይቅ ማግኘት አልቻለም።

ረ. የሰውነቱን _____ አይተው፣ “ይህን ሰውነት ይዘህ ብር ትጠይቃለህ!” አሉት።

ሰ. በልጁ መታመም ደንግጦ ገንዘብ ለማግኘት ሲል የቆጥ የባጡን _____።

ሸ. ልጁ ስለዳነ፣ የማህበሩ ሊቀመንበር ስለሆነ _____ ደስታ ተሰማው።

መጻፍ

በ4.2.1 የመጻፍ ተግባር የገፀባሕርያት ዝርዝር ያወጣችሁበትን አጭር ልቦለድ ታሪክ ከአንድ ገፅ ባልበለጠ አሳጥራችሁ ጻፉ።

4.2.3 መናገር

ሀ. “ማሩ ፎርሳ ክፍል ኹለት” በሚል ርዕስ ከቀረበው አጭር ልቦለድ የመረጣችሁትን አንቀጽ ሐሳብ ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

ለ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ተግተው በመሥራት የድህነት ህይወታቸውን የለወጡ ሰዎች ታሪክ በንግግር አቅርቡ።

ሰዋስው

1. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ወደጥገኛ ሐረግ ለውጣችሁ ጻፉ።

   ሀ. ልጆች ወላጆቻቸውን ያከብራሉ።

   ለ. መላኩ በመኪና ወደጎጃም ሄደ።

   ሐ. ሰላም ለወንድሟ ስንቅ አዘጋጀች።

   መ. መሠረት የሰው ገንዘብ ወሰደች።

   ሠ. ዓለማየሁ መማሪያ መጽሐፍ ጻፈ።

   ረ. ሠናይት ለእናቷ ብዙ ብር ላከች።

ማስታወሻ

ባለቤት (ድርጊት ፈጻሚ) እና አንድ ማሰሪያ አንቀጽ ያለው የቃላት ሥርአታዊ ስብስብ ነጠላ ዓረፍተነገር ይባላል። የዓረፍተነገሩ ግስ እንዳያስር ሙሉ ስሜት እንዳይሰጥ ሲደረግ ደረጃው ዝቅ ብሎ ጥገኛ ሐረግ ይሆናል። ምሳሌ፦

1. ሰናይት እንጀራ ትጋግራለች።
   (ሰናይት እንጀራ ስትጋግር)
2. ማሩ ወደሰማይ ጦር ወረወረ።
   (ማሩ ወደሰማይ ጦር ሲወረውር)

2. የሚከተሉትን ሐረጎች ወደነጠላ ዓረፍተነገር ለውጣችሁ ጻፉ።

ሀ. አስካል ስልክ ስትደውል

ለ. በክፋ ሥራችን መሬት ስትንቀጠቀጥ

ሐ. ወደማታ ፀሐይ ከወጣች

መ. ቂሱ መስቀል ሲይዙ

ሠ. ዘመድኩን መኪና ገዝቶ

ረ. ዘውዱ ወደጎንደር ሲሄድ

4.3.1 አንብቦ መረዳት

ሸካራ እጆች

ቅድመንባብ

ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ሸካራ እጆች

የአንድ ኩባንያ ባለቤት ብቁ ሥራአስኪያጅ ለመቅጠር ማስታወቂያ አወጣ። ተወዳድረው ካለፉት ሦስት ሰዎች መካከል በዕድሜ ትንሹ ለቃለመጠይቅ ተጠራ። ወጣቱ አለባበሱን አሳምሮ መንፈሱን አንቅቶ ጠበቀ። የኩባንያው ባለቤት የወጣቱን የትምህርትና የሥራ ሁኔታ የሚገልጸውን ማስረጃ አገላብጦ አየ። ወጣቱ ትምህርቱን የተከታተለው አንቱ በሚባሉ ት/ ቤቶች ነው። የመጀመሪያና ኹለተኛ ዲግሪውን የሠራው የናጠጡ ሀብታሞች በሚማሩበት ኮሌጅ ውስጥ ነው።

የኩባንያው ባለቤት "ይህን ሁሉ የትምህርት ክፍያ ይከፍልልህ የነበረው አባትህ ነው አይደል?" ሲል ጠየቀው። "ልጁን አንደላቆ ያስተማረው ማን ሊሆን ይችላል?" ልጁም "አባቴ አይደለም፤ አባቴን በልጅነቴ ነው ያጣሁት" ሲል መለሰለት። "አ! ይቅርታ! ታዲያ ነፃ የትምህርት እድል አግኝተህ ነበር?" ሲል ጠየቀው። ወጣቱም "እስካሁን በትምህርት ጉዞዬ ነፃ የትምህርት እድል የሚባል አላጋጠመኝም" ሲል መለሰ። በዚህ ጊዜ ሥራአስኪያጁ "መቼም ከዘመዶችህ አንዱ የተሻለ ገቢ ያለው ሰው መሆን አለበት?" አለ በፈገግታ። "እኔ ሀብታም ዘመድ የለኝም፤ ኧረ እንዲያውም ዘመድ ራሱ የለኝም" አለ ወጣቱ።

"ታዲያ ይህንን በመሰሉ ት/ቤቶች ገብቶ ለመማር እኮ ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል፤ ማን እየከፈለልህ ነበር የምትማረው?" ሲል በአግራሞት ጠየቀው። "የምትከፍልልኝ እናቴ ነበረች" አለና ወጣቱ በኩራት መለሰ። "እናትህ ምን ዓይነት ሥራ ነው

የምትሠራው?" አለው የኩባንያው ባለቤት። "እናቴ የሰዎችን ልብስ እየሰበሰበች የምታጥብ ናት" አለው ወጣቱ። "ልብስ እያጠበች ነው ይህንን በመሰለ ት/ቤት ያስተማረችህ?" ሲል መልሶ ጠየቀው። "አዎ" "አንድ ጊዜ እጅህን ማየት እችላለሁ?" አለው የኩባንያው ባለቤት። ሲያየው የወጣቱ እጅ ከኬክ የለሰለሰ ነበር።

"ለመሆኑ እናትህን በልብስ አጠባው ረድተሃት ታውቃለህ?" ሲል የኩባንያው ሀላፊ ሌላ ጥያቄ ለወጣቱ አቀረበ። ወጣቱም "አላውቅም" ሲል ባጭሩ መለሰለት። "ለምን? "ለምን?" አለ ሥራሰስኪያጁ።

"እናቴ እኔ ምንም ሥራ እንድሠራ አትፈልግም፤ እንድማር፣ እንዳጠናና እንዳልፍ ብቻ ነው የምትፈልገው፤ ስለዚህ ሥራ ሠርቼ አላውቅም።"አለው።

"በጣም ጥሩ! ቃለመጠይቁን ነገ እንቀጥላለን፤ አሁን ወደቤትህ ሒድና አንድ ነገር አድርግ" አለው።

"ወጣቱ እየገረመው" ምን?" አለ።

"የእናትህን እጅ እጠብ፤ ከዚያ የሆነውን ነገ ትነግረኛለህ።" አለው።

ቤቱ ገብቶ እናቱን እጇን ለማጠብ ጠየቃት፤ አዲስ ነገር ስለሆነባት ጠየቀችው። እርሱም ዛሬ ያጋጠመውን ነገር አጫወታት። እናቱም እጇን እንዲያጥባት ፈቀደችለት።

ውኃና ሳሙና አቀረበና የእናቱን እጆች ማጠብ ጀመረ። የተኮራመቱ፣ የሻከሩ፣ የተሰነጣጠቁ፣ የቆሳሰሉ እጆች! የእርሱንና የእናቱን እጆች እያስተያየ ማልቀስ ጀመረ። እነዚህ እጆች እንዲህ የሆኑት እሱን ለማስተማር መሆኑን አሰበ። እነዚህ ጠባሶች የእርሱ ጠባሶች ናቸው። እነዚህ እጆች ናቸው ለእርሱ የትምህርት ውጤት መሠረቶቹ! እነዚህ እጆች ናቸው ዛሬ ለቆመበት ታላቅ ደረጃ ያበቁት። የእናቱን እጆች አጥቦ ሲጨርስ የቀሩትን ልብሶች ሁሉ ከእናቱ ጋር አጠበ። በዚያች ሌሊት ከእናቱ ጋር ረዥም ስዓት ሲያወሩ አደሩ። ነግራው የማታውቀውን ታሪክ ነገረችው፤ ሰምቶት የማያውቀውን ታሪክም ሰማ።

በማግስቱ ወጣቱ ወደኩባንያው ባለቤት ዘንድ ሄደ:: የኩባንያው ባለቤት "ትናንት ያደረከውንና ያጋጠመህን ልትነግረን ትችላለህ?" ሲል ጠየቀው። "የእናቴን እጆች አጠብኳቸው። የእናቴ እጆች እንደዚህ መሆናቸውን አላውቅም ነበር። ብዙ ነገር ነገረችኝ፤ ልብሶቹንም አብሬያት አጠብኩ።" አለው።

"ታዲያ ምን ተማርክ?" አለው የኩባንያው ባለቤት። "ሦስት ነገሮችን ተምሪያለሁ። መጀመሪያ ነገር አድናቆትና ምስጋናን ተምሪያለሁ። እናቴን ምን ጊዜም ላመሰግን፣ በሒድኩበት ሁሉ ቀድሜ ስሟን ልጠራ እንደሚገባ ተረድቻለሁ። ኹለተኛ፣ እናቴ

ያለፈችበትን እውነተኛ ነገር መረዳት የቻልኩት አብሪያት ሆኜ ሥራዋን ስጋራት ነው። በሱታፌ ካልሆነ በቀር በነቢብና በትምህርት ብቻ የአንድን ነገር ርግጠኛ ጠባይና ሁኔታ መረዳት አይቻልም። ሦስተኛ፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ መኖር ብቻ ሳይሆን ቤተሰባዊ ትሥሥርም ወሳኝ መሆኑን ተረድቻለሁ።" አለ።

የኩባንያው ባለቤት "የምፈልገው ሥራ አሥኪያጅ አሁን ተገኘ። ለእርሱ ሕይወት ሌሎች የከፈሉትን መሰዋዕትነት የሚረዳ፣ አብሮ በመሥራት ችግሮችን መጋፈጥንና መፍታትን የተማረ፣ የሥራ ግቡ ገንዘብ ማግኘት ብቻ ያልሆነ ሰው አሁን ተገኘ" አለና ቀጠረው።

ከእኛ ሕይወት ጀርባ ስንት ሰዎች አሉ? ለመሆኑ ዋጋ እንሰጣቸዋለን? እናመሰግናቸዋለን?... አምፖሎቹ ዝም ብለው አልበሩም። አምፖሎቹ እንዲበሩ ያደረገው ጀኔሬተር ነው። ጀኔሬተሩ ግን አይታይም። የሚታዩት አምፖሎቹ ናቸው። አብዛኛው ሰው አምፖሎቹን ለማሳመርና ቤቱን ለማድመቅ ይጥራል እንጂ ስለጀኔሬተሩ አይጨነቅም። ወሳኙ ግን እርሱ ነው።

(ዳንኤል ክብረት፤ 2005 ዓ.ም. ገጽ 93-96። ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ።)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "አባቴን በልጅነቱ ነው ያጣሁት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. የኩባንያው ባለቤት ስለወጣቱ ማመን የተቸገረው ለምንድን ነው?

ሐ. የኩባንያው ባለቤት ወጣቱን አስተምረውታል ብሎ ያሰባቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ።

መ. የኩባንያው ባለቤት ለምንድን ነው የወጣቱን እጆች ማየት የፈለገው?

ሠ. የኩባንያው ባለቤት ወጣቱ የእናቱን እጆች እንዲያጥብ ያዘዘው ለምንድን ነው?

ረ. ወጣቱ ምንም ሥራ ሠርቶ የማያውቀው መሥራት ስለማይፈልግ ነበር? መሆን የነበረበት ምን ነበር?

ሰ. "እነዚህ ጠባሶች የእርሱ ጠባሶች ናቸው" የሚለውን ዓረፍተነገር ሐሳብ አብራሩ።

ሸ. ወጣቱ የእናቱን እጅ ማጠቡና ልብሶችን ከእናቱ ጋር አብሮ ማጠቡ ያሰገኘለትን ዋነኛ ጥቅም አስረዱ።

ቀ. ወጣቱ የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ለመቀጠር ያስቻለው ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

“ሸካራ እጆች” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

4.3.2 ቃላት

1. ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ወጣቱ የተማረው <u>አንቱ</u> ከተባሉ ት/ቤቶች ነው።

   ለ. ለሚጠይቁት ጥያቄ አዕምሮና መንፈሱን <u>አንቅቶ</u> ጠበቀ።

   ሐ. የትምህርት <u>ማስረጃውን</u> አገላብጠው አዩ።

   መ. ጥሩ ለሠራ <u>አድናቆት</u>፣ መልካም ለሠራ <u>ምስጋና</u> ያስፈልጋል።

   ሠ. እናቴ <u>ያለፈችበትን</u> እውነተኛ መንገድ መረዳት ችያለሁ።

   ረ. ለመሆኑ ላሳደጉና ላስተማሩን ሰዎች <u>ዋጋ</u> እንሰጣለን?

2. በ“ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት/ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ሸካራ	ሀ. ማሳመር
2. ያጣሁት	ለ. ያላገኘሁት
3. ነቢብ	ሐ. ሥራ መሪ
4. ሱታፌ	መ. ለስላሳ ያልሆነ
5. መጋራት	ሠ. ንግግር
6. መቅመስ	ረ. መተጋገዝ
7. ማድመቅ	ሰ. ችግር ማቃለል
	ሸ. በተግባር ማየት
	ቀ. ተግባር

3. የሚከተሉትን ሐሳቦች አብራርታችሁ ጻፉ።

   ሀ. “ኧረ እንዲያውም ዘመድ ራሱ የለኝም።”

   ለ. “አምፖሎቹ ዝም ብለው አልበሩም።”

   ሐ. “ከእኛ ሕይዎት ጀርባ ስንት ሰዎች አሉ!?”

   መ. “እነዚህ ጠባሶች የእርሱ ጠባሶች ናቸው።”

መጻፍ

በ4.3.1 ከአንበባችሁት ጽሑፍ ወጣቱንና እናቱን ከአምፖልና ጀነሬተር ጋር እያወዳደራችሁና እያነፃፀራችሁ “አምፖልና ጀነሬተር” በሚል ርዕስ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

4.3.3 መናገር

“ከእያንዳንዱ ትልቅ ሰው ጀርባ ብልህ ሴት አለች” በሚል ርዕስ የንግግር ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ፣ ሀሳባችሁን በምሳሌ እያስደገፋችሁ ለጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

ሰዋስው

1. ነጠላና ድርብ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ ጻፉ።

   ሀ. እናት ልጇን ትንከባከባለች።

   ለ. የሕዝብ ቁጥር ለልማት አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

   ሐ. የሕዝብ ቁጥር እድገትና ልማት ያፋጥናል።

   መ. ሕዝብ በራሱ ሀብት ነውና የሕዝብ ቁጥር መጨመር አያሰጋም።

   ሠ. ልጆች እናታቸውን ያግዛሉ ወይም ከአባታቸው ጋር ይሠራሉ።

2. የራሳችሁን ሦስት ነጠላ ዓረፍተነገሮችና ሦስት ድርብ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምዕራፍ 5 ሥነሕዝብ

5.1.1 አንብቦ መረዳት

የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤዎች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤዎች” ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምንባቡ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ለ. “ማሽቆልቆል” እና “መንስኤዎች” ከሚለው የርዕሱ ቃላት ተነስታችሁ የሚያሽቆለቁለው ነገር ምን ሊሆን እንደሚችልና መንስኤዎቹም ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምታችሁን ተናገሩ።

የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤዎች

የሕዝብ ብዛት እድገት የሕዝብ ቁጥር በሚጠበቀው ደረጃ እየጨመረ መሄድን ያመለክታል። የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል ደግሞ የህዝቡ መጠን ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥር እያነሰ መሄድ አልያም የህዝቡ ቁጥር ይጠበቅ ከነበረው ቁጥር እያነሰ መሄድ አልያም የህዝቡ ቁጥር በሚጠበቀው ወይም በተተነበየው ደረጃ ሳይጨምር መቅረት ይመለከታል።

የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤዎች በርካታ ናቸው። ከነዚህም መካከል ጦርነት፣ ተላላፊ በሽታ ወይም ወረርሽኝ፣ ከተመኖነት፣ እድሜአለፍ ጋብቻ፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ የዘር ማጥፋት፣ ፍልሰት፣ መንግስት መር የሆነ የወሊድ መጠን ቅነሳና ድህነት ይጠቀሳሉ።

በአንድ ሀገር ውስጥ በሕዝቦች መካከልም ሆነ አንድ ሀገር ከሌላ ሀገር ጋር የሚደረግ ጦርነት ለማህበረሰቡም ሆነ ለሀገሩ ሕዝብ ቁጥር መቀነስ ጉልህ ድርሻ አለው። የጦር መሣሪያን በመጠቀም በሹለት ተቀናቃኝ ሀይሎች መካከል የሚደረግ ውጊያ፣ በአውደ ውጊያው እንደሚሞተው የሰው ቁጥር ብዛት ውጊያው "ጦርነት" ወይም "ግጭት" ተብሎ ሊሰየም ይችላል። ውጊያው ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች ህልፈተ ሕይወትን ያስከተለ ከሆነ "ጦርነት" የሚኾች ቁጥር ከአንድ ሺህ በታች ከሆነ ደግሞ "ግጭት" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ውጊያው ርስበርስም ሆነ በሀገራት መካከል፣ ሚኾቹ ወታደሮቹም ሆኑ ሰላማዊ ዜጎች፣ ውጊያው ከግጭት አልፎ ወደጦርነት ደረጃ ከተሸጋገረ በሁሉም ተፋላሚ ሀይሎች ላይ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መቀነስ ያስከትላል።

ዓለማችን፣ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መቀነስን ያስከተሉ ጦርነቶችን አስተናግዳለች። ለአብነት ያህል በ1940ዎቹ የተካሄደውን ኹለተኛው የዓለም ጦርነት መጥቀስ ይቻላል። በወቅቱ በነበረው የርስበርስ ጦርነት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች ሕይወት አልፏል። በሚሊዮን የሚቆጠሩት ደግሞ ሀገር ጥለው ተሰደዋል። በኢትዮጵያም በ1970ዎቹ በደርግ መንግስትና በሻዕቢያና በህወሓት መካከል በነበረው የርስበርስ ጦርነት በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ አልቋል። ከዚያም በኋላ በኢሐዴግ መንግስትና በኤርትራ መንግስት በነበረው ጦርነት ወደሰባ ሺህ የሚጠጋ ሕዝብ ህይወቱን አጥቷል።

ተላላፊ በሽታ ወይም ወረርሽኝም እንዲሁ በሕዝብ ብዛት እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይፈጥራል። በአጭር ጊዜ በመስፋፋት ወይም በተደጋጋሚ በመከሰት የሕዝብ ብዛት እድገትን ከሚገቱ ወይም ከሚያሽቆለቁሉ በሽታዎች (ወረርሽኞች) መካከል ኤች. አይ. ቪ./የኤድስ፣ ኢቦላ፣ ወባ፣ ኮሌራና በቅርብ ጊዜ የዓለምን ሕዝብ እየጨረሰ ያለው ኮቪድ 19 በዋናነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ በሽታዎች የወሊድ መጠንን በመግታትና የሞት መጠንን በላቀ ሁኔታ በመጨመር (እልቂት በማድረስ) የሕዝብ ቁጥር በአጭር ጊዜ እንዲያሽቆለቁል ያደርጋሉ።

ከተሜነትና እድሜአለፍ ጋብቻም የሕዝብ ብዛት ቁጥርን በመቀነስ ረገድ የራሳቸው ድርሻ አላቸው። በአንድ ማህበረሰብ ወይም ሀገር ውስጥ አብዛኛው ሰው እድሜው ከገፋ በኋላ ጋብቻ የሚፈጽም ከሆነ እያንዳንዱ ሰው የመውለጃ ጊዜው ስለሚያጥር ብዙ ልጆች የመውለድ እድል አይኖረውም። እንዲህ ዓይነት የዘገዬ ጋብቻም ተስፋፍቶ የሚገኘው በሰለጠነ፣ በተማረና ከተሜ በሆነ ማህበረሰብ ዘንድ ነው። በእንዲህ ዓይነት ማህበረሰብ ውስጥ በጋብቻ እድሜ መግፋት ሳቢያ ብቻ ሳይሆን

አብዛኛው ሰው የቤተሰብ ምጣኔ እውቀት ስላለውና አገልግሎቱን ማግኘት ስለሚችል የወሊድ መቆጣጠሪያ የመጠቀም እድሉ የሰፋ ነው። በዚህም የተነሳ የህብረተሰቡ የወሊድ መጠን ያነሰ ይሆናል።

የኢኮኖሚ እድገትም በሕዝብ ብዛት እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። በከፍተኛ የወሊድ መጠን መኖርና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ መካከል ትስስር አለ። በኢኮኖሚ ድሃ በሆኑ አካባቢዎች፣ ለወሊድ መጠን መጨመር ዋነኛው መንስኤ ተብሎ የሚታሰበው የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ ሰዎች አነስተኛ መሆን ነው፤ በተጨማሪም ማኅበራዊ ደረጃቸው ዝቅ ያሉ ሰዎች መብዛትና የተማሩ እናቶች ቁጥር ማነስ የውልደት መጠን እንዲጨምር አስተዋፅኦ ያደርጋል።

የዘር ማጥፋት፣ የዘር ማጽዳትና በፓለቲካ ወይም በኢኮኖሚ እርካታ እጦት ሳቢያ ወደሌላ ሀገር የሚደረግ ፍልሰት ለሕዝብ ብዛት ማሽቆልቀል መንስኤዎች ናቸው። ከነዚህም በተጨማሪ በግዳጅ ወይም በፍላጎት የሚፈፀም ማንነትን የመተው (የመካድ) ተግባር ይጠቀሳል። መንግስት መር የሆነ የወሊድ መጠን መቀነሻ ማበረታቻዎች ወይም ማስገደጃዎች መተግበር ሌላው ለሕዝብ ቁጥር ማሽቆልቆል ምክንያት ነው፤እንዲሁም ለማግባት ወይም ለመውለድ በማያስችል የድህነት ሕይወት ውስጥ መኖር ለሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤ ይሆናል።

(ከዳምጠው ተሰማ ጥናት ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ለሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤ የሚሆኑ ዐምስት ምክንያቶች ዘርዝሩ።

ለ. ጦርነት ለሕዝብ ብዛት ማደግ ምክንያት ይሆናል? ከሆነ እንዴት? ካልሆነ ለምን?

ሐ. በኹለት አገሮች መካከል ውጊያ ተከፍቶ የዘጠኝ መቶ ሰዎች ሕይወት አልፏል፤ በኹለቱ አገሮች መካከል የተከሰተው ግጭት ነው ወይስ ጦርነት?

መ. በከፍተኛ የወሊድ መጠን መኖርና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ መካከል ያለውን ትስስር አስረዱ።

ሠ. በኢኮኖሚ ድሃ በሆኑ ሀገራት ለወሊድ መጠን መጨመር ዋናው መንስኤ ምንድን ነው? እያንዳንዱን መንስኤ አብራሩ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል መንስኤዎች” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሠጣችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

5.1.2 ቃላት

1. የተሠመረባቸውን ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ባላቸው ሌሎች ቃላት በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

   ሀ. በጦርነት ምክንያት ሰዎች ሀገር <u>ጥለው</u> ተሰደዋል።

   ለ. በነበረው ጦርነት ብዙ ሰው <u>አልቋል</u>።

   ሐ. ዓለም፣ ሕዝብ ያስጨረሱ በርካታ ጦርነቶችን <u>አስተናግዳለች</u>።

   መ. <u>ለአብነት</u> በኹለተኛው የዓለም ጦርነት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አልቀዋል።

   ሠ. ወረርሽኝ በሕዝብ ብዛት እድገት ላይ ከፍተኛ <u>ተፅዕኖ</u> አለው።

   ረ. አንዳንድ ሰዎች አገራቸውን <u>ትተው</u> ለሰው ሀገር አገልጋይና ጠበቃ ይሆናሉ።

   ሰ. የሕዝብ ቁጥር <u>ማሽቆልቆል</u> መንስኤዎች ብዙ ናቸው።

   ሸ. የሕዝብ ብዛት ማሽቆልቆል የሕዝብ ቁጥር <u>በሚጠበቀው</u> ደረጃ ሳይጨምር መቅረት ነው።

2. ለሚከተሉት ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. አውደውጊያ

   ለ. ጦርነት

   ሐ. እድሜ አለፍ

   መ. ግጭት

   ሠ. ወረርሽኝ

   ረ. ሳቢያ

መጻፍ

ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ባለሦስት አንቀጽ ተራኪ ድርሰት ጻፉ።

ሀ. የትምህርትቤታችን ግንባታ

ለ. የዓባይ ግድብ

ሐ. የአካባቢያችን መንገድ ሥራ

መ. የርከን ሥራዎች

ማስታወሻ

ተራኪ ድርሰት ሁነትንና ድርጊትን እንዲህ ሆነ፣ ወይም እንዲህ ተደረገ በማለት መንገሪያ ወይም መተረኪያ ነው። ታሪኩ ራሱ ተራኪው የደረሰበት፣ በልምድ ያገኘው፣ በሀሳቡ ያውጠነጠነው ወይም ከሌላ የሰማው ሊሆን ይችላል።

(ዳኛቸው ወርቁ, 1977፣ 171)

5.1.3 ማዳመጥ

ስደተኛዋ ዋኔ

ቅድመማዳመጥ

“ስደተኛዋ ዋኔ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ሐሳቦችን እየጻፋችሁ በትኩረት አዳምጡ።



ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

   ሀ. ዋኔዋ “በእኔና በሌሎች የደረሰ መከራ አይድረስብህ” ስትል ምን ማለቷ ነው? በእርሷና በሌሎች የደረሰው መከራ ምንድን ነው?

   ለ. “እንደዛሬው ሳይሆን...” የሚለው ሐረግ ምን ይገልጻል?

   ሐ. ዋኔዋ ምን ሆና ነው ጨዋታዋን አቋርጣ ወደወንዝ የወረደችው?

   መ. ዋኔ ወፍ ናት፤ እንዴት ከሰው ጋር ተነጋገረች?

   ሠ. ዋኔዋ ትንሽ ናት ትልቅ? እንዴት አወቃችሁ?

   ረ. ዋኔዋ የተሰደደችው በምን ምክንያት ነው?

   ሰ. እረኛውን ያሳዘነው የሰው ልጅ ከንቱ ሥራ ምንድን ነው?

2. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ማለዳ

   ለ. ጉረኖ

   ሐ. መስክ

   መ. አዝመራ

   ሠ. ንፍሮ

   ረ. አገልግል

ሰዋስው

ጥንድ ዓረፍተነገሮቹን በማቀናጀት ድርብ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፦

ማሚት ከሥራ ቦታ ወደቤት መጣች።

ማሚት ዶሮ ወጥ ሠራች።

ማሚቲ ከሥራ ቦታ ወደቤት መጣችና ዶሮ ወጥ ሠራች።

ሀ. በርትተሽ በመማር ኑሮሽን ለውጪ።

በንግድ ሥራ በመሰማራት አትራፊ ሁኚ።

ለ. የተማሩ ሴቶች ልጆችን አራርቀው ይወልዳሉ።

የተማሩ ሴቶችን ስለቤተሰብ ምጣኔ ማስተማር አይከብድም።

ሐ. ወላዶች ይመጣሉ።

መውለጃ ክፍሉን ለወላዶች እናዘጋጅላቸው።

መ. የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል።

የሕዝብ ቁጥር ማደጉ አይቀርም።

ሠ. ወደውጭ ሀገር ይሄዳል።

ሀገር ውስጥ ይማራል።

5.2.1 አንብቦ መረዳት

የመውለድ መጠንን የሚወስኑ ሁኔታዎች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ በአንድ ቤተሰብ በአማካይ ስንት ልጆች ይኖራሉ?

ለ. ብዙ ልጆች ያሏቸው ሰዎች ኑሮ ጥቂት ልጆች ካሏቸው ቤተሰቦች ኑሮ ይለያል? የትኞቹ የተሻለ ሕይወት ይኖራሉ?

የመውለድ መጠንን የሚወስኑ ሁኔታዎች

የውልደት መጠን፣ እናቶች የሚወልዷቸውን የሕፃናት ብዛት የሚገልፅ ጽንሰ ሐሳብ ነው። የወላጆች የገቢ መጠን ከልጆቻቸው ቁጥር ጋር የተመጣጠነ ከሆነ፣ የሕዝብ እድገቱ ጤናማ ይሆናል። የወላጆች የገቢ መጠን ከልጆቻቸው ቁጥር ጋር ካልተመጣጠነ ደግሞ እንደችግር ይቆጠራል። የውልደት መጠን በባህላዊ፣ በሃይማኖታዊና በማኅበራዊ መስተጋብሮች ይወሰናል።

የውልደት መጠንን ከፍ ከሚያደርጉ ባህላዊ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የልጅነት ጋብቻ ነው። በብዙ ሀገሮች በተለይ ሴቶች እድሜያቸው ለጋብቻ ሳይደርስ እንዲያገቡ ይደረጋሉ። በለጋ እድሜያቸውም መውለድ ይጀምራሉ። በትዳርም ረጅም ጊዜ ስለሚቆዩ፣ አማካይ የመውለድ መጠናቸው ከፍተኛ ይሆናል። ይህ ባህላዊ ችግር ከወላጆች የማሳደግ ኢኮኖሚያዊ አቅም ጋር ካልተመጣጠነ ልጆችንም ሆነ ወላጆችን ለረሃብና ለችግር ይዳርጋቸዋል። ችግሩን ለማስወገድ ወላጆችን ማስተማር አንዱ መፍትሔ ሊሆን ይችላል። የተማሩ ወላጆች የአስተሳሰብና የመረዳት ለውጥ ስለሚያመጡ ልጆቻቸውን ከመዳር ይልቅ ወደትምህርት ቤት ይልካሉ። ሌላው ባህላዊ ሁኔታ ልጅ መውለድን እንደፀጋ የመቁጠር አስተሳሰብ ነው። በዚህም "ወንድ መውለድ ጥቃትን ለመመከት"፣ "ሴት ልጅ መውለድ ብረት መዝጊያ የሚሆን አማች ለማምጣት" በሚሉ አመለካከቶች ሴቶች ደጋግመው እንዲወልዱ ይበረታታሉ። ይህም የሕፃናትን ቁጥር ይጨምራል።

ሃይማኖትም በተመሳሳይ የውልደት መጠን እንዲጨምር ምክንያት ሊሆን ይችላል። "ልጅ መውለድ የፈጣሪ ፀጋ ነው" የሚለው አስተሳሰብ ምንጩ ሃይማኖታዊ ነው። ስለሆነም ብዙዎቹ የሥነተዋልዶ ዘዴዎች በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል። ወሊድን መቆጣጠር፣ የሃይማኖትን ህግ እንደመጣስ ሊቆጠር ይችላል። በዚህም የእናቶች ልጅ የመውለድ መጠን ይጨምራል። በተከታታይ መውለድ በእናቶች ጤንነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ በልጆች አስተዳደግ ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ይህም ከቤተሰብ አልፎ ማኅበራዊ ችግር ያመጣል።

የወሊድ መጠንን ለመቀነስና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል። እናቶች ግንዛቤ ከሌላቸው ህይወታቸውን በተሻለ መንገድ መምራትም ሆነ ጤንነታቸውን መጠበቅ ይሳናቸዋል፤ የልጆችን ቁጥር

መመጠንም ሆነ አራርቆ መውለድ አይችሉም። እናቶች ብዙ ልጆች በመውለድ ጤንነታቸውንና የልጆቻቸውን አስተዳደግ ይጎዳሉ።

በአጠቃላይ ያልተመጣጠነ የውልደት መጠንን ለመቀነስ፣ ስለቤተሰብ ምጣኔና ስለአራርቆ መውለድ ጠቀሜታ ለወላጆች ማስተማር ተገቢ ነው። መጥኖ መውለድ የልጆች ጤንነትና እድገትን ለመጠበቅ፣ እንዲሁም የልጆች ፍላጎትን አሟልቶ ለማሳደግ ይጠቅማል። በዚህም የተመጣጠነ የሕዝብ እድገት መፍጠር ይቻላል፤ ልጆች፣ ቤተሰብና ሀገርም ተጠቃሚ ይሆናሉ።

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ 8ኛ ክፍል። (2007ዓ.ም) ገፅ 65-66 ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የውልደት መጠን ምን ማለት ነው?

ለ. የሕዝብ እድገት ጤናማ የሚሆነው ምን ሲሆን ነው?

ሐ. የውልደት መጠንን የሚወስኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

መ. ለውልደት መጠን መጨመር ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን ዘርዝሩ።

ሠ. መጥኖ የመውለድ ጥቅምና ጉዳቶችን በአካባቢያችሁ ከሚኖሩ ቤተሰቦች ሕይወት ጋር እያገናዘባችሁ ግለጹ።

ረ. ሃይማኖት እንዴት ለውልደት መጠን መጨመር ምክንያት እንደሚሆን አስረዱ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የመውለድ መጠንን የሚወስኑ ሁኔታዎች” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

ማስታወሻ

የአቀላጥፎ ማንበብ የትክክለኛነት መስፈርቶች

ያለምንም ስህተት ማንበብ

- ፊደላትንና ቃላትን በትክክል መጥራት (ሳይንተባተቡ ማንበብ)
- በራስ ማስተካከል
- ማሚላት
- መደጋገም
- ተገቢ አነባበብን (ማላላት ወይም ማጥበቅን ጨምሮ) መጠቀም

በስህተት ማንበብ ማለት

- መንተባተብ
- ማስተካከል አለመቻል
- መግደፍ
- በሌላ መተካት
- መዝለል
- መተው ወዘተ.

5.2.2 ቃላት

በሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ እንዲኖራቸው አድርጋችሁ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- አራርቆ መውለድ የእናቶችን ጤና ለመጠበቅ ይረዳል።

ሀ. የተመጣጠነ

ለ. ውልደት

ሐ. ባህላዊ

መ. የጋብቻ እድሜ

ሠ. ለጋ

ረ. ትዳር

ሰ. ፀጋ

ሸ. ብረት መዝጊያ

ቀ. አማች

በ. ጤና

መጻፍ

በሚከተለው አስተዋፅኦ ታግዛችሁ “ከዘር እስከመኸር” በሚል ርዕስ አንድ አርሶአደር የሚያከናውናቸውን ተግባራት በትረካ ስልት ጻፉ።

አስተዋፅኦ

- ማሳን መከስከስ
- ማሳን ማለስለስ፣
- ማሳን ዘር መዝራት
- ማረም
- ማጨድ
- መከመር
- መውቃት
- መጫን/ማጓጓዝ
- በጎተራ መከዘን

5.2.3 መናገር

በቡድን ተመዳድባችሁ አንዱ ቡድን ለጤናማ ሕይወት “የልጆች መብዛት ጥሩ ነው።” የሚል ሐሳብ በመደገፍ፣ ሌላው ቡድን ለጤናማ ሕይወት “የልጆች መብዛት ጥሩ አይደለም” የሚል ሐሳብ በመደገፍ ክርክር ተከራከሩ።

ማስታወሻ

ክርክር በሚካሄድበት ጊዜ ሊታወሱ የሚገቡ ነጥቦች፡-

1. የሚከራከሩበትን ርዕስ በቅድሚያ ማወቅ፣
2. ከልዩ ልዩ መረጃ ምንጮች የመከራከሪያ ነጥቦችን አስቀድሞ ማዘጋጀት፣
3. ሐሳቦች ሲዘጋጁና ክርክር ሲካሄድ ማስታወሻ መያዝ፣
4. ከርዕሱ አለመውጣት፣
5. የተመደበውን የመከራከሪያ ጊዜ ማክበር፣
6. የተከራካሪን ሐሳብ እንጂ ተከራካሪን አለመንቀፍ፣
7. ተራ በመጠበቅ መከራከር፣
8. የክርክር ዳኞችን ወይም ዳኛን ውሳኔ ማክበር።

ሰዋስው

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በኢሀላፊ ጊዜ ጻፏቸው።

ምሳሌ፦

ሀላፊ ጊዜ	ኢሀላፊ ጊዜ
1. ዝናሽ የወርቅ ቀለበት ገዛች።	ዝናሽ የወርቅ ቀለበት ትገዛለች።
2. አርሶአደሩ ትልቅ ቤት ሠራ።	ገብሬ ትልቅ ቤት ይሠራል።

ሀ. ሙሀመድ ትልቅ ሱቅ ከፈተ።

ለ. ሃሊማ ቆንጆ ጫማ አደረገች።

ሐ. ወርቅነሽ ወደቡሬ ሄደች።

መ. መርከብ ኹለት በራዎች ሸጠ።

ሠ. ስመኝሽ ልጆቿን ጥሩ አድርጋ መከረች።

5.3.1 አንብቦ መረዳት

ብድር መላሽ ያርገኝ!

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች ምን ሲያጋጥማቸው ነው “ብድር መላሽ ያርገኝ” የሚሉት?

ለ. ከርዕሱ በመነሳት የጽሑፉ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ብድር መላሽ ያርገኝ!

አንድ ቀን አንዲት ትንሽ የገጠር መንደር ኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ደረሰባት። በዚህም በመንደሯ የሚገኙ ቤቶች በሙሉ ፈረሱ። የመንደሯ ነዋሪዎች ተፈናቅለው ተሰደዱ። ይህ ሁኔታ ለአይጦች መልካም አጋጣሚ ፈጠረ። አይጦች በዚች ትንሽ መንደር ያለሥጋት መኖርና መራባት ጀመሩ። በጥቂት ወራትም ቁጥራቸው በመቶ ሺዎች ... ከዚያም በሚሊዮኖች ጨመረ።

ከትንሿ መንደር አለፍ ብሎ አንድ ትልቅ ሐይቅ ነበር። በርካታ ዝሆኖች ውኃ ለመጠጣት ወደሐይቁ የሚሄዱት በመንደሯ በኩል ነበር። ታዲያ እነዚህ ዝሆኖች ሲጓዙ ግዙፍ ከመሆናቸው የተነሳ በእግራቸው ብዙ አይጦችን እየደፈጠጡ ይገድሉ ነበር። አንድ ዝሆን ብቻ በቀን ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ አይጦችን ይገድላል። አይጦቹ በወገኖቻቸው ላይ የሚደርሰው ግድያ እንዲቆም በማሰብ ተሰብስበው

ተወያዩ። በኋላም የአይጦች ንጉሥ ራሱ ሄዶ የዝሆኖችን ንጉሥ እንዲያነጋግር ተስማሙ።

በነጋታው ጧት የአይጦች ንጉሥ በርካታ ረዳቶቹን ይዞ የዝሆኖቹን ንጉሥ ለማነጋገር ሄደ። የዝሆኖች ንጉሥም ጥሩ አቀባበል አደረገለት። ከዚያም ለምን እንደመጣ ጠየቀው። የአይጦች ንጉሥም "ንጉሥ ሆይ!" በእውነቱ ዝሆኖች በወገኖቼ ላይ እያደረሱ ያለው ጭፍጨፋ በጣም ይዘገንናል። በርግጥ ዝሆኖቹ በእኔ መንደር የሚያልፉት ለሐይቁ ቅርብ ሆኖ አግኝተውት ይሆናል። ሆኖም ወገኖቼን እየገደሉ እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። ስለዚህ አመጣጤ በሌላ መስመር እንዲጓዙ ትዕዛዝ እንዲሰጡልኝ ለማመልከት ነው። "እኔና ወንድሞቼም አንድ ቀን ብድራችንን እንከፍል ይሆናል" በሚል የዛቻ ንግግር ደመደመ።

በዚህ ጊዜ የዝሆኖቹ ንጉሥ ከልቡ ሳቀና፣ "ብድር መክፈሉን እንኳን ተወው፤ ደግሞ እናንተ ትንንሽ ፍጡሮች በምን አቅማችሁ ነው ለዝሆን ብድር የምትከፍሉት? ለማንኛውም ግን ወገኖቼ በሌላ መስመር እንዲጓዙ ትዕዛዝ አስተላልፋለሁ!" ብሎት ሸኘው። የአይጦች ንጉሥም ወገኖቹን ሰብስቦ ከዚህ በኋላ አንድም ዝሆን በመንደራቸው እንደማያቋርጥ ነገራቸው። አይጦቹም ደስታቸውን በጭፈራና በሆታ ገለፁ።

እውነትም በነጋታው ዝሆኖቹ መንገዳቸውን ቀይረው በሌላ መስመር መጓዝ ጀመሩ። ሆኖም ከጥቂት ቀናት በኋላ የሀገሪቱ ንጉሥ ዝሆኖችን ለሠራዊት ስንቅ ማጓጓዣነት ስለፈለጋቸው፣ በብዛት ይታደኑ ጀመር። ታዲያ አንድ ቀን አይጦቹ በሚኖሩበት አካባቢ የሚኖሩት ዝሆኖች ውኃ ሊጠጡ በመስመር ሲጓዙ የንጉሡ ጠባቂዎች ተመለከቷቸው። የንጉሡ ጠባቂዎች ቶሎ ብለው ጊዜ ሳያጠፉ ትልቅ መረብ ዝሆኖቹ ላይ ወርውረው አጠመዷቸው። ዝሆኖቹ ቢዘሉ፣ ቢንፈራገጡ፣ ቢወራጩ ከወጥመዱ ማምለጥ ሳይችሉ ቀሩ።

በመጨረሻ ግን የዝሆኖቹ ንጉሥ የአይጦቹን ዛቻ አስታወሰ። እናም ጮክ ብሎ የአይጦቹን ንጉሥ ጠራ። የአይጦቹ ንጉሥም የዝሆኑን ጥሪ ሰምቶ "ምን አጋጠማቸው?!..." በማለት ወገኖቹን ሰብስቦ ከስፍራው ደረሰ። ዝሆኖቹ በሙሉ ወጥመድ ውስጥ ገብተው ለማምለጥ ይወራጫሉ። የአይጦች ንጉሥም፣ "አይዟችሁ ተረጋጉ!... አሁን ይህን መረብ እኔና ወገኖቼ በጥርሳችን እምሽክ ነው የምናደርግላችሁ! ..." ብሎ ሁሉንም አይጦች በግራና በቀኝ አሰማራቸው።

አይጦቹ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ መረቡን ብጥስጥሱን አወጡት። ዝሆኖችም እየዘለሉ መውጣት ጀመሩ። በመጨረሻም የዝሆኖቹ ንጉሥ የአይጦቹን ንጉሥ፣ "ትንንሽ ናችሁ ብዬ በመናቄ ይቅርታ አድርጉልኝ! ህይወታችንን ስላተረፋችሁልን እናመሰግናለን!" ብሎት ተጨባብጠው ተለያዩ።

(እስክንድር፤ (2003)። የሕፃናት ተረቶች፣ ከገጽ 6-9፣ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የመሬት መንቀጥቀጥ ለሰዎች መጥፎ፣ ለአይጦች መልካም አጋጣሚ መሆን ምንን እንድንገነዘብ ያደርገናል?

ለ. ሐይቅ ባይኖር ዝሆኖች አይመጡም ነበር፤ ዝሆኖች ባይመጡ አይጦች አይሞቱም ነበር። ይህንን ምክንያታዊ የድርጊቶች ቁርኝት ከሀገራችን አንዳንድ ጉዳዮች ጋር ማያያዝ ይቻላል? እንዴት?

ሐ. የዝሆኖች ንጉሥ በአይጦች ንጉሥ መሳለቁ ትክክል ነበር ትላላችሁ? ለምን?

መ. ከአይጦች ለዝሆኖች ብድር መመለስ የሰው ልጅ ምን መማር ይችላል?

ሠ. የዝሆኖች ንጉሥ የአይጦች ንጉሥን ይቅርታ የጠየቀበት ምክንያት ምንድን ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

“ብድር መላሽ ያርገኝ!” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

5.3.2 ቃላት

1. በ“ሀ” ክፍል ላሉት ቃላት/ሐረጋት ከ“ለ” ክፍል ተዛማጅ ቃላትን መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. በመረብ	ሀ. አጋጣሚ
2. ክልቡ	ለ. ደረሰ
3. ንጉሥ	ሐ. መኖር
4. ያለሥጋት	መ. ሆይ!
5. መልካም	ሠ. ሳቀ
	ረ. አጠመዷቸው

2. የተሠመረባቸውን ቃላት በሌሎች ዓረፍተነገሮች በማስገባት የቃላቱን ፍቺ አብራሩ።

ምሳሌ፦

የመጀመሪያ ዓረፍተነገር	ሌላ ዓረፍተነገር
በወገን ላይ የሚደርሰው <u>ግድያ</u> እንዲቆም ተመካከሩ።	የእንስሳት <u>ግድያ</u> በህግ መከልከል አለበት።

ሀ. አንዲት የገጠር <u>መንደር</u> የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ደረሰባት።

ለ. በተፈጠረው ግጭት የአካባቢው ሰው <u>ሥጋት</u> ላይ ነው።

ሐ. ዝሆን <u>ግዙፍ</u> እንስሳ ነው።

መ. የዝሆኖች ንጉሥ ለአይጦች ንጉሥ ጥሩ <u>አቀባበል</u> አደረገለት።

ሠ. ዝሆኖች ሲጓዙ ብዙ አይጦች <u>ደፈጠጡ</u>።

ረ. ብዙ ወፎች <u>መስመር</u> ሰርተው ይበራሉ።

ሰ. የአይጦች ንጉሥ ለዝሆኖች ንጉሥ <u>ብድር</u> ለመመለስ ያብቃኝ አለ።

ሸ. የዝሆኖች ንጉሥ ለአይጦች ንጉሥ፣ ትንንሽ ፍጡሮች ምን <u>አቅም</u> አላችሁ አለ።

ቀ. ዝሆኖች መንገዳቸውን <u>ቀይረው</u> በሌላ መስመር ተጓዙ።

በ. ዝሆኖች <u>ቢንፈራገጡ</u>፣ <u>ቢወራጩ</u> ከወጥመድ ማምለጥ አልቻሉም።

ተ. አይጦች መረቡን በጥርሳቸው <u>እምሽክ</u> አደረጉት።

መጻፍ

የሚከተለውን አስተዋፅኦ መሠረት በማድረግ “የኤሊና ጥንቸል የሩጫ ውድድር” በሚል ርዕስ በትረካ ስልት ድርሰት ጻፉ።

አስተዋፅኦ

- ጥንቸል ኤሊን መንገድ ላይ ስትጓዝ አየቻት።
- ጥንቸል በኤሊ ቀርፋፋነት ተሳለቀች።
- ኤሊ ተናዳ የሩጫ ውድድር ግጠሚኝ አለች።
- ጥንቸል ከልቧ እየሳቀች ተስማማች።

- ዳሞች ተመረጡ።
- የመጀመሪያውን ዙር ጥንቸል በሰፊ ልዩነት አሸነፈች።
- ኤሊ ድጋሚ ፍልሚያ ጠየቀች።
- ዳሞችም ፈቀዱላት።
- ውድድሩ ተጀመረ።
- ወንዝ ስለሞላባት ጥንቸል መሻገር ተቸገረች።
- ዉኃው ሲጎድል ኤሊ ተመልሳ ከወንዙ ደረሰች።
- ጥንቸል ልቧ እስኪፈርጥ ብትሮጥም ልትደርስባት አልቻለችም።
- ኤሊ አሸነፈች።
- ጥንቸል ሌላ ፍልሚያ ጠየቀች።
- ኤሊ ከወንዙ ሳትደርስ ጥንቸል ተመለሰች።
- ሀይለኛ ሙቀት ስለነበረ በኤሊ እየሳቀች ዛፍ ሥር አረፍ አለች።
- እንቅልፍ አሸለባት።
- አሸንፋ ሲጨበጨብላት በህልሟ እያየች ረጅም ጊዜ ተኛች።
- ኤሊ ቀስ ብላ ኮሽታ ሳታሰማ አልፋት ሄደች።
- ኤሊ በድጋሜ አሸነፈች።
- በከፍተኛ ጮኸትና ጭብጨባ ሽልማት ወሰደች።

5.3.3 መናገር

በጥንድ እየሆናችሁ ጋዜጠኛንና ኤሊን በመወከል ቃለምልልስ አድርጉ።

ጋዜጠኛ፡- ክብርት ወይዘሪት ኤሊ! በመጀመሪያ ለዚህ ቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ።

ኤሊ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

ጋዜጠኛ፡- ለመጀመር ያህል ራሰዎን ለተመልካቾች ቢያስተዋውቁልኝ?

ኤሊ፡- ኤሊ በትዕግስቱ እባላለሁ፤ የተወለድኩት መዳብቸ ከሚባል ጎጥ ነው። የአየሩ ፀባይና የቦታው አቀማመጥ ለኤሊ መኖሪያ ምቹ ቦታ ነው፤ 10ኛ ዓመቴን አክብሪያለሁ... አይበቃም!?

ጋዜጠኛ፡- አመሰግናለሁ! ለውድድር ያነሳሳዎትን ምክንያት ሊገልጡልኝ ይችላሉ?

ኤሊ፡- በጥንቸል የማይገባ ንግግርና ስላቅ በመናደድ ነው ፍልሚያ የጠየኩት።

ጋዜጠኛ፡- የጥንቸል ፍጥነት የታወቀ ነው፤ የኤሊ ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ ነው፤ እንዴት ደፍረው ጠየቁ?

ኤሊ፡- አየህ! በራስ ከመመካት በፈጣሪ መመካት ይበልጣል። በዚያ ላይ ደግሞ አንተ አትግፋ እንጅ ከተገፋህ በለስ ይቀናሀል።

ጋዜጠኛ፡- በመጀመሪያው ውድድር በሰፊ ልዩነት ሲሸነፉ አልደነገጡም? ተስፋስ አልቆረጡም?

ኤሊ፡- መደንገጥም፣ ተስፋ መቁረጥም ከእኔ ዘንድ ቦታ የላቸውም፤ ካሰብኩት ለመድረስ በልህ፣ በወኔ መግፋት ብቻ ነው...

(ቀሪውን ክፍል ራሳችሁ ቀጥሉ)

ሰዋስው

“መከረ”ና “ፈለጠ” በሚሉት ግሶች በተለያየ ቅርጾቸው በርካታ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡- “ሰበረ” የሚል ግስ የተለያዩ ቅርጾች፡-

ሀ. እኔ እንጨት ሰበርኩ።

ለ. አንተ እንጨት ሰበርክ።

ሐ. አንች እንጨት ሰበርሽ።

መ. እርሱ እንጨት ሰበረ።

ሠ. እርሷ እንጨት ሰበረች።

ረ. እኛ እንጨት ሰበርን።

ሰ. እናንተ እንጨት ሰበራችሁ።

ሸ. እነርሱ እንጨት ሰበሩ።

ምዕራፍ 6 በረሃማነት

6.1.1 አንብቦ መረዳት

የተፈጥሮ ደን መመናመን

ቅድመንባብ

ለሚከተሉት ቃላት በቃላችሁ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ደን

ለ. ሰንሰለት

ሐ. ወጣገባ

መ. ገደል

ሠ. ተራራ

ረ. ተፈጥሮ

የተፈጥሮ ደን መመናመን



የወፍ ዋሻ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን፣ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን፣ ከደብረብርሃን ከተማ በአንኮበር መንገድ በ24 ኪ.ሚ ርቀት ላይ ይገኛል። በምዕራብ ክፍል ገደላማ፣ በምስራቅ ደግሞ ወጣገባ ነው። ደኑ ሸለቆ የበዛበት ሲሆን ከስምጥ ሸለቆ ይዋሰናል። ከደቡብ ምስራቅ ወደሰሜን ምዕራብ የተዘረጋው የተራራማ ሰንሰለቱ ተፋሰስ የአዋሽን ሸለቆ ወደምስራቅ፣ ዓባይን ደግሞ ወደምዕራብ ያዋስናል።

የወፍ ዋሻ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን በአብዛኛው በአረጆና ግዙፍ በሆኑ በአበሻ ጽድ፣ በዝግባና በወይራ ዛፎች የተሸፈነ ቢሆንም ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የአበሻ ጽድ ነው። ደኑ በእጅጉ ተጎድቷል። ተተኪ ዛፎቹ ከላይ ወደታች ሥነምህዳሩን ጠብቀው የበቀሉ ቢሆንም ከጊዜ ወደጊዜ ግን እየሳሱ መጥተዋል። ከነዚህ መካከል ጅብራ፣

ጓሣ፣ ጋርዳ፣ አስታ፣ የአበሻ ጽድ፣ ኮሶ፣ አሞጃ፣ ዝግባ፣ ወይራ፣ እምብስ፣ ብሳና፣ ዋንዛ፣ አጣጥ፣ ቋጥቋጦና የሣር ዝርያዎች ይገኙበታል።

ደኑ በዘንቦ፣ በእምትና በመስጫ ቀበሌዎች በመንከርና በእርሻ ማሳ አልፎ አልፎ የተቆራረጡ ክፍሎቹ ይጨምራል። በአንድ ላይ የተጠቃለለው የደን ሽፋን ከ600 ሺህ ሄክታር አይበልጥም። በየመንደሩ የተከፋፈሉት ደኖች የዝግባና የወይራ ዛፎችን በውስጣቸው ይዘዋል።

የወፍ ዋሻ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን በአብዛኛው በአንኮበር ወረዳ ይገኛል። ደኑ የጓሣ፣ ጅብራ፣ ጋርዳና (የዋልያ ሾህ) ጦስኝ ይበቅልበታል። የገደሉን አፋፍ ተከትሎ የሚያዋስኑት ከምስራቅ ወደምዕራብ ደበሌ፣ ጎሾሀገር፣ ቀይት፣ አባሞቴ፣ ጎደበረትና ባሶዳንሳራ ጎጦች ናቸው። በአጠቃላይ ደኑ የ15 ቀበሌዎች አካል ሲሆን እነዚህ ቀበሌዎች ደግሞ በሦስት ወረዳዎች ይከፈላሉ። በዚህም ባሶና ወራና በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ እስከሰሜን ምዕራብ ድረስ ያካልላል። አንኮበር ደግሞ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ደኑን ያዋስናል። ይህም ከ2000 እስከ 3700 ሜትር ከፍታ ከባሕር ወለል በላይ የሚገኝ በሳቦ አፍሮ አልፓፋን ሥርዓተምህዳር ላይ ይገኛል።

የተፈጥሮ ደኑ ስፋት ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ መጥቷል። በ1994 ዓ.ም. 92,200 ሄክታር ይሸፍን ነበር። በ2002 ዓ.ም. ወደ8290 ሄክታርና በ2005 ዓ.ም ደግሞ ወደ 8222 ሄክታር ዝቅ ማለቱ በጥናት ተረጋግጧል። ባለፉት ሦስት ዓመታትም ከዚህ ሊቀንስ እንደሚችል አሁን የሚታዩ ችግሮች ያመለክታሉ።

የወፍ ዋሻ ደን እየተመናመነ ቢመጣም ማራኪ የሆነ የሥነምህዳር አምባ ነው። በአቀማመጡ የደጋማውን ከፍተኛ አካባቢ ከደበሎ እስከባሶ ደንጎራ የአፍሮ አልፖይን ገፅታ ያላቸው አፅዋት ይገኙበታል። እፅዋቶቹ ከዋናው ደን ቀጥ ባለ ገደል ተከፍለዋል። ወደዋናው ደን መግቢያ አካባቢ አልፎ አልፎ ባሉ ገደላማ ቦታዎች የገደሉን አፋፍና ግርጌ የሚሸፋን የአስታ ዛፉ ነው። ደኑን ወደታች ሲመለከቱት የአስታው ዛፍ እየቀነሰ የአበሻ ጽድ እየበዛ ይታያል።

ደኑ በብዙ ዛፎች የተሸፈነ ቢሆንም የዛፎቹ የውፍረት መጠን ግን ዝቅተኛ ነው። ይህም የደኑን መጎዳት ያመለክታል። ለዚህም ዋና ምክንያቱ የውፍረት መጠናቸው ከፍተኛ የሆኑ ዛፎች በተለያየ ጊዜ ለግንባታና ለእንጨት ኢንዱስትሪ መመንጠራቸው ነው። በዚህም ከ40 እስከ100 ሴንቲሜትር ደያሜትር ውፍረት ያላቸው ዛፎች የምንጠራውና የቆረጣው ሰለባዎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ያረጁ ዛፎች መውደቃቸውና አልፎ አልፎም እየደረቁ በመጥፋት ላይ መሆናቸውን መረጃዎች ያሣያሉ።

የአበሻ ጽድ፣ ኮሶ፣ ወይራና ምሳርገንፎ ደግሞ በተፈጥሮም ቢሆን ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረላቸው ለማገገም ይቸገራሉ። ስለዚህ ትኩረት ሰጥቶ በመጠበቅ፣ ለትውልድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሥነምህዳሩን መጠበቅም ሆነ ዘላቂ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል።

(አብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ መስህብ፤2005 ዓ.ም ተሸሲሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የወፍ ዋሻ ጥብቅ ደን በአብዛኛው የተሸፈነው በምን ዓይነት ዛፍ ነው?

ለ. ለምንጠራ የሚመረጡት ዛፎች ምን ያህል ውፍረት ያላቸው ናቸው?

ሐ. የወፍ ዋሻ ጥብቅ ደን ከባሕር ወለል በላይ ስንት ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል?

መ. ከአስታና ከአበሻ ጥድ የትኛው ነው የበለጠ ቀዝቃዛ በሆነ አካባቢ የሚበቅል?

ሠ. የወፍ ዋሻ ጥብቅ ደን በብዛት የሚገኘው በየትኛው ወረዳ ነው? የስንት ቀበሌዎች አካል ነው?

ረ. የወፍ ዋሻ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ከ1994 — 2005 ዓ.ም. ምን ያህል ሄክታር ቀንሷል? ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?

ሰ. በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል ሄክታር የሚቀንስ ይመስላችኋል?

ሸ. ከአጠቃላይ የደኑ ሽፋን ተቆራርጦ የሚገኘው ደን ስፋት ምን ያህል ይሆናል?

አቀላጥፎ ማንበብ

“የተፈጥሮ ደን መመናመን” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

6.1.2 ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ያላቸው ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ሀ. ጥብቅ	ሠ. መመንጠር	ቀ. የተቆራረጡ ደኖች
ለ. ወጣገባ	ረ. አዋሳኝ	በ. ሥነምህዳር
ሐ. ሸለቆ	ሰ. ስምጥ ሸለቆ	
መ. ተፋሰስ	ሸ. የተራራ ሰንሰለት	

2. የሚከተሉትን ቃላት ምን ዓይነት እፅዋት እንደሚወክሉ ከመዝገበቃላት በማየት ወይም ሰው በመጠየቅ አስረዱ።

ሀ. ጓሣ	ሠ. ፅድ	ቀ. ዝግባ
ለ. ጅብራ	ረ. ኮሶ	በ. እምብስ
ሐ. ጦስኝ	ሰ. አምጃ	ተ. ወይራ
መ. አስታ	ሸ. ዋንዛ	ቸ. አጣጥ

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም "ተማሪ" በሚል ርዕስ ከፍተኛ የመማር ፍላጎት ያላቸውን ዝቅተኛ የመማር ፍላጎት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በማወዳደር አወዳዳሪ ድርሰት ጻፉ።



6.1.3 ማዳመጥ

እሮሮ

ቅድመማዳመጥ

“እሮሮ” በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ግጥም መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የመጀመሪያውን አንጓ ወይም ስታንዛ መልዕክት አብራሩ።

ለ. “አንተ የምትለቀውን ካርቦንዳኦክሳድ በርትቼ በዋጥኩኝ፣ ኦክስጂን ተንፍሼ
አየርክን ባደስኩኝ፣”

ከሚሉት የአየር ልውውጥ ስንኞች ተነስታችሁ በሰዎችና በዕፅዋት መካከል ያለውን መስተጋብር አስረዱ።

ሐ. የዓለም የአየር ሙቀት ሚዛን ጠባቂ ማነው?

መ. በግጥም እሮሮ ያቀረበው ማን ነው? ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. እሮሮ አቅራቢው “መመስገን ነበረብኝ” ያለው ምን ስላደረገ ነው? ትስማማላችሁ?

ረ. “የእኔ ሞት ያንተ ሞት መሆኑ እንዴት ጠፋህ?” የሚለውን ስንኝ ሐሳብ አብራሩ።

ሰዋስው

ሦስት አወንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፡-

አወንታዊ፡- መስከረም ለነፃነቷ ቀናኢ ናት።

አሉታዊ፡- ዳምጠው ወታደር አይደለም።

መጠይቃዊ፡- ዘይነባ መቼ መጣች?

ቅድመንባብ

ሥዕሉንና ርዕሱን አይታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ቁጭት



የተወለድኩት ረባዳማ ቦታ ላይ በምትገኝ አነስተኛ መንደር ነው። ከመንደሯ በቅርብ ርቀት አነስተኛ ጫካ ነበር። ድሮ በጫካው ውስጥ የግራር፣ የዝግባ፣ የሾላና የዋርካ ዛፎች ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ ከቤታችን ወጥተን ድብብቆሽ የምንጫወተውና ፍራፍሬ ለቅመን የምንበላው ከዚሁ ጫካ ነበር።

በጊዜው በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች የመብራት ተጠቃሚ አይደሉም፤ ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙት በእንጨትና በከሰል ነው። ቤት ለመሥራት ከእንጨት ሌላ አማራጭ የላቸውም። ኗሪዎቹ የተለያዩ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ጫካውን መነጠሩት። ለቤት መስሪያ፣ ለማገዶ፣ ለተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መስሪያ በሚል ጫካውን ጨፈጨፉት። በዚህም የተነሳ አካባቢው እየተራቆተ መጣ። በተለይም የከሰል አክሳዮች የዕለት ተዕለት የጭፍጨፋ ተግባር ሁኔታውን ይበልጥ አባበሰው።

ይህ ተወልጄ ያደግኩበት ቦታ፣ ጫካው ስለተመነጠረና አካባቢው ስለተራቆተ አፈሩ በጎርፍ መታጠብ ጀመረ። የእርሻ መሬቶች የተፈለገውን ምርት መስጠት አቆሙ። በዚህ የተነሳ የአካባቢው ነዋሪዎች ለረሃብና ለድህነት ተዳረጉ። ቤተሰቦቹ ሲሰቃዩ ዝም ማለት ያልቻለው ጓደኛዬ፣ ሥራ ፍለጋ ወደሌላ አካባቢ ሄዶ ሳይመለስ ቀረ። ይህን ሁኔታ ከልጅነቴ ጀምሮ እያስተዋልኩ አደግኩ።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩት እዚያው ባደግኩበት አካበቢ በሚገኝ ትምህርትቤት ነው። የኹለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩት ግን ከቤተሰቦቼ በቅርብ ርቀት በምትገኘዋ የወረዳ ከተማ ነበር። ከትምህርቴ ጎን ለጎን ቤተሰቦቼን በሥራ አግዝ ነበር። ሆኖም ወላጆቼ ለፍተው የሚያገኙት ምርት እየቀነሰ ሄደ። ይህም የሆነው በአፈሩ መራቆትና ለምነት ማጣት እንደሆነ ተረድቻለሁ። ስለዚህ ወደፊት በምማረው ትምህርት፣ አካባቢዬን መለወጥ እንዳለብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ።

በዚህ ሁኔታ እያለሁ የ12ኛ ክፍል ፈተናዬን ተፈትኜ ወደዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ጥሩ ውጤት አስመዘገብኩ።

ከነበረኝ ቁጭት በመነሳትም የደን ልማት ትምህርት ለመከታተል ወሰንኩ። በዚህም የወንዶገነትን የደን ኮሌጅ በአንደኛ ደረጃ መረጥኩ። በምርጫዬ መሠረት በመመደቤ ደስተኛ ሆንኩ። ትምህርቴን ተግቼ በማጥናት በደን ልማት የመጀመሪያ ዲግሪዬን ተመርቄ በግብርና ሚኒስቴር ውስጥ የደን ልማት ባለሙያ ሆኜ ተመደብኩ።

በሥራ ዓለም እያለሁ የተለያዩ የውጭ ሀገሮችን የመጎብኘት እድል አገኘሁ። ሁሉም የጎበኟቸው ሀገሮች አረንጓዴ ለብሰው፤ ስመለከት የመንፈስ ቅናት አደረብኝ። ስለኢትዮድያ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያቀነቀኑ የጥበብ ሰዎች፣ በፈጠራ ሥራዎቻቸው አሁን ያለውን እውነት በትክክል አለማንፀባረቃቸውን ተረዳሁ። በርግጥ ኢትዮድያ በቀደሙት ጊዜያት በደን ሀብት የታደለች እንደነበረች ከታሪክ ብረዳም ሀብቷንና ልምላሜዋን ጠብቆ ለማቆየት አለመቻሉ አበሳጭቶኛል።

በዚህ በመቆጨት በተወለድኩበት አካባቢ ያሉ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ስለደን ልማት አካባቢ ጥበቃ ለማስተማር በቀበሌው አስተዳድር አማካይነት ሰበሰብኳቸው። ተሰብሳቢዎችም በተባለው ጊዜና ቦታ ተገኙ። ለመንደሬ ነዋሪዎች የመጣሁበትን ዓላማ በማስተዋወቅ ማስተማር ጀመርኩ። “ቀደም ሲል አካባቢያችን በደን የተሸፈነ፣ ምርታችን የተትረፈረፈ እንደነበር አያቶቻችንና አባቶቻችን እያጫወቱን አድገናል። አሁን ግን በእኛ በልጆቻቸውና በልጅ ልጆቻቸው ደኖች እየተጨፈጨፉ፣ የደን ሽፋኑ እየቀነሰ በመምጣቱ አፈሩ ተራቆተ። ተለፍቶ ተደክሞ የሚገኘው ምርትም ከዕለት ወደዕለት እየቀነሰ መጣ። በየጊዜው ይጥል የነበረው ዝናብም በመጥፋቱ አካባቢው በድርቅ መመታት ጀመረ። ለዚህ ሁሉ መነሻው በአካባቢያችን ያሉትን ደኖች መጨፍጨፋችንና ተዳፋት ቦታዎችን ሳይቀር ማረሳችን ነው” በማለት ገለፃዬን ጨረስኩ። ተሰብሳቢዎችም ሀሳቤን አጠናከሩት።

በመጨረሻም የወደሙትን ደኖች መልሶ ማልማት እንዳለባቸው አመኑ። “የጥፋቱ መነሻ እኛ በመሆናችን አካባቢያችንን በመንከባከብ፣ ጥብቅ ደኖችን በመጠበቅና መልሶ በማልማት፣ የሳር ቦታዎችን ከከብቶች ንክኪ ነፃ በማድረግ አካባቢውን ወደድሮ ይዞታው እንመልሳለን” በማለት ቃል ገቡ። እኔም ሀሳቤ ተቀባይነት በማግኘቱ ደስተኛ ሆንኩ። የአካባቢው ማህበረሰብም አካባቢያቸውን በልማት “ቁጭቴን በልጄ ተወጣሁ” የሚሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ።

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ 8ኛ ክፍል፤ የመምህር መምሪያ (2007)። ገፅ 85-86 ተሸሽሎ የተወሰደ።)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የደን አገልግሎቶችን ዘርዝሩ።

ለ. የሰዎች ፍላጎት ከደን ጋር ያለውን ግንኙነት አብራሩ።

ሐ. "የጥፋቱ መነሻ እኛው ስለሆን የመፍትሔው አካል እኛው መሆን አለብን።" የሚለውን አብራሩ።

መ. ሰው ደንና አፈር ያላቸውን ሰንሰለታዊ ቁርኝት አስረዱ።

ሠ. "ሰውን ለረሀብና ለድህነት የሚዳርገው ራሱ ሰው ነው" የሚለውን ሐሳብ ከምንበቡ ሐሳብ ጋር እያገናዘባችሁ አስረዱ።

ረ. "ስለኢትዮድያ ልምላሜ ያዜሙ የጥበብ ሰዎች አሁን ያለውን ተጨባጭ እውነታ አያንፀባርቁም" ሲባል ምን ማለት ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

"ቁጭት" በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

6.2.2 ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተዳፋት	መ. ተግቼ	ሰ. እየተበራከተ
ለ. ቁጭት	ሠ. ተደረገ	ሸ. ረባዳማ
ሐ. ጠብቆ	ረ. የተነሳ	

2. በ"ሀ" ረድፍ ላሉት ተዛማጅ ቃላትን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ቃል	ሀ. አደረብኝ
2. መልሶ	ለ. ሸፋን
3. የደን	ሐ. ገባሁ
4. ቅናት	መ. ታጠበ
5. በጎርፍ	ሠ. ማልማት

3. የሚከተሉት ሐረጎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ደኖች ተጨፈጨፉ፣ መ. የጥበብ ሰዎች

ለ. መሬት ተራቆተች፣ ሠ. በሥራ ዓለም

ሐ. በድርቅ ተመታ ረ. በቅርብ ርቀት

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም በችግርና መፍትሔ ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።



6.2.3 መናገር

በቡድን ተመዳድባችሁ፣ አንዳችሁ ስለደን ጭፍጨፋና ጉዳት፣ አንዳችሁ ስለደን መልሶ መልማትና ጥቅም በመዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

ሰዋስው

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም የተለያዩ መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፦



ሀ. መስከረም መጣች?

ለ. መስከረም መቼ መጣች?

ሐ. መስከረም ለምን መጣች?

መ. መስከረም እንዴት መጣች?

ሠ. መስከረም ከማን ጋር መጣች?

ረ. መስከረም በምን መጣች?



ሀ. _____

ለ. _____

ሐ. _____

መ. _____

ሠ. _____

ረ. _____

6.3.1 አንብቦ መረዳት

ጥሪ

ቅድመንባብ

ርዕሱን ተመልክታቸሁ ስለግጥሙ ገምቱ።

ጥሪ

ተራራው፣ ሸለቆው፣ ጋራው ሸንተረሩ፣
የሰው ቀልብ ሚስበው ነፋሻው አየሩ፣
ዛሬ በእኛ ጊዜ ምነው መቀየሩ?
የዱር እንስሳቱ የኖረው በተስፋ፣
ዛሬ ተሰደዱ ሁሉም ጥሎ ጠፋ።
ለሀገር ሀብትነት ምንጭ እንዳልነበሩ፣
መጠጊያ ጠፍቷቸው ጮኸው ቢያማርሩ፣
አቤት ባይ አጡና ጥለውን በረሩ።
ደኑ ተጨፍጭፎ መጠለያ ቢያጡ፣
ስንት የዱር እንስሳት፣ ስንት አዕዋፋ ሞቱ?
ምን ያደርጋል እንጂ ቁጥር መዘርዘሩ፣
ሚዳቋ፣ ድኩላው፣ ባለአራት እግሩ፣
ባገራችን ጫካ ስንት እንደነበሩ፣
በእሪታ በጩኸት ሄዱ እያማረሩ።
በአየሩ መዛባት፣ በፀሐይ ሰቆቃ፣
የሰው ልጅ መኖሪያ ተቃርቧል ሊያበቃ፣
ትንሽ ቀን ቀርቶናል ከቀንም ደቂቃ።
ደናችን ሲወድም ሳናውቅ እንደአዋቂ፣
ማነው ተጠቃሹ? ማነው ተጠያቂ?
ሀገር በበረሃ እንደስብ ሳትቀልጥ፣
ወገን ለደን ልማት እንትጋ እንሯሯጥ።

ከማሩ ጀምሮ ብንሄድ እስከሰሙ፣

ከደን አበባ ነው ንቦቹ ሚቀስሙ።

ይሄን ሁሉ ጥቅም አየነው በዋላ፣

አይጨፍጨፍ ደኑ ወገን አደብ ግዛ።

ለራሳችን ችግር እኛ እንፍጠር መላ፣

በበረሃ ንዳድ፣ በሳት ሳንበላ፣

ሁሉም በየቤቱ አስር ችግኝ ያፋላ።

ሁሉም ችግኝ ተክሎ ዉኃውን ካጠጣ፣

የምን በረሃነት የምን ሙቀት መጣ።

ትሽፈን በደኑ ኢትዮድያ ሀገሬ፣

አይጠቅምም ቀጠሮ እንጀምር ዛሬ።

(ዋለልኝ። (2001 ዓ.ም)። መቅረዝ፤ ገጽ 202፣ ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የመጀመሪያዎቹን ሦስት ስንኞች ሐሳብ በጽሑፍ ግለጹ።

ለ. ለሀገራችን የዱር እንስሳት መመናመን ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ተጠያቂውስ ማን ነው?

ሐ. በስደት ምክንያት ያጣነው የሀገር ሀብት ምንድን ነው? ይህን ሀብት ላለማጣት ምን መደረግ ያለበት ይመስላችኋል?

መ. “በአየሩ መዛባት በፀሐይ ሰቆቃ፣

የሰው ልጅ መኖሪያ ተቃርቧል ሊያበቃ፣

ትንሽ ቀን ቀርቶናል ከቀንም ደቂቃ።”

የሚሉትን ስንኞች መልዕክት በሦስት ዓረፍተነገር ጻፉ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ጥሪ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

6.3.2 ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

መቀየር	መጠጊያ	ሰም	መላ
ሸንተረር	መዛባት	ዋዛ	ፈላ
ጥሎ	ሰቆቃ	አደብ ገዛ	ቀጠሮ

ሀ. ደበበ ጧት ጧት ልብስ _____ ይወዳል።

ለ. የኢትዮጵያ መልክዓምድር ተራራ፣ ሸለቆ፣ _____ ይበዛበታል።

ሐ. በጣም ስለቸኮለ ስልኩን _____ ሔደ።

መ. ደኖች ከተመናመኑ ወፎች _____ ያጣሉ።

ሠ. የአየር ንብረት _____ በሰዎችና በእንሰሳት ላይ ጉዳት ያደርሳል።

ረ. ድመቷን በድንጋይ ሲመታት የ_____ ድምፅ አሰማች።

ሰ. ጧፍ ከክርና ከ _____ ይሠራል።

ሸ. በቁምነገር _____ ፈዛዛ የለም።

ቀ. ስብሰባ ላይ ልክልኩን ሲነግሩት _____።

በ. አሁን የሚያስፈልገው ለችግሩ _____ መፈለግ ነው።

ተ. አባቱ ድንገት ስለደረሱበት “ጉድ _____” አለ።

ቸ. ከጓደኛዬ ጋር የቤት ሥራ ለመስራት _____ ይዘናል።

መጻፍ

በ6.1.2 በተሰጠው የመጻፍ ተግባር “ተማሪ” በሚል ርዕስ በማወዳደር ስልት የጻፋችሁትን አወዳዳሪ ድርሰት ከልሳችሁ ጻፉ።

ማስታወሻ

የድርሰት መገምገሚያ (ማረሚያ) መስፈርት

ሀ. ርዕስ ጠብቆ መጻፍ፣

ለ. የአንቀጹን ዋና ሐሳብ በግልጽ ማሳየት፣

ሐ. ዋናውን ሐሳብ በተገቢ መዘርዝሮች መግለጽ፣

መ. ሐሳብን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት፣

ሠ. ቃላትን በአግባቡ መጠቀም፣

ረ. አንባቢዎች ሊረዷቸው የሚችሏቸውን ዓረፍተነገሮች መጠቀም፣

ሰ. የተሟላ ዓረፍተነገር መጠቀም፣

ሸ. የሐሳብ ፍሰቱን ጠብቆ መጻፍ፣

ቀ. ተገቢ ሥርዓተነጥብን በተገቢው ቦታ መጠቀም፣

በ. የሐሳብ አንድነትና ግጥምጥምነት ያላቸው አንቀጾች ማዋቀር።

6.3.3 መናገር

1. በጽሑፍ ቅድመዝግጅት አድርጋችሁ የንብንና የታታሪ ሴትን ባሕርያት በማወዳደርና በማነጻጸር ንግግር አድርጉ።

2. የሚከተሉትን ግጥሞች ሐሳብና በቅርቡ በአገራችን በጦርነት የደረሰውን ውድመት እያነጻጸራችሁ ስለጦርነት አስከፊነት ንግግር አድርጉ።

   ሀ. አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፣

   አቃጥሎ ለብልቦ አንድዶ ይፍጃችሁ።

   ለ. ዘወር ዘወር ብላ አየችው ቀሚሷን፣

   ረሳችውና ባፈር መለወሷን።

   ሐ. ሞጣ ቀራኒዮ ምነው አይታረስ፣

   በሬሳ ላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚያ ድረስ።

ሰዋስው

የሚከተሉትን መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ወደአወንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ለውጣችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

መጠይቃዊ፡- ካሣ መቼ ወደቡሬ ይሄዳል?

አወንታዊ፡- ካሣ ነገ ወደቡሬ ይሄዳል።

አሉታዊ፡- ካሣ ነገ ወደቡሬ አይሄድም።

ሀ. ካሳ ስንት ጊዜ ወደቡሬ ይሄዳል?

ለ. ካሳ ወደቡሬ እንዴት ይመጣል?

ሐ. መሠረት ደብዳቤ በምን ትጽፋለች?

መ. መሠረት መቼ ደብዳቤ ትጽፋለች?

ሠ. ዛፏ ለምን ወደባሕር ዳር ትሄዳለች?

ምዕራፍ 7 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ

7.1.1 አንብቦ መረዳት

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስኤዎች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ሕፃናት ምን ምን ሥራ ይሠራሉ? ለምን ያህል ስዓት? ሥራው ከአቅማቸው በላይ ነው?

ለ. ከርዕሱ ተነስታችሁ የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስኤዎች



የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከሕፃናት ሥራ ይለያል። የሕፃናት ሥራ፣ ህፃናቱ በቤተሰብ ድጋፍ ቀላል ሥራን የሚለማመዱበትን፣ ትምህርታቸውን፣ ጤንነታቸውንና እድገታቸውን በማይፈታተን መልኩ የሚሠሩትን ይመለከታል። ይህም ማኅበራዊ ሕይወትን በማሻሻል የሥራ ፍቅር ኖሯቸው እንዲያድጉ የማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ግን ሕፃናት እድሚያቸው ለሥራ ሳይደርስና ጉልበታቸው ሳይጠነክር ያለምንም እገዛና ስልጠና በግዳጅ የሚያከናውኑት ተግባር ነው።

በኢትዮጵያ በርካታ ሕፃናት እጅግ አደካሚ፣ አሰልቺና ከባድ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። ከሥራዎች ከባድነት በተጨማሪም

ሕፃናት ለረጅም ስዓታት ያለረፍት እንዲሠሩ ይገደዳሉ። ለሠሩበትም ተመጣጣኝ ክፍያ ያለማግኘታቸው የጉልበት ብዝበዛውን ከፍ ያደርገዋል። ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ ከሚያጋልጧቸው ምክንያቶች መካከል ድህነት፣ የወላጆች የተዛባ አመለካከትና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ይጠቀሳሉ።

ድህነት ለሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ አንዱ ምክንያት ነው። ድህነት ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ወላጆች፣ የልጆችን የምግብ፣ የልብስና የመሳሰሉ ፍላጎቶችን አሟልተው የማሳደግ አቅም ያጣሉ። በዚህ የተነሳ ለልጆቻቸው የተሻለ ሕይወትን በመመኘት ሌላ አማራጭ ያማትራሉ። “ልጄን ያስተምሩልኛል፤ ሥራ ያለማምዱልኛል” በማለትም ልጆቻቸውን ለዘመድም ሆነ ለባዕድ አሳልፈው ይሰጣሉ። ህፃናቱ ግን የታሰበውን የትምህርትና የስልጠና ዕድል በማግኘት ፈንታ፣ ለከፍተኛ የስራ ጫናና ጉልበት ብዝበዛ ይጋለጣሉ። በሌላ መልኩም ህፃናቱ በራሳቸው ተነሳሽነት፣ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከወላጆቻቸው በመነጠል ወደሌላ አካባቢ ይሰደዳሉ። በደረሱበት ቦታም ሕይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ አቅማቸውን በማይመጥንና ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በሚጥል ሥራ ለመሠማራት ይገደዳሉ።

የወላጆች የተዛባ አመለካከት ሌላው ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርግ ጉዳይ ነው። ወላጆች ለሕፃናት አስተዳደግ ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው። ሕፃናትን በጥሩ ሥነምግባር አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት ለህፃናቱም ለወላጆችም ይጠቅማል። ሆኖም አንዳንድ ወላጆች ሀላፊነታቸውን ከመወጣት ይልቅ ልጆቻቸውን ወደሌላ ቦታ በመላክ በጉልበታቸው ለመጠቀም ይፈልጋሉ። ህፃናቱም በወላጆቻቸው ግፊትና ተፅዕኖ ወደአልፈለጉበት ሕይወት ይሰማራሉ። በማይችሉት ሥራ ላይ በመሠማራትም ለከፍተኛ ችግርና ስቃይ ይዳረጋሉ። ከቤተሰብ ተነጥለው በመኖራቸው ለብቸኝነት ይጋለጣሉ። እንደሕፃናት ተጫውተው ባለማደጋቸው ደስታና ፍቅር ይርቃቸዋል። ሠርተው ወላጆቻቸውን መርዳት ቀርቶ ለራሳቸውም ለብሶና በልቶ ለማደር ይቸገራሉ። በየጊዜው በሚፈፀምባቸው ጥቃትና የሥራ ጫና መንፈሳቸውና አካላቸው ይጎዳል። በመጨረሻም ለቤተሰቦቻቸውም ሆነ ለሀገራቸው ሸክም ይሆናሉ።

ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዋና ምክንያቶች ናቸው። ሕፃናትን በማታለል ወይም በመስረቅ ከቤተሰቦቻቸውና ከትውልድ መንደራቸው በማሰኮብለል በግል ፍላጎታቸው መጠቀሚያ ያደርጓቸዋል። አንዳንዶቹን ሕፃናት በሌሎች ቤት በማስቀጠር የጉልበታቸውን ዋጋ በመቀበል ኑሯቸውን ይመራሉ። ሌሎቹን ደግሞ በራሳቸው ቤት ሸሽገው ለረዥም ሰዓታት ያሠሯቸዋል። ሰዓት ጠብቀው ምግብ አያቀርቡላቸውም፤ ቢሰጧቸውም ለድካማቸው የሚመጥን

አይደለም። በዚህም አካላቸው ይጎዳል። አንዳንድ ሕፃናት የሸማ ስራ እንዲሰሩ ይደረጋሉ።

የሕፃናት ጉልበት ከሚበዘበዙባቸው ተግባራት መካከል አንዱ የሸማ ሥራ ነው። የሸመና ሥራ በብዛት በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ሕፃናት ሸመና እንዲሠሩ ይደረጋሉ። በዚህ ሥራ የተሠማሩ ሕፃናት በሰዎች አዘዋዋሪዎች ለብርቱ ችግር የተጋለጡ ናቸው። እነዚህ ሕፃናት ለረኽርም ሰዓታት በጠባብ ክፍል ውስጥ ጥበብ ልብሶችን ይሠራሉ። ሥራው ረፍት የማይሰጥ በመሆኑ የፀሐይ ብርሃን ሳያገኙ ይውላሉ። አቀርቅረው ስለሚውሉ አጥንታቸው ይጎዳል፤ ዓይናቸው ይደክማል፤ በእነዚህና ሌሎች ተደራራቢ ችግሮች የተነሳም መላ ጤንነታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል።

በአጠቃላይ ለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚያጋልጡ መንስኤዎች ድህነት፣ የወላጆች የተዛባ አመለካከትና የህገወጥ ደላሎች ናቸው። ይህ ደግሞ ሀገር ተረካቢ በሆኑ ሕፃናት ላይ የአካልና የሥነልቡና ጉዳት ያደርሳል። ሕፃናት በእንክብካቤ ማደግ ሲገባቸው ይጎሳቆላሉ፤ የትምህርት እድል ይነፈጋቸዋል። በደስታና በፍቅር ስለማያድጉ ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ደካማ ይሆናል። ለራሳቸው፣ ለወላጆቻቸውና ለሀገር እድገት አስተዋፅኦ የማድረግ አቅማቸው ይዳከማል ወይም ይጠፋል።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ የሚያጋልጡ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ጥቀሱ፤ በሕፃናት ሕይወት ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ አብራሩ።

ለ. “በተለያየ ተፅዕኖ ሕፃናት አላስፈላጊ ሕይወት ውስጥ ይገባሉ” ሲል አላስፈላጊ ሕይወት የተባለው ምንድን ነው?

ሐ. በሕፃናት ሥራና በሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

መ. የወላጆች የተዛባ አመለካከት የተባለው ምንድን ነው? በሕፃናት ላይ ምን ያስከትላል?

ሠ. ድህነት በሕፃናት ሕይወት ላይ ያለውን ተፅዕኖ አብራሩ።

ረ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስኤዎች” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

7.1.2 ቃላት

1. በ“ሀ” ረድፍ የቀረቡትን ቃላት/ሐረጋት ይበልጥ ከሚቀርቧቸው የ“ለ” ረድፍ ቃላት/ሐረጋት ጋር አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ለሥራ	ሀ. ክፍያ
2. ጉልበታቸው	ለ. ጫና
3. ተመጣጣኝ	ሐ. ሳይጠነክር
4. የሥራ	መ. ማደር
5. በልቶ	ሠ. ሳይደርሱ
	ረ. ዋጋ

2. በ“ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ”ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. መንፈሳቸው	ሀ. ማሳመን
2. ባዕድ	ለ. ፈቃድ
3. ማታለል	ሐ. መዋል
4. አቀርቅረው	መ. አካላቸው
5. ብርሃን	ሠ. ዘመድ
6. ማደር	ረ. ተመጣጣኝ
7. ጠባብ	ሰ. ጨለማ
8. ግዳጅ	ሸ. ሰፊ
	ቀ. ቀና ብለው

3. ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ባዶ ቦታውን አሟሉ።

ብዝበዛ	አሰልቺ	ግፊት	ጥቃት	አድካሚ
መትጋት	ከባድ	ይዘፈቃሉ	እርምጃ	መረጃ

በህገወጥ ደላሎች _____ ሕፃናት አላስፈላጊ ሕይወት ውስጥ _____። ከአቅማቸው በላይ _____፣ _____ እና _____ ሥራ እንዲሠሩ ይገደዳሉ። በአሠሪዎቻቸው የተለያየ _____ ይደርስባቸዋል። ይህ ሁሉ _____ ቢኖርም መንግሥት _____ ወስዶ ይህንን አስከፊ የሕፃናት ጉልበት _____ ማስቆም አልቻለም። ስለዚህ መንግሥትም ሕዝብም ሕፃናትን ለመታደግ _____አለባቸው እንላለን።

መጻፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም "የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች" በሚል ርዕስ በዋናና መዘርዝር ስልት ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችሉ ሐሳቦችን አስፍሩ።

ርዕስ

መግቢያ

የአንቀጽ አንድ ዋና ሐሳብ

ዝርዝር ሐሳቦች _____

_____

_____

የአንቀጽ ኹለት ዋና ሐሳብ

ዝርዝር ሐሳቦች _____

_____

_____

የአንቀጽ ሦስት ዋና ሐሳብ

ዝርዝር ሐሳቦች _____

_____

_____

የአንቀጽ አራት ዋና ሐሳብ

ዝርዝር ሐሳቦች _____

_____

_____

ማጠቃለያ

ዝርዝር ሐሳቦች _____

_____

_____

_____

7.1.3 ማዳመጥ

ስጦታ

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ስጦታ ተቀብላችሁ ወይም ሰጥታችሁ ታውቃላችሁ?

ለ. “ስጦታ” ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምታዳምጡት ምንባብ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. “አጎቱ ገንዘብ ነፍሱ ነው” የሚለውን ሐሳብ በአጭር ግለጹ።

ለ. “አጎቱ ምን ሆኖ ነው የሚያነክሰው?”

ሐ. “የስጦታ ነገር እንደኩፍኝ በልጅነቱ ነው የወጣለት” የሚለውን አባባል አብራሩ።

መ. ምን ዓይነት ዘመዶች ናቸው በስጦታ ተቀባዩ አንደኛ ደረጃ የተሰጣቸው?

ሠ. ስጦታ ተቀባዩ ልጅ ለሰጦታ ሰጭዎች በሰጣቸው ደረጃ ትስማማላችሁ? ለምን? አብራሩ።

ረ. ባለታሪኩ ስጦታ ሲቀበል እናትዬዋ ለምን በሳቅ ፍርስ አሉ?

ሰ. የስጦታ ተቀባዩ ልጅ ቤተሰቦች ምን ዓይነት የኑሮ ደረጃ ያላቸው ይመስላችኋል?

ሰዋስው

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም በተውሳከግሳዊ ቃላት ዐምስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፦



ምን ይሻላል?

ቅድመንባብ

ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምንባቡ ገምቱ።

ምን ይሻላል?

አሁንስ መረረኝ። ገና በአሥር ዓመቴ የሃያ አመት ሰው የሚሠራውን ስለምሠራ ቤቱ አስጠልቶኛል። አጎቴና እትዬ ራቅ ያለ መስሪያቤት ውስጥ የመንግስት ሠራተኞች ናቸው። ስለእኔ ድካም ምንም አያውቁም፤ ሁሉንም ሥራ ለእኔ ትተውታል። የቤቱ ሥራ ትምህርቴን በተገቢው እንደላጠና አድርጎኛል። ወላጆቼ ከዘመድ ቤት ያስጠጉኝ እንድማር ነበር።

እትዬም ከሥራ ስትመለስ "ሚሚ ያንን ትልቅ በርሚል እያንከባለለሽ ቧንቧው ላይ ደቅኚው" ስትለኝ በርሚሉን አንከባልዬ ዉኃ እቀዳለሁ። "ሚሚ ዕቃዎችን እጠቢ፤ ቤት ወልውዪ፤ የልጆችን ልብስ እጠቢ፤ አልጋ አንጥፊ..." የሚባሉ ትዕዛዞች ለእኔ የዘወትር ተግባራት ናቸው።

የምትሰጠኝ የሚበላ ነገር አጥግቦኝ አያውቅም። "ምን ይሻለኛል? ከሁሉም የሚያናድደኝ ልጆች እቃ ቤት ገብተው የፈለጉትን በልተው በእኔ ሲመካኝ ነው። ስንት ቀን የተቀመጠ ማርና ስኳር ልጆቹ ሲልሱ እያየኋቸው፣ "ማን ጨረሰው?" ሲባሉ እንደተለመደው በእኔ ያመካኛሉ። እኔ አይደለሁም፤ ብልም እንኳን መደብደቤ አይቀርም። ልጆች በሰረቁ ቀን እኔ እራሴን ለዱላ አዘጋጃለሁ። እንዲያው ምን ይሻላል?

አሁን አሁን ብዙ ነገር እያሰብኩ ነው። ጠፍተሽ ሂጂ የሚል ሐሳብ መጥቶብኛል። ፈልገው እንኳን ቢያገኙኝ ተፀፅተው ሊንከባከቡኝ ይችላሉ። ግን በመንገድ ችግር ቢደርስብኝስ? የሚል ፍርሃት ተሰሞቶኛል። የምሰማው ዜና ሁሉ "በሕፃንነቷ አስገድዶ ደፈራት" የሚል ነው። እኔ ደግሞ ይህ ነገር ያስፈራኛል።

ብቻ አይድረስ ነው! ልጆችም ይህ አያሳስባቸውም፤ እትዬ "ቡታጋዙን አያይገርው" ስትለኝ ሁልጊዜም እፈራለሁ። እምቢ እንዳልላት ትገርፈኛለች ብዬ እፈራለሁ። ስትጋረፍ ጨካኝ ናት። አምናም ዘንድሮም ያመጣሁት ውጤት ዝቅተኛ ነው። አምናና ታች አምና እንደዘንድሮው አንደኛ ክፍል ነበርኩ። በዚህ ዓይነት ዘንድሮ አላልፍም። ክፍል ቁጭ ብዬ ትዝ የሚለኝ አሁን ስንለቀቅ እትዬ ምን ታዝዘኝ

ይሆን? የሚለው ነው። አስብ አስብና ከአቅሜ በላይ የምሸከመውና የምሠራው ነገር ይታየኛል።

ጎረቤታችን እትዬ አልታዬ ሁሌ ባገኙኝ ቁጥር "ምነው ከሣሽ? ደግሞ ጠቋቆርሽ! እቤት እህል አይሰጡሽም?" ይሉኛል። "አረ በደንብ ነው የምበላ!" እላቸዋለሁ፤ ሁሉንም ደብቄ። ዛሬ ግን ሁሉንም ይወቁት፤ ነግሬያቸው ካልሰሙኝና መኪና ካገኘሁ ለምኜ ከዚህ ቤት መጥፋት ነው። አሁን ወደእትዬ አልታዬ ልሂድ። በራፉም ክፍት ስለሆነ ሳልፈራ ልንገራቸው። ምን ይሻላል? መጥፋት ወይስ መናገር? እያሰብኩ ገባሁ። የሆነው ይሁን በማለት በራቸውን በቀስታ አንኳኩቼ ገባሁ።

"እንደምን ዋልሽ ሚሚ? ምነው የፈራሽ ትመስያለሽ ልጄ?"

"አይ አይደለም እ... ግን ፈርቻለሁ እንዴ?"

"በቀኑ ምን አስፈራሽ?"

"እርሰዎም ሕፃን ስለሆንኩ አያምኑኝም ብዬ ነው"

"ምኑን ልጄ? ንገሪኝ እስኪ! ዛሬስ ከሰው ጋር ተነጋገርሽ" አሉኝ።

ዝምተኛ ስለሆንኩ በመናገሬ ተገርመው፤ አይናፋር ያደረገኝ የምናገረውን ሁሉ እትዬ ስለማትቀበለኝ ነው። ስለዚህ ዝም ማለቱን እመርጣለሁ።

"ካለአቅሜ ሥራ ያሠሩኛል፤ ሳልሰርቅ ሌባ ይሉኛል። ስለዚህ ወደዘመዶቼ መሄድ ስለፈለኩ መጓጓዣ፣ ገንዘብ ይስጡኝ ብዬ ነው?" አልኳቸው።

"ምን? ደግሞ ይሄን ማን ነው ያሳሰበሽ። በይ ዝም በዪ እኔ እነግራቸዋለሁ። መጥፎ ሐሳብ ግን አታስቢ! ለኔ በመናገርሽ ደስ ብሎኛል" በማለት አግባቡኝ።

"ሳልነግርዎ ደግሞ፣ ምግብ እስክጠግብ አይሰጡኝም። ጠግቤ በልቼ አላውቅም።"

"እውነትሽን ነው እንዲህ ካደረጉማ በጣም አጥፍተዋል! እንኳን ነገርሽኝ! እኔ እቆጣቸዋለሁ! አሁን ቁጭ በይና እንጀራ ልስጥሽ። ወ/ሮ አንጎቼንም፣ አጎትሽንም ከሥራ ሲመጡ አብራርቼ እነግራቸዋለሁ! አይዞሽ ችግሩ ይፈታል! የዘመድቤት ስለሆነ ጥለሽ መሄድ የለብሽም፣ ይልቅ ትምህርትሽን በርትተሽ ያገኘው..."

"እትዬ አልታዬ ባይነግሯቸው ይሻላል! አልበደልናትም ብለው ቢክዱስ? ያላመኑ እንደሆንስ? ቢገርፉኝስ? በቃ ይተውት አይናገሩ።"

“ኧረግ! በይ ዝም በዪ፤ እናገራለሁ እንጂ! ህፃኗ ስትበደዪ እንዴት ዝም ብዬ እመለከታለሁ? እናገራለሁ!”

“እትዬ አልታዬ! እንደዛሬው ተደስቼ አላውቅም! ከተናገሩልኝ ከስር ቤት እንዳስፈቱኝ ነው የምቆጥረው!”

“ኧረ ችግር የለም ከእስር እንደወጣሽ ቁጠሪው። ካልሆነም ወደቤተሰቦችሽ እመልስሻለሁ፤ አታስቢ”

“እሺ።”

(ቤዛዊት ታምሩ፡- መቅረዝ። 1993። ተሻሽሎ የተወሰደ።)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከዘመድ ቤት የምትኖረው ሕፃን እቃቤት ይቆለፍባታል? እንዴት አወቃችሁ?

ለ. “ልጆች በሰረቁ ቀን ራሴን ለዱላ አዘጋጃለሁ።” የሚለውን የልጅቱን አገላለጽ እንዴት እንደተረዳችሁት አብራሩ።

ሐ. የአሥር አመቷ ልጅ “ልጆችም ይህ አያሳስባቸው” ስትል እነማንን ነው ልጆችም ያለቻቸው? እድሜዋንና አነጋግሯን እንዴት ታዩታላችሁ?

መ. ሕፃኗን እንዳትጠፋ ያደረጋትና ሊደርስብኝ ይችላል ብላ የምትፈራው ችግር ምንድን ነው?

ሠ. ሕፃኗ አንደኛ ክፍል ስንት ጊዜ ደግማለች? ትምህርት የማይገባት ሰነፍ ናት ማለት ነው?

ረ. እትዬ አልታዬ “ደግሞ ይዤን ማነው ያሳሰበሽ?” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

ሰ. ልጆች ዓይን አፋር የሚሆኑት ምን ሲሆኑ ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

“ምን ይሻላል?” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

7.2.2 ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ያላቸው ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ሀ. መረረኝ	ሠ. መጥፋት	ቀ. ስትበደዱ
ለ. ቤቱ አስጠልቶኛል	ረ. መጥፎ ሐሳብ	በ. ያሳሰበሽ
ሐ. የሚበላ ነገር	ሰ. አብራርቼ	
መ. ደብቁ	ሸ. ጨካኝ	

2. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን በድብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።







3. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን በድብተራችሁ አዘጋጅታቸሁ አሚልታችሁ ጻፉ።



መጻፍ

በ7.1.2 "የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች" በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ በሐሳብ ማደራጃ ቢጋር ያስፈራችኋቸውን ሐሳቦች አደራጅታችሁ በዋናና ዝርዝር ስልት ድርሰት ጻፉ።

7.2.3 መናገር

"የሕፃናት ሥራ" በሚል ርዕስ ዋና ዋና ሐሳቦችን በሚከተለው የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር በማደራጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራበተራ ንግግር አድርጉ።

በሕፃናት የሚሠሩ ሥራዎች	በሕፃናት የማይሠሩ ሥራዎች
•	•
•	•
•	•

ሰዋስው

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተውሳከግስ የሆኑ ቃላትን አውጥታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ዓረፍተነገር	ተውሳከ ግስ
ዘርፊ ትናንት ደስተኛ ነበረች።	ትናንት

ሀ. መስፍኔ መላኩ ነገ ወደጋይንት ይሄዳል።

ለ. አዝመራው ሲሳይ ገና ይደሰታል።

ሐ. ዘበርጋ ክፉኛ ተጎሳቁሏል።

መ. ዘሀራ ቶሎ ትመጣለች።

ሠ. ላቀች እንደገና ተሸለመች።

ረ. ፈለጉሽ ዛሬ ከቡሬ መጣች።

7.3.1 አንብቦ መረዳት

ማኅበራዊ ሕይወት

ቅድመንባብ

“ማኅበራዊ ሕይወት ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምንባቡ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ማኅበራዊ ሕይወት

“እማዬ እኔስ እንዲያው እየጨነቀኝ ነው፤ ልቤ በጣም ያዝናል።” “ምኑ ልጄ? ለምንድን ነው ሁልጊዜ በባዶ የምትጨነቀውና ካለዕድሜህ የምታስበው? ቀለብ አትጠየቅ! ልብስ ግዛ አትባል! ልብስ ልግዛ አትል! መጠለያ ቤት ሥራ የሚልህ የለ! የሚገርም እኮ ነው! የዛሬ ልጆች ከዕድሜያችሁ ቀድማችሁ የማያሳስበው ነገር ሁሉ ያስጨንቃችኋል!”

“እናቴ የምጨነቀው እኮ በባዶ ቦታ አይደለም፤ በዓይኔ በእውን ያየሁት በሃሳቤ እየመጣብኝ ነው። እማዬ ትናንት አንቺ ጋር ቁጭ ብለን በቴሌቪዥን ያየነውን ረሳሽው? እረስተሽው ከሆነ ያየነውን ነገር እኔ አንድ በአንድ ዘርዝሬ ልንገርሽ። እንቁራሪቷ እርቧት አድብታ አንዷን ተባይ ይዛ ገና ዋጥ ስታደርጋት፣ ከኋላዋ እባቡ ትንፋሹን በሩቅ ረጨባትና ተዝለፍልፋ ስትወድቅ ተስቦ መጥቶ ብድግ

አደረጋት። ከዚያም ቀስ እያለ ከጭንቅላቷ ጀምሮ እስከ እግሯ ሳያላምጥ ሆዱ ውስጥ አስገባት። ይገርማል!

እባቡ ገና ውጦ እያጣጠመ ሳለ፣ ድመት የመሰለ አውሬ ዘሎ ከጭንቅላቱ ላይ ያዘው። እንደጅራፍ እያወናጨፈ ቀረጣጥፎ በላው። እባቡን የበላው አውሬ ሆዱ በመመላቱ እየተኮፈሰ ሲንጎራደድ፣ ሌላ ደንደሱ ያበጠ አውሬ እየሮጠ መጣበት። እሱም እግሬ አውጭኝ ብሎ ሮጦ ማምለጥ አልቻለም። ግዙፉ አውሬ ዘሎ አንገቱን ሲጥ አድርጎ ገደለው። ከዚያም እያንዘፈዘፈ ወደጫካ ውስጥ አስገብቶ እስከሚጠግብ በልቶ የተረፈውን ሲያስቀምጥ፣ አንበሳ እያነፈነፈ ጠብደሉ አውሬ ወደተኛበት ቦታ መጣ። ጠብደሉ አውሬ የኮቴ ድምጽ ሰምቶ ቀና ብሎ ሲመለከት አንበሳ ጎፈሩን ነስንሶ ወደእሱ ሲገሰግስ አየው። በግዙፋነቱ የተማመነው ጠብደሉ አውሬ የተረፈውን ሥጋ አላሥነካውም፤ እጥለዋለሁ ብሎ በማሰብ ተከምሮ ጠበቀው። ትንቅንቅ ተያያዙ! አቧራው ጨሰ! ከብዙ ግብግብ በኋላ ሆዱ የሞላው ጠብደሉ አውሬ ተረታ። በጀርባው መሬት ላይ ተዘረረ።

አንበሳው ጠብደሉን አውሬ ሆዱ ላይ ጉብ ብሎ አፉ እንደሞላ አካላቱን እየቦጫጨቀ መብላቱን ተያያዘው። ታዲያ እናቴ ይህ ሁሉ ሆድ ለሆድ ጠላት የሆነበት መበላላትና ጭካኔ አያሳዝንም? እኔ እኮ እናቴ ይህን የሚያስፈራራና የሚያሳዝን ነገር ሁሉ የማየው በዚህ ቴሌቪዥን ነው። ይህ ባይኖር እኮ እነዚህን አይቼ አልጨነቅም ነበር። እንዲያው እማዬ! አውሬዎችን አስቀደምኩኝ እንጅ ሰውና ሰው ሲተናነቅ፣ ሲገዳደል ሲቀማማ እያየን አይደለም እንዴ? በተለይ የፈረንጆቹ ፊልም ላይ ሰዎች ከእናቱ ነጥለው ሕፃን ልጅ ሲወስዱ፣ ሕፃን ልጅ የታቀፈች እናት ሲገድሉ አላየሺም? እናትዬ! አንቺ የሕፃኑን እናት ብትሆኚ አታለቅሺም? እኔስ ልክ እንደሕፃኑ እናት አንቺን ቢገድሉብኝ ምንድን ነው የምሆነው? ቴሌቪዥን ከእንግዲህ ወዲያ መግዛትም ሆነ ቤት ውስጥ ማስቀመጥ አያስፈልግም! ፈቃደኛ ከሆንሽ የኛን ቴሌቪዥን ብሰብረው ደስተኛ ነኝ። ከሰይጣን ጋር መኖር ሰይጣን ያደርጋል።"

"ማሙዬ! ቴሌቪዥን ሠይጣን አይደለም። መሰበርም መጣልም የለበትም፤ ከቤት ቴሌቪዥን መኖሩ የሚጎዳው ነገር የለም። በቴሌቪዥን ጠቃሚ የሆነ መልዕክትና ትምህርትም ይሰጣል። አንተ እንደጠቀስከው ጎጂ ምስሎችና ፊልሞችም ይቀርቡበታል። መበላላቱም ፈጣሪ ያዘዘው የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ ነው፤ አንደኛው ሕይወቱን ለማቆየት የግድ ሌላውን መስዋዕት እንዲሆን ያደርጋል። አንተ ሁልጊዜ ሥጋ መብላት ትወዳለህ፤ ባለፈው ዓመት በዓል ሲደርስ አንተን እንደጓደኛ አድርጎ ት/ቤት ስትሄድ ሸኝቶ፣ ስትመጣ ተቀብሎ ልብስህንና አካልህን እያሸተተ ያደገው

ጓደኛህ በጋችን ካልታረደ ብለህ አባትህ አላረደውም? በዕለቱ ዱለቱ፣ አልጫው፣ ጥብሱ፣ ቀይ ወጡ መረቁ... በዓይነት ቀርቦና ዘመድ አዝማዱም ተሰብስቦ በሳቅ በደስታ መብላታችንን ረሳኸው? ይህ ለምን አላሳዘነህም?”

ስለዚህ ያየኸው ሁሉ እንደዚሁ ማለት ነው። አሳቢነትና አሳዛኝነት ያስፈልጋል፣ ከልክ ባለፈ ሐሳብ አዕምሮህን አስታስጨንቅ፤ የአንድም ጉዳይ ጥቅምና ጉዳት፣ ሐቅና ሐሰት ለይተህ ለማወቅ ጥረት አድርግ።”

(አድናን ኡመር፣ መቅረዝ፣ ቁጥር 7 ከገፅ 190 ተሻሽሎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ሕፃኑን ለጭንቀት የዳረገው ምንድን ነው? ከዚህ ወላጆችና ልጆች ምን መማር አለባቸው?

ለ. “ሆድ ለሆድ ጠላት የሆነበት፣ የመበላላት ጭካኔ አያሳዝንም?” የሚለውን የሕፃኑን ንግግር አብራሩ። ንግግሩን ከእድሜው አንፃር እንዴት ታዩታላችሁ።

ሐ. ሕፃኑ ስለቴሌቪዥን ባለው አመለካከት ትስማማላችሁ? ለምን? ምን መሆን አለበት?

መ. “ስለጎጅ ፊልሞች” ያላችሁን አመለካከት ግለጹ።

ሠ. “የአንዱ ሞት ለሌላው ሕይወት ይሆናል” የሚለውን አባባል ከምንባቡ ታሪክ እያጣቀሳችሁ አስረዱ።

ረ. በማሰብና መጨነቅ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ።

ሰ. “በእውን ያየሁት በሀሳቤ እየመጣብኝ” የሚለውን “በእውን ያየሁት በህልሜ እየመጣብኝ” ከሚለው ጋር እያነፃፀራችሁ አብራሩ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ማኅበራዊ ሕይወት” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

7.3.2 ቃላት

1. በ“ሀ” ረድፍ ላሉት ተዛማጅ የሚሆኑትን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. እግሬ	ሀ. ጨሰ
2. ስምንተኛው ሽህ	ለ. አትጠየቅ
3. ግራ	ሐ. አውጭኝ
4. አባራው	መ. ደርሷል
5. ቀለብ	ሠ. ቀድማችሁ
6. አንገቱን	ረ. ሲጥአድርጎ
7. ከእድሜያችሁ	ሰ. ያጋባል
	ሸ. ዘነበ
	ቀ. ዘርግፎ

2. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ጨነቀኝ (1ኛ አንቀጽ)
ለ. ቀለብ (1ኛ አንቀጽ)
ሐ. ባዳ (1ኛ አንቀጽ)
መ. ጭንቅላት (2ኛ አንቀጽ)
ሠ. እውን (2ኛ አንቀጽ)
ረ. ቀረጣጥፎ (3ኛ አንቀጽ)
ሰ. አውሬ (3ኛ አንቀጽ)
ሸ. ደንደስ (3ኛ አንቀጽ)
ቀ. አነፈነፈ (3ኛ አንቀጽ)
በ. ኮቴ (3ኛ አንቀጽ)
ተ. ጠብደል (3ኛ አንቀጽ)
ቸ. ትንቅንቅ (3ኛ አንቀጽ)
ነ. ተረታ (3ኛ አንቀጽ)
ኘ. መበላላት (3ኛ አንቀጽ)

መጻፍ

በ7.2.2 “የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች” በሚል ርዕስ የጻፋችሁትን ድርሰት በሚከተሉት የድርሰት መገምገሚያ መስፈርት በመፈተሽ ድርሰቱን አስተካክላችሁ ጻፉ።

7.3.3 መናገር

በቡድን ተደራጅታችሁ ከተማ ውስጥ ጫማ በማጽዳት ሥራ፣ ገጠር ውስጥ ከብት በመጠበቅ ሥራ ስለተሠማሩ ሕፃናት ሕይወት ንግግር አድርጉ። የንግግራችሁ ትኩረት መቋጫ እናንተ ወደፊት ስልጣንና ሀላፊነት ብታገኙ ለእንደነዚህ ዓይነት ሕፃናት ምን ልታደርጉላቸው እንደምትፈልጉ ይሁን።

ሰዋስው

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አገልግሎት ግለጹ።

ሀ. ካሰች ሁልጊዜ ጸሎት ታደርጋለች።

ለ. አምላክ ሆይ! አገራችን ሰላም አድርግልን!

ሐ. እንዴት ብለሽ ነው ዓይኗን የምታያት!?

መ. ለክፋም ለደጉም ፈጦ መድኃኒት ነው።

ሠ. ፈጠን ፈጠን ብለህ ሂድ።

ረ. መጣህም ቀረህም ስልክ ደውልልኝ።

ሰ. ለምን እንደዘገየህ ልትነግረኝ ትችላለህ?

ሸ. ቁም! እንዳትንቀሳቀስ!

ቀ. ፈጥነህ የማትመጣ ከሆነ ልቅር ወይ

በ. በርትታ ስላጠናች ማለፏ የማይቀር ነው

ምዕራፍ 8 ሰላም

8.1.1 አንብቦ መረዳት

ደባ ራሱን ስለት ድጎሱን

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን” የሚል አባባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ለምን የሚነገር ይመስላችኋል?

ለ. “ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን” የሚለውን ርዕስ አንብባችሁ ስለምንባቡ መልዕክት ገምቱ።

ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን

በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ ጎረቤቱን ሰላም የሚነሳ ነስርዲን የሚባል ሰው ነበር። ይህ ሰው ሼህ አብደላ የተባሉ ታጋሽ ጎረቤቱን በነገር ያስመረረ፣ ሁሌም የእሳቸውን ጉዳት የሚመኝ ክፋተኛ ሰው ነበር። ጎረቤቱ ላይ ያያት ትንሽ ነገር ሁሉ ታስቀናዋለች። ሁሌም እሳቸውን ለመጉዳት እንቅልፍ አጥቶ እንዳደረ ነው። የእሱን ነገረኛነትና ምቀኛነት የአካባቢው ሰው ሁሉ ያውቃል።

አንድ ቀን ነገረኛው ነስረዲን በጥዋት ተነስቶ ግቢውን ሲጎበኝ አጥሩ ጥግ የበቀለው የጎረቤቱ ማንጎ ብዙ ፍሬ አዝሎ አዬ። ፍሬዎቹን እያዬ እያለ የማንጎው ዛፍ በርካታ ቅርንጫፎች አጥሩን አልፈው ወደእሱ ግቢ እንደተንገረገጉ አስተዋለ። ወዲያው ወደጎረቤቱ ሄደና “አጥሩን አልፈው ወደእኔ ግቢ የገቡትን የማንጎ ቅርንጫፎች በአስቸኳይ ይቁረጡልኝ!” በማለት ጭቅጭቅ አነሣና ለአካባቢው ሽማግሌዎች አመለከተ።

ሼህ አብደላ ተከሰው ሽማግሌዎች ፊት ቀረቡ። ሽማግሌዎቹም ሼህ አብደላን “የእርሰዎ ማንጎ ቅርንጫፎች የጋራ አጥሩን አልፈው ወደነስረዲን ግቢ ገብተዋል?”

ሲሉ ጠየቋቸው። ሼህ አብደላም “እውነት ነው! ይሁንና ቅርንጫፎቹ በነስረዲን ላይ ምንም ጉዳት አላደረሱም፤ ፍሬ የያዙት ቅርንጫፎች ከሚቆረጡ ፍሬያቸው ሲበስል በጋራ ልንጠቀምባቸው እንችላለን” በማለት ሐሳብ አቀረቡ።

ነስረዲን በቁጣ “አይሆንም ክቡር ሽማግሌዎች! እኔ በጋራ መጠቀም አልፈልግም! ሼህ አብደላ ቅርንጫፎቹ ጉዳት አላደረሱም ላሉት፣ አሁን ጉዳት ባያደርሱ ወደፊት ጉዳት ያደርሱብኛል። በአጥሩ ጥግ ቲማቲም ልዘራ ስለሆነ ቅርንጫፎቹ ፀሐይ ይከለክሉብኛል” አለ።

ሽማግሌዎቹም “አቶ ነስረዲን የማንሳው ቅርንጫፎች ፍሬያቸው ደርሷል፤ ለመብሰል ጥቂት ቀናት ቢፈጁ ነው፤ ፍሬዎቹ እስኪበስሉ ልትታገስ አትችልም ወይ?” ሲሉ ጠየቁት። ነስረዲን በጥድፊያ “መታገስ አልችልም”! ቲማቲሙን ነገ ነው የምዘራው!” ሲል መልስ ሰጠ። ሽማግሌዎቹም በነስረዲን ቅንነት የጎደለው ምላሽ ቅር ቢሰኙም፣ ወደአብደላ ዞረው” እንግዲህ እምቢ ካለ ምን ማድረግ ይቻላል? በቃ አጥሩን አልፈው ወደእሱ የገቡትን ቅርንጫፎች ይቁረጡለት!” በማለት ፈረዱ። ሼህ አብደላ የሽማግሌዎችን ውሳኔ አሜን ብለው በመቀበል ቅርንጫፎቹን ቆረጧቸው። ነስረዲን የቅርንጫፎቹን መቆረጥ ሲያይ በደስታ እየተንጎማለለ” እኔ ጀግናው! ገና ሰላም እነሳቸዋለሁ!” አልለቃቸውም? እያለ ፎከረ።

ነስረዲን እንደፎከረው አልቀረም፤ ከሳምንታት በኋላ አንድ ቀን እንዲህ ሆነ። ብዙ እህል ሸጦ ከገበያ ሲመለስ ሼህ አብደላ ከኋላው ሲመጡ አያቸው። ትንሽ ተንኮል ሲያውጠነጥን ቆየና ወደሰፈሩ ሊደርስ ሲል፣ ከኪሱ የነበረውን ብር አውጥቶ መንገዱ ላይ ጣለው። ወዲያው ሰፈር እንደደረሰ” ከገበያ ስመጣ መንገድ ላይ ብዙ ብር ጠፋብኝ፤ ከኋላዬ ሲከተሉኝ የነበሩ ሼህ አብደላ ናቸው፤ እሳቸው መሆን አለባቸው አግኝተው የወሰዱብኝ!” እያለ ወሬውን ነዛው” የሰፈሩ ሰውም” አዬዬ...” ይህ ነገረኛ ሰው ዛሬ ደግሞ ምን ተንኮል አስቦ ይሆን የሼህ አብደላን ስም የሚያጠፋው?” በማለት መጠያየቅ ጀመረ።

ወዲያው ከነስረዲን በኋላ የደረሱት ሼህ አብደላ “በየቤቱ እየዞሩ ከገበያ ስመጣ መንገድ ላይ አራት ሺህ ብር ወድቆ አግኝቻለሁ፤ የጣለ ሰው አለ ወይ?” እያሉ ማጠያየቅ ጀመሩ። የሰፈሩ ሰውም “ነስረዲን ብር ጠፋኝ ሲል ነበር፤ የእሱ መሆን አለበት፤ ወስደው ይሰጡት።” አላቸው። ሼህ አብደላም በተባሉት መሠረት ወደነስረዲን ቤት ሄደው “መንገድ ላይ ስመጣ አራት ሺህ ብር ወድቆ አግኝቻለሁ፤ የአንተ ከሆነ እንካ ውሰደው።” አሉት። ነስረዲን ግን የተንኮል ፈገግታ እያሳያቸው” ብሩ የኔ ነው፤ነገር ግን መንገድ ላይ የጠፋብኝ አራት ሺህ ብር ሳይሆን ዐምስት ሽህ ብር ነው፤ አንዱን ሺህ ብር አስቀርተውብኛል።” በማለት ወነጀላቸው። እየሮጠ ሄዶም ሼህ አብደላን ባለፈው ለፈረዱለት ሽማግሌዎች ከሰሳቸው።

ሽማግሌዎችም ሼህ አብደላን አስጠርተው ሲጠይቋቸው “አዎ መንገድ ላይ ብር ወድቆ አግኝቻለሁ። ያገኘሁት ግን አራት ሺህ ብር እንጂ ዐምስት ሺህ ብር አይደለም። ነስረዲን ዐምስት ሺህ ብር ነው የጠፋብኝ ያለው እኔን ሊወነጅል ፈልጎ ነው። አንድ ሺህ ብር አስቀርቼ ምን ልጠቀም? የሰው ገንዘብ ከፈለግኩ ወድቆ አገኘሁ ምን አሰኘኝ? ድምፄን አጥፍቼ አራት ሺ ብሩን እንዳለ ለራሴ ማድረግ እችል ነበርኮ!” በማለት ተናገሩ። ሽማግሌዎችም ሲያስቡ ቆዩና “አቶ ነስረዲን ሼህ አብደላ የተናገሩትን ሰምተሃል። እርግጠኛ ነህ ዐምስት ሺህ ብር ነው የጠፋብህ?” ሲሉ ጠየቁት። ነስረዲን” አዎ እርግጠኛ ነኝ! ቀደም ብዬ ቆጥሬው ነበር፤ ዐምስት ሺህ ብር ነው የጠፋብኝ!” በማለት ሽምጥጥ አድርጎ ካደ።

ሽማግሌዎችም በመገረም ነስረዲንን ሲያዩት ቆዩና “ለዚህ ተንኮለኛ ሰው ትምህርት መስጠት አለብን!” ሲሉ አሰቡ። ከዚያም በፈገግታ ወደሼህ አብደላ ዞረው “እንግዲህ አቶ ነስረዲን የጠፋበት ዐምስት ሺህ ብር መሆኑን ካረጋገጠ እርሰዎ ወድቆ ያገኙት ገንዘብ የሌላ ሰው ነው ማለት ነው። ስለዚህ አራት ሺህ ብሩ የእኔ ነው ባይ እስኪመጣ ድረስ እርሰዎ ጋ ይቆይ።” ካሉ በኋላ ወደናስረዲን ዞረው” ነስረዲን ሆይ! አንተ ደግሞ ዐምስት ሺህ ብር ወድቆ አገኘሁ ባይ ሲመጣ፣ ብሩ የአንተ መሆኑ ተረጋግጦ ይሰጥሀል” በማለት ፈረዱበት።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “ነስረዲንና ሼህ አብደላ የኾለት ዓለም ሰዎች ናቸው” ቢባል ምን ማለት ይሆናል?

ለ. እናንተ ነስረዲንን ብትሆኑ በሼህ አብደላ ማንጎ ላይ ምን ዓይነት ውሳኔ ትወስኑ ነበር።

ሐ. የነስረዲን ሆን ብሎ አራት ሺህ ብር መጣል ምን ይነግራችኋል?

መ. “ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን” ከሚለው ምንባብ ስለሀገራችን የሸምግልና ዳኝነት ምን ተማራችሁ?

ሠ. የምንባቡን ሐሳብ ከርዕሱ ጋር እያገናዘባችሁ በአጭሩ አጠቃላችሁ ጻፉ።

ረ. ሽማግሌዎቹ “ለዚህ ሰው ትምህርት መስጠት አለብን” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

ሰ. በመጨረሻ ነስረዲን የሚፀፀት ይመስላችኋል? መፀፀቱን በመደገፍ ወይም በመቃወም ማጠቃለያ በሚሆኑ ሦስት ዓረፍተነገሮች ምንባቡን ቋጩት።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

8.1.2 ቃላት

1. የተሠመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ሊገልጹ በሚችሉ ሌሎች ቃላት/ሐረጋት በመተካት ጽሑፉን እንደገና ጻፉ።

   ሼህ አብደላና ነስረዲን ጎረቤት ናቸው። ነስረዲን ለጎረቤቱ መጥፎ ነገር የሚመኝ ክፋ ሰው ነው። ከግቢያቸው ፍሬው የተንዠረገገ ማንጎ አላቸው። የማንጎው የተወሰኑ ቅርንጫፎች ከነፍሬያቸው ወደነስረዲን ግቢ ዘልቀዋል። ይህን ያየው ነስረዲን፣ ጭቅጭቅ ወዳጅ ነውና፣ ሼሁ ላይ ደባ ለመሥራት ፎከረ። እንደፎከረም አልቀረ፣ ጉዳት አድርሶብኛልና ዛፋቸውን አስቆርጡልኝ በማለት ለአካባቢ ሽማግሌዎች አመለከተ። ሽማግሌዎቹ ክሱ የተንኮል መሆኑን ቢረዱም ዛፉ ከሰው ግቢ ገብቷልና ማንጎው ከበሰለ ፍሬው ጋር እንዲቆረጥ ወሰኑ። ሼሁም ፍሬውን ተካፍለን እንብላ ቢሉት አሻፈረኝ ስላለ ሽማግሌዎች የወሰኑትን ውሳኔ አሜን ብለው ተቀበሉ።

2. በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት የተለያዩ ሐረጋት አዋቅሩ።

   ሀ. ሀላፊነት　　ለ. ወሬውን　　ሐ. የወንድ

ምሳሌ፦



መጻፍ

በሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩ መሠረት በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት ጻፉ።



8.1.3 ማዳመጥ

ስግብግቡ ቀበሮና አሞራ

ቅድመማዳመጥ

ርዕሱን ተመልክታችሁ ስለምንባቡ መልዕክት ገምቱ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ንጉሡ አዋጅ ያወጁት በምን ምክንያት ነው?

ለ. ቀበሮ ለምንድን ነው ተንኮል የጠነሰሰው? የራሱ ድርሻ ስላልበቃው ነው?

ሐ. ንጉሡ የቀበሮና የአሞራን ድርጊት ቢሰሙ ምን ዓይነት ፍርድ የሚፈርዱ ይመስላችኋል?

መ. ከቀበሮና አሞራ ታሪክ ምን መማር ይቻላል?

ሰዋስው

በ“ሀ” ረድፍ ካሉት ግሶች ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸውን ከ”ለ” ረድፍ መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. መከረ	ሀ. ፈርዳ ነበር
2. ሰብሯል	ለ. ሰንቃለች
3. ፈርክሶ ነበር	ሐ. ወሳስዷል
4. ይፈልጣል	መ. ትፈርጣለች
5. ፈላልጧል	ሠ. ወሰደ
6. ይፈረክስ ነበር	ረ. መክሯል
7. አነጋገር	ሰ. ይሰርቅ ነበር
8. መስክራለች	ሸ. አወሳሰድ
9. ወቅራ ነበር	ቀ. ይነግራል
	በ. ዘርፎ ነበር

8.2.1 አንብቦ መረዳት

አሁን መልካም ሥሩ!

ቅድመንባብ

ሀ. “የሥራ ይደር ያስቸግራል፣ የምግብ ይደር ያገለግላል” ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? አባባሉ ምን ያስተምራል?

ለ. “አሁን መልካም ሥሩ!” ከሚለው ርዕስ በመነሳት የግጥሙን መልዕክት ገምቱ።

አሁን መልካም ሥሩ!

ውበትን ተላብሰው ግርማ ሞገሳቸው፣
ቱባ ጉንጉን መስሎ ሽብቶ ፀጉራቸው፣
በውል ተጣፍተው በሚያምር ኩታቸው
ፀሐይ እየሞቁ ዱካ ላይ ቁጭ ብለው፣
ልጆች ኑ! በማለት ጠሩን ከበራቸው።

እኛም ተሯሩጠን ወደእማቸው ሄድን፣
ያሉትን ልንሰማ ከፊታቸው ቆምን።
እማማም ልባቸው በደስታ ተሞላ፣
“ጎሽ ልጆቼ” ብለው መረቁን በጅምላ።
አዳምጡኝ በማለት መናገር ቀጠሉ፣
ድሮ የሠሩትን እያመሳሰሉ።
እንደናንተ እያለሁ ገና እምቦቃቅላ፣
ቤት ስጠርግ ሳፀዳ ወይ ቡና ሳፈላ፣
የቤተሰብ ችግር ኖሬያለሁ ሳሚላ።
አቅሜ በፈቀደ እናቴን በመርዳት፣
ስላላክ ኑሬያለሁ ለዘመድ ጎረቤት።
ተምሬ ስላደግሁ ሰላምና ፍቅር፣
ከእህት ከወንድሜ ከጎረቤት ሳይቀር
መተማመን እንጂ የለም መጠራጠር።
ሁሉን በቅንነት ስለገለገልኩኝ፣
እድሜዬ እንዲረዝም ሁሉም ሰው መረቀኝ።
ያኔ በልጅነት በሠራሁት ሥራ
ይኸው የምታዩት ለኔ ፍሬ አፈራ።
እንደኔ ማን አለ የሞላ መቶ አመት፣
እድሜው የረዘመ ኑሮው ያማረለት።
ፍቅርና ሰላም ለራስም ይበጃል፣
ተንኮልና ግጭት እድሜ ያሳጥራል።
እኔ የታደልኩት ገባችሁ ምስጢሩ፣
ነገ የሚያፈራ አሁን መልካም ሥሩ።
ታላቅን መሳደብ ጎራቤት ላይ ማፍጠጥ

መጥፎ ቦታ መዋል ወላጅን ማንጓጠጥ።

በዋላ ፈዛዛ ጊዜ እያጠፋችሁ

አላፊ አግዳሚውን ሰው ካሣዘናችሁ፣

እድሜያችሁ እንዲያጥር ትረገማላችሁ።

ሰማችሁ ልጆቼ ምክሬን ተቀበሉ፣

ክፉ መጥፎ ቦታ አደራ እንዳትውሉ።

በማለት መከሩን ካንጀት ከልባቸው

ሲነግሩን ሲያወሩን ሲቃ እየያዛቸው።

በፍቅር እንድንኖር ስለማሰባቸው፣

በጣም አስደሰቱን እናትነታቸው።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የመልካም ሥራ ትሩፋትን ከግጥሙ መልዕክት ጋር እያገናዘባችሁ አብራሩ።

ለ. የ"እማማ"ን ዘመንና የአሁኑን ዘመን የልጅ አስተዳደግ ዘርዝሩ።

ሐ. "ያኔ በልጅነት በሠራሁት ሥራ፣ ይኸው የምታዩት ለእኔ ፍሬ አፈራ።" የሚሉትን ስንኞች ሐሳብ፣ በልጅነት ምን እንደሰሩ አሁን ምን እንዳፈሩ በመጥቀስ አስረዱ።

መ. "እኔ የታደልኩት ገባችሁ ምስጢሩ፣

ነገ የሚያፈራ አሁን መልካም ሥሩ።" የሚሉትን ስንኞች ሐሳብ አብራሩ።

ሠ. አጠቃላይ የግጥሙ መልዕክት ምንድን ነው? የእማማን የልጅነት ተግባር ከዘመኑ ልጆች ጋር እያገናዘባችሁ ገምግሙ።

ረ. በግጥሙ መሠረት መልካምና መጥፎ ባሕርያትን ዘርዝሩ።

ሰ. በግጥሙ መሠረት የሚከተሉትን ስንኞች ሐሳብ አብራሩ።

- እማማም ልባቸው በደስታ ተሞላ
- የቤተሰብ ችግር ኖሬያለሁ ሳሚላ
- ክፉ መጥፎ ቦታ አደራ እንዳትውሉ

አቀላጥፎ ማንበብ

“አሁን መልካም ሥሩ” በሚለው ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

8.2.2 ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ቱባ	ሠ. እምቦቃቅላ	ቀ. ማንጓጠጥ
ለ. ሸበቶ	ረ. ያኔ	በ. ሲቃ
ሐ. ዱካ	ሰ. ይበጃል	ተ. ጉንጉን
መ. ጅምላ	ሸ. ማፍጠጥ	ጨ. ተሞላ

መጻፍ

ከሚከተሉት ሥርዓተነጥቦች መርጣችሁ በጽሑፉ ውስጥ ቁጥሮቹን ተኩ።

“ ” ! ፤ ? ፣

አንድ አባት አህያ እየነዳ ከልጁ ጋር መንገድ መሄድ ጀመረ። እልፍ እንዳለ ሰዎች “ምን ዓይነት ምኞች ናቸው1 እንዴት አህያ እያለ በእግራቸው ይሄዳሉ! “በማለት ተሿቸው 2 አባት ትችቱን ሲሰማ ኹለቱም አህያዋ ላይ ወጡና መንገዳቸውን ቀጠሉ። ጥቂት እንደሄዱ ሰዎች 3 እንዴት ያሉ ጨካኞች ናቸው! እንዴት አንድ አህያ ለኹለት ይጋልባሉ 3 ብለው ራሳቸውን ነቀነቁባቸው።

አባትየው ከአህያዋ ላይ ወረደ የተወሰነ መንገድ እንደተጓዙ ሌሎች መንገደኞች “አይ ስምንተኛው ሺህ 4 ልጅ በአህያ ተቀምጦ ሽማግሌ አባቱን በእግር ያስኬዳል 5 በማለት ተሿቸው። ወዲያው አባትዬው ልጁን ከአህያዋ አውርዶ እርሱ ጋለበና ጉዞ ተጀመረ። ከገበያ የሚመጡ ሰዎች አገኟቸውና “እንዴት ምኑንም የማያውቅ ልጅ በእግሩ እየሄደ እርሱ በአህያ ይሄዳል? ወይ ጭካኔ 6” ብለው ደረታቸውን ደቅተው ሄዱ።

በዚህ ጊዜ አባትየው 7 ከአህያዋ ወረደ። “አየህ ልጄ፣ በዚህ ዓለም ምንም ነገር ብትሠራ ሰውን ሁሉ ማስደሰት አትችልም። ሰዎች እንዲህ ይሉኛል እያልክ የምትፈራ ከሆነ ምንም ነገር ማድረግ አትችልም” አለው።

8.2.3 መናገር

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም “ልጆችና የእናቶች ምክር” በሚል ርዕስ በክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ።



ሰዋስው

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በሀላፊ ጊዜ ቅርጽ ጻፉ።

ምሳሌ፦

ኢ.ሀላፊ ጊዜ	ሀላፊ ጊዜ
1. አስማረች ነገ ትመጣለች።	▪ አስማረች ትናንትና መጣች።
2. ፈለቀ ትምህርት ይማራል።	▪ ፈለቀ ትምህርት ተማረ።
3. ሀዋ ወደቤት እየመጣች ነው።	▪ ሀዋ ወደቤት መጣች።

ሀ. መስከረም ትዳር ትይዛለች።

ለ. ጀሚላ ልጆችን ትመክራለች።

ሐ. ፈለቀ ቤት ይሠራል።

መ. ሳራ እንጀራ ትጋግራለች።

ሠ. ወሰነ ሰነፍ ይጠላል።

የኑሩ ትዝታ

ቅድመንባብ

ከርዕሱ ተነስታችሁ የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

የኑሩ ትዝታ

ቅዳሜና እሁድ ለኑሩ የሚወደዱ ዕለቶች ናቸው። አዲስ ሳምንት ተጀምሮ እነዚያ የሚወዳቸው ቀናት እስኪመጡ ያቅበጠብጠዋል። በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ እያሉ ጣፋጭ ተረቶችን የሚያቀርቡለት አባባ ተስፋዬና የልጆች ክፍለጊዜ አዘጋጆችን በሙሉ ማየት ያስደስተዋል። ኑሩ ዛሬም እንደተለመደው የእሁድ የልጆች ክፍለጊዜን ተቀምጦ ይመለከታል። አበባ ተስፋዬም የወፎችን ጎጆ ስለሚያፈርስ ስለአንድ ወጣትና ስለአንዲት ወፍ ተረት ያወሩ ነበር።

ኑሩ ቴሌቪዥን እያየ እያለ የኋላ እግሯን የተሰበረች ሙሉ ነጭ ድመት ከኑሩ አጠገብ መጥታ ተቀመጠች። በጣም የሚወዳት ድመት ነች። ከእሷ ሌላ ምንም እንስሳ አቅርቦ አያውቅም። ድመቷን ያገኛት በአንድ አጋጣሚ ነበር። የተሰበረ እግሯን በለስላሳ ጣቶቹ እየዳበሰ ወደትዝታው ገባ። አንድ ቀን ከሚማርበት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከኤፍሬም ጋር ወደቤታቸው እየተሯሯጡ ይመጣሉ። ከቤታቸው መድረሻ አካባቢ ከፊት ለፊታቸው አንዲት ፀጉራም የሆነች ነጭ ድመት፣ ትንሽ ኳስ ቢጤ እያንከባለለች ስትጫወት ያያሉ። ኹለቱም እሷኑ ለመምታት ድንጋይ አነሱ። ኑሩ ግን ያነሳውን ድንጋይ ሊወረውርባት አልፈለገም። ምክንያቱም ጨዋታዋ ደስ ስላለውና መልኳም ስለአማረው ወድዷታልና!

ጓደኛው ኤፍሬም የያዘውን ድንጋይ ለመወርወር እጁን ሲያነሳ፦

“ኤፍሬም ተው አትምታት! በጣም የምታምር ድመት ናትኮ?”

“ሂድ ሞኝ! ድመቶች ደግሞ ምናቸው ያምራል።”

“እንዴ ድመቶች እኮ በጣም ደስ ይላሉ። ደግሞም አይጥ ለመያዝ ይጠቅሙናል።”

“አረ ምን ይጠቅሙናል? ሌቦች አይደሉም እንዴ! የተሰቀለ ስጋ ከመብላት፣ ወጥና ወተት የያዘን እቃ ከመድፋት ሌላ ምን ያውቃሉ!።” እንዲያውም እማምዬን አስም ያስያዘቻት እኛ ቤት የነበረችው ድመት ናት፤ አልጋው ሥር እየተፀዳዳች።”

“እንደሱ አይደለም። ድመቶችን ስርቆት እንዳይማሩ አድርገን ካሳደግናቸው በጣም የሚወደዱ የቤት እንስሳት ናቸው።”

“እማዬ ግን ድመቶች መጥፎ ናቸው፤ እንዳትቀርቧቸው ስላለችኝ ይህችን ድመት መምታት አለብኝ።”

“ተው እንጂ ኤፊ! አንተ ካልወደድካት እኔ ወስጄ ላሳድጋት” አለው ኑሩ በማባበል።

ኹለቱ ትንሽ ከተከራከሩ በኋላ ኤፍሬም የያዘውን ድንጋይ ወረወረባት። ድንጋዩ ከኋላዋ የቀኝ ታፋዋ ላይ አረፈ። የስቃይ ድምፅ አሰምታ ለማምለጥ ትንሽ ከሮጠች በኋላ መሄድ አቅቷት ወደቀች። ኤፍሬም ድመቷን በመምታቱ “ወንዳታ! መታኋት! ይኼ ነው!” አለና ወደድመቷ እየሮጠ ሄዶ ተመለከታት። የማንቋረር ድምፅ ታሰማለች። “ይህቺ ሙትቻ ሠራሁላት” በማለት የመታትን እግሯን እንደገና ለመርገጥ እግሩን ሲያነሳ ኑሩ ባለ በሌለ ኃይሉ ገፈተረው። ኤፍሬምም ወደኋላ ወደቀ።

“በጣም መጥፎ ልጅ ነህ። አሁን እሷን መታህና ምን ጥቅም ታገኛለህ?” አለ በንዴት። በጣም አሳዝናዋለች። ቁጭ አለና የተሰበረ እግሯን ሲነካካላት ኤፍሬም ከወደቀበት በመነሳት” ምን ብለህ ነው ገፍትረህ የምትጥለኝ! ደግሞ ለእልክህ እገላታለሁ!” አለና አሁንም በእርግጫ ለመምታት እግሩን ሲያነሳ ኑሩም ከተቀመጠበት ተነስቶ ተፋጠጡ። መገፋፋትና መጎሻሸም እንደጀመሩ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ ሽማግሌ መጥተው ገላገሏቸውና፡-

“ምነው ልጅ ምን ያጣላችኋል?” ብለው ኑሩን ጠየቁት።

“አዩት አባባ! ይችን ድመት በድንጋይ መትቶ እንደሰበራት! ለምን ትመታታለህ እቤት ወስጄ ላሳድጋት ብለው እምቢ ሲለኝና እንደገና ሊመታት ሲል ብገፈትረው ወደቀ።”

“ውሸቱን ነው አባባ። ሆንብሎ ነው የገፋኝ”

ሽማግሌው የወደቀችውን ድመት አየት አድርገው ወደኤፍሬም ዘወር በማለት “በእውነት ጥሩ አልሠራህም። ይቺ ድመት ምኗ ይመታል? እንስሳን ማፍቀርና መንከባከብ እንጂ መምታት ነውር ነው። ጓደኛህ እቤት ወስጄ ላሳድግ ሲልህ እሺ ማለት ነበረብህ። በል አሁን ታረቁ።” ብለው ካስታረቋቸው በኋላ የድመቷን ሰባራ እግር አሻሽተው ለኑሩ አስያዙት። ኤፍሬምንም ኹለተኛ እንስሳትን መምታት እንደሌለበት መክረው፣ ወደቤታቸው እንዲሄዱ አደረጉ። በዚህም ያች ድመት ዛሬ የኑሩ ጓደኛ ሆና አብረው በአንድ ቤት ይኖራሉ። የኑሩና የኤፍሬምም ጓደኝነት ተጠናክሮ ቀጠሏል።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ቅዳሜና እሁድን የኑሩ ተወዳጅ ዕለታት ያደረጋቸው ምንድን ነው?

ለ. ድመቷ ከመሰበሯ በፊት ዱር አደር ነበረች?

ሐ. ድመቷ ቆንጆና ተጫዋች ናት፤ ለምንድን ነው ኤፍሬም የጠላት?

መ. ኤፍሬም የኑሩን ሐሳብ ቢቀበል ኑሮ ታሪኩ ምን ይሆን ነበር?

ሠ. የኤፍሬም እናት ለድመቷ መሠበርና ለኹለቱ ጓደኛሞች መጣላት ያላቸውን ሚና ግለጹ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የኑሩ ትዝታ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

8.3.2 ቃላት

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚልታችሁ ጻፉ።





ለ. የሐሳብ ማደረጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚልታችሁ ጻፉ።



መጻፍ

ርዕስ መርጣችሁ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት አራት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ።

8.3.3 መናገር

መምህራችሁ በሚሠጧችሁ መመሪያ መሠረት ሥራ ለሠሪው ምን ጥቅም እንዳለው ለማወቅ ቃለመጠይቅ አዘጋጁ።

ማስታወሻ

ቃለመጠይቅ ስታዘጋጁና ስታቀርቡ ሁሉም የቡድኑ አባላት የሥራ ድርሻ ቢኖራቸው መልካም ነው። ሁሉንም ለማሳተፍ የሚከተሉትን ነጥቦች እንደመመሪያ መከተል ትችላላችሁ።

1. አንዲት/አንድ ተማሪ ለቃለመጠይቅ የሚሆኑ ጥያቄዎች ታዘጋጅ/ያዘጋጅ፣
2. አንዲት/አንድ ተማሪ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በማየት አርማ/አርሞ ታስተካክል/ያስተካክል።
3. ሌላ ተማሪ እንደጋዜጠኛ ጠያቂ ትሁን/ይሁን።
4. ሌላ ተማሪ ተጠያቂ በመሆን መልስ ትስጥ/ይስጥ።
5. ሌላ ተማሪ ፎቶ ማንሳት ወይም ቪዲዮ የመቅረጽ ሥራ ትፈፅም/ይፈፅም።
6. ሌሎች ተማሪዎች አድማጭና ተመልካች በመሆን የቃለመጠይቅ ድባብ ይፍጠሩ።
7. ጠያቂና ተጠያቂ በመቀያየር ልምምድ ማድረግ ይቻላል።

ሰዋስው

መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ለቃለመጠይቅ የሚያገለግሉ ዐምስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፡- የጎረቤት ልጆችን በሥነምግባር ስለማነፅ፤

ሀ. ሰው በጉርብትና እንዴት መኖር አለበት ይላሉ?

ለ. ልጆች ከጎረቤት ምን ይማራሉ?

ሐ. ማነው ከወላጆች ሌላ ልጆችን በጥሩ ሥነምግባር የሚያንፅ?

መ. በምንድን ነው ልጆችን ማነፅ የሚገባ?

ሠ. መቼ ነው ልጆች በሥነምግባር መታነፅ ያለባቸው?

ምዕራፍ 9 የአየር ንብረት

9.1.1 አንብቦ መረዳት

የአማራ ክልል አየር ንብረት

ቅድመንባብ

ስለአየር ንብረት የምታውቁትን ተናገሩ።

የአማራ ክልል አየር ንብረት

የአየር ንብረት ሰፋ ካለ አካባቢ ላይ ወይም መልክዓምድር ላይ ለበርካታ አመታት የተመዘገበ የሙቀት፣ የቅዝቃዜ፣ የደመናና የንፋስ መጠን አማካይ ውጤት ነው። የአማራ ክልል ምዕራባዊ፣ ሰሜናዊ፣ ደቡባዊና ምስራቃዊ ክፍል ዝቅተኛ የሙቀት መጠን 12.4 ዲግሪ ሴሊሺየስ ነው። ከፍተኛው ደግሞ 27.8 ዲግሪ ሴሊሺየስ ነው። ክልሉ በአራት ዓይነት የአየር ንብረት ቀጠናዎች የተከፋፈለ ነው። ይኸውም በክልሉ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ቀጠና 1 ውርጭ (3%) ፣ ቀጠና 2 ደጋ (31%) ፣ ቀጠና 3 ወይና ደጋ (60%) ና ቀጠና 4 ቆላ (6%) ይሸፍናሉ። በመሆኑም ክልሉ ከበረሃ የአየር ንብረት ባሻገር ሁሉንም የአየር ንብረቶች ይዟል። ይህም ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1፡- በክልሉ አማካይ የዝናብ መጠን በየአየር ንብረት

የአየር ንብረት	ዓመታዊ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ	ስፋት በኪ.ሜ. ስኩየር	ሽፋን (%)
ቆላ	566-835	4,040	6
ወይና ደጋ	835-1189	94,638	60
ደጋ	1,189-1,711	48,801	31
ውርጭ	<1,711	4,636	3

(ምንጭ፡- የአማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት፣ 2011 ዓ.ም.)

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተገለፀው አብዛኛውን የክልሉን የቆዳ ስፋት (60 በመቶውን) የሚሸፍነው ወይና ደጋ የአየር ንብረት ነው። የዝናብ ስርጭቱም በቂ የሚባል ስለሆነ የተለያዩ አዝዕርትን ያበቅላል። የተለያየ ዝርያ ያላቸውንም እንስሳት ለማርባት ምቹ እንደሆነ ያመለክታል።

ሠንጠረዥ 2፡- የክልሉ የዝናብ መቀነስና መጨመር አዝማሚያ

ተ.ቁ	አዝማሚያዎች	የቆዳ ስፋት በኪ.ሜ ስኩየር	ሽፋን በ(%)
1	በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ	24,064.1	15.4
2	በተወሰነ ደረጃ መቀነስ	98,580.2	63
3	በከፍተኛ ደረጃ መጨመር	2,245.02	1.4
4	በተወሰነ ደረጃ መጨመር	31,477.9	20.1
	ድምር	156,367.3	100

(ምንጭ፡- የአማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት፣ 2011 ዓ.ም.)

ሠንጠረዥ 3፡- የክልሉ የዝናብ መጠን የቆይታ ጊዜ

ተ.ቁ	ዝናብ የሚቆይባቸው ወራት	አካባቢ	ሽፋን በሄክታር	ሽፋን በመቶኛ
1	ለ5 ወራት የሚያገኙ	ቀጠና 1	799,890.1	5.09
2	ለ4 ወራት የሚያገኙ	ቀጠና 2	4,581,629.8	29.16
3	ለ3 ወራት የሚያገኙ	ቀጠና 3	8,494,029.5	54.08
4	ለ2 ወራት ወይም ከዚያ ያነሰ የሚያገኙ	ቀጠና 4	1,834,129.6	11.67
	ድምር		15,712,679.1	100.00

(ምንጭ፡- የአማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት፣ 2011 ዓ.ም.)

ከላይ በተገለፁት ሠንጠረዦች መሠረት፣ ክልሉ በቂ ዝናብ ማግኘት ይችላል። በዚህም በመኸር ሰብል ብቻ ከመጠቀም ባለፈ የተለያዩ የዉኃ የማቆር ሥራዎች መስራት ይቻላል። ይህም በበጋ መስኖ ለማልማት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በሌላ በኩል በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የዝናብ መቀነስ አዝማሚያ እየጨመረ ነው። ስለዚህ የሚገኘው የዉኃ ሀብት ሳይባክን መጠቀም የአየር ንብረት መዛባትን መመለስ ያስፈልጋል። በክልሉ በከፍተኛ መጠን የዝናብ መቀነስ የሚታይባቸው አካባቢዎች(ወረዳዎች) ሰቆጣ፣ ጋዝቢላ፣ ግዳን፣ ቆቦ፣ ላስታ፣ ጉባላፍቶ፣ ደላንታ፣

ዳውንት፣ መቅደላ፣ ተንታ፣ ሳይንት፣ ደሴና ለጋንቦ ናቸው። በአንባሩ ከፍተኛ የሆነ ዝናብ የመጨመር አዝማሚያ የሚታይባቸው ደግሞ በምዕራብ አማራ የሚገኙ አካባቢዎች ናቸው።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በአማራ ክልል የማይካተተውን የአየር ንብረት ጥቀሱ።

ለ. ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያለው የአየር ንብረት የትኛው ነው?

ሐ. ከፍተኛ የቆዳ ስፋት (ሽፋን) ያለው የትኛው የአየር ንብረት ነው?

መ. አጠቃላይ የክልሉ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከስንት እስከስንት ይደርሳል?

ሠ. የክልሉ የዝናብ መጠን አዝማሚያ በመቀነስ ወይም በመጨመር ላይ መሆኑን በመረጃ አስረዱ።

ረ. ከፍተኛ የቆዳ ሽፋን የሚይዘው ለስንት ወራት ዝናብ የሚቆይበት የአየር ንብረት ቀጠና ነው?

ሰ. ዝቅተኛ የቆዳ ሽፋን የሚይዘው ለስንት ወራት ዝናብ የሚቆይበት የአየር ንብረት ቀጠና ነው?

አቀላጥፎ ማንበብ

በሚከተለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ የማንበብ ፍጥነትን ተለማመዱ።

የዓለም የሙቀት መጨመር ተፅዕኖ	የቃላት ብዛት	1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ	6ኛ
የዓለማችን ሙቀት በየብስም ሆነ በባሕር እየጨመረ	6	\	...	...	...	...	...
ይገኛል። የሙቀቱ መጨመርም ትነት እንዲጨምርና	11	\	...	...	...	...	...
የአፈር ርጥበት እንዲሟጠጥ በማድረግ ድርቅን እያባባሰ	17	...	...	...	...	...	...
ነው። የባሕር በረዶ ከአርክቲክ ዙሪያ ጠረፍ እየሸሸ ነው።	25	...	...	...	...	...	...
በአልኘስ፣ በአላስክ፣ በግሪንላንድና በዓለም ዙሪያ በሚገኙ	31	\	...	...	...	...	...

የተራራ ሰንሰለቶች የሚገኘው የበረዶ ግግር በፍጥነት	37	...	...	...	...	...	...
እየቀለጠ ነው፤የባሕር ወለልም ከፍ እያለ ነው።	44	...	...	...	...	...	...
የሙቀት መጨመርን ተከትሎ የእንስሳትና የዕጽዋት	48	...	...	...	...	...	...
ዝርያዎች ወደምድር ዋልታዎች አቅጣጫ በመሸሸ	54	...	...	...	...	...	...
ከፍታ ባላቸው ቦታዎች መታየት ጀምረዋል። በባሕር	60	\	...	...	...	...	...
ዳርቻዎች በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ በርካታ ሰዎች	67	...	...	...	...	...	...
በባሕር ወለል መጨመር ምክንያት ለሚመጣ ማዕበል	73	...	...	...	...	...	...
ተጋላጭ ሆነዋል። በባሕር ዳርቻዎችና በዝቅተኛ ቦታዎች	79	\	...	...	...	...	...
ላይ የሚገኙ ደሴቶች ለትልቅ ስጋት ተዳርገዋል።	84	...	...	...	...	...	...
ከአሁኑ ለመቀነስ ጥረት ካልተደረገና አስፈለጊ	89	\	...	...	...	...	...
ርምጃዎች ካልተወሰዱ በተደጋጋሚና ረዘም ላለ ጊዜ	95	...	...	...	...	...	...
የሚከሰት ጠንክር ያለ/ሙቀት የብዙ ሰዎች ሕይወት	102	...	...	...	...	...	...
ለህልፈት የሚዳርግ ይሆናል። በሚቀጥሉት አሥርት	107	...	...	...	...	...	...
አመታት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የአካባቢ አየር ሙቀት፣	115	...	...	...	...	...	...
የትነት ሁኔታ መዛባት፣ ከፍተኛ የሆነ የአፈር ርጥበት	121	...	...	...	...	...	...
መቀነስ... በብዙ አካባቢዎች የግብርና ሥራዎችን	127	...	...	...	...	...	...
ለማካሄድ በጣም አስቸጋሪ ያደርጋሉ፤ በዉኃ ሀብት	134	...	...	...	...	...	...
እጥረት ከፍተኛ ውጥረት ይፈጠራል።	136	...	...	...	...	...	...

የተማሪዋ ፍጥነት 98 ቃላት በደቂቃ

በተማሪ በስህተት የተነበበ ቃላት 6 ቃላት

በደቂቃ ትክክል የተነበ ቃለት 92

ማስታወሻ

“የዓለም ሙቀት መጨመር ተፅዕኖ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በምሳሌነት ያነበበችውን ተማሪ ውጤት ለመረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውሉ።

1. አንባቢዋ አንድ ደቂቃ ሲያልቅ የቆመችበት ቦታ ምንባቡ ውስጥ በእዝባር (\) ምልክት ተመልክቷል። ይህም ‘ያለ’ የሚለው ላይ ይገኛል።

2. እዝባሩ ድረስ የተነበቡት ቃላት ብዛት 98 (102-4 = 98) ነው። “102” አንባቢዋ የቆመችበት መሥመር ድረስ ያሉትን ቃላት ብዛት ሲያሳይ፣ “4” ደግሞ ከእዝባሩ በኋላ መሥመሩ ውስጥ ሳይነበቡ የቀሩትን ቃላት ብዛት ያሳያል። ስለዚህ የአንባቢዋ አጠቃላይ ፍጥነት በደቂቃ “98” ቃላት ነው።

3. አንባቢዎች በሚለውና “ነኛ” በሚለው ሥር ከላይ እስከታች የሚታዩት ምልክቶች (\) የአንባቢዋን ስህተቶች ያሳያሉ። ብዛታቸው “6” ነው። ስለዚህ የአንባቢዋ ትክክለኛ ንባብ 92 (98-6) ቃላት በደቂቃ ነው። ይህ ነው የተማሪው ፍጥነት በደቂቃ ትክክል የሚባለው።

4. “አንብቦ መረዳት በሚለው ሥር አራት የትክክለኛነት (√) ምልክቶች ይታያሉ። የመለሰቻቸው ጥያቄዎች ሲታረሙ የተሳሳተችው አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። የአንባቢዋ አንብቦ መረዳት ችሎታ 4/5 ወይም 80% መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ የአንባቢዋ፡-

ፍጥነት		98 ቃላት በደቂቃ
ትክክለኛ ንባብ	→	92 ቃላት በደቂቃ
አንብቦ መረዳት	→	4/5 ወይም 80% መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በዚህ መንገድ የምታገኟቸውን መረጃዎች እንደሚከተለው ማስፈር ትችላላችሁ።

ሀ. ትክክለኛ ንባብ _____

ለ. ፍጥነት _____

ሐ. አንብቦ መረዳት_____

9.1.2 ቃላት

1. በ“ሀ” ረድፍ ካሉት ጋር የሚዛመዱትን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. የቆዳ	ሀ. ጊዜ
2. የአየር	ለ. ስርጭት
3. የሙቀት	ሐ. ማቆር
4. የዝናብ	መ. ስፋት
5. የቆይታ	ሠ. መጠን
6. የዉኃ	ረ. ንብረት
	ሰ. ውርጭ

2. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ቀጠና	ሰ. አዝርዕት
ለ. ውርጭ	ሸ. መኸር
ሐ. ደጋ	ቀ. በጋ
መ. በረሃ	በ. ሳይባክን
ሠ. አማካይ	ተ. መዛባት
ረ. መሙቀት	ቸ. በአንዳሩ

መጸፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በመጠቀም “ሰው ሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች” በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።



9.1.3 ማዳመጥ

ደኖችና የአየር ንብረት ለውጥ

ቅድመማዳመጥ

“ደኖችና የአየር ንብረት ለውጥ” ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምታዳምጡት ምንባብ ምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የደኖችን ጥቅም ዘርዝሩ።

ለ. የደን እምቅ የብዝሃ ሕይወት ሀብቶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ደኖች እንዴት ነው ምድር እንድትቀዘቅዝ አስተዋፅኦ የሚያደርጉት?

መ. በአለም ደረጃ ደኖች በሰዎች የሚፈጠርን የተቃጠለ አየር ምን ያህል በመቶ ያስወግዳሉ?

ሠ. የኢትዩድያን የጥንትና የአሁን የደን ሽፋን በማነፃፀር በሕዝቦችና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ተፅዕኖ አብራሩ።

ሰዋስው

በሚከተሉት ድብልቅ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙ ጥገኛ ሐረጎችን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. አንድ የክባቢ የአየር ሙቀት መጠን ሲቀየር በሌላ የክባቢ የአየር ንብረት ሙቀት ይተካል።

ለ. የአየር ፀባይ በአጭር ጊዜ መለስቀለስ ሲል የአየር ንብረት ግን ለረዥም ዘመን ይዘልቃል።

ሐ. የአየር ንብረት ከተለወጠ በሰዎች አኗኗር ላይ ተፅዕኖ ይደርሳል።

መ. ነባር ዝርያዎች የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም ካቃታቸው በአዳዲስ ዝርያዎች ይተካሉ።

ሠ. የዋልታዎች ግግር በረዶ ሲቀልጥ የባሕር ወለል ከፍ ይላል።

9.2.1 አንብቦ መረዳት

አለሚቱና መምህሯ

ቅድመንባብ

ከመማሪያ ክፍላችሁ ውጭ አስተማሪዎቻችሁን ጥያቄ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ቀድማችሁ ጥያቄ አዘጋጅታችሁ ወይስ ሳታዘጋጁ?

አለሚቱና መምህሯ

አለሚቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ናት። የምትኖርበት አካባቢ ከጊዜ ወደጊዜ የሙቀት መጠኑ እየጨመረ መምጣቱን ከአካባቢው ነዋሪዎች ትሰማለች። ይህም ነገር ሁሌ ለራሷ ጥያቄ ይፈጥርባታል። አንድ ቀን የህብረተሰብ ሳይንስ መምህሯን ለመጠየቅ ወሰነች። ጥያቄዎችን አደራጅታ ቃለመጠይቅ እንደምታደርግላቸው ነግራቸው ቀን ወሰኑና ተለያዩ።

በቀጠሯቸው ቀን ተገናኙና አለሚቱና መምህሯ ወ/ሮ ወይንሸት ስለአየር ንብረት ለውጥ ያከናወኑት ውይይት እንደሚከተለው ቀርቧል።

አለሚቱ፡- "መምህር ለጥያቄዎቼ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው ስላገኘሁዎት አመሰግኖዎታለሁ!"

መምህር፡- "መልካም! እኔም ለማወቅ ስለተዘጋጀሽ አመሰግናለሁ!"

አለሚቱ፡- መምህር የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎችን ቢያስረዱኝ?"

መምህር፡- “የአየር ንብረት ለውጥ ሙሉ በሙሉ ሰው ሠራሽ ነው ባይባልም ለለውጡ የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ለምሳሌ የሕዝብ ቁጥር ሲጨምርና ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፋ የሀይል ምንጭ አጠቃቀምና የጥሬ እቃዎች ፍጆታ ይጨምራል። ይህም በበኩሉ ጎጂ ኬሚካላዊ ነገሮች እንዲመረቱና በከባቢ አየር ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ይሆናል።

አለሚቱ፡- “ታዲያ መምህር! በከባቢ አየር ውስጥ ተከማችተው ምን ይፈጥራሉ?”

መምህር፡- “በከባቢ አየር ውስጥ የግሪን ሀውስ ጋዝ ክምችት ይፈጥራል፤ ይህም መንስኤው ሰውሠራሽ ነው ማለት ነው።”

አለሚቱ፡- “መምህር! የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ነው ማለት ይቻላል?”

መምህር፡- “አይ! ይህ ብቻ አይደለም፤ የአህጉራት መፈራቀቅ፣ በእሳተገሞራ ፍንዳታና በፀሓይ ብርሃን መጠን መለዋወጥም የአየር ንብረት ለውጥ ሊከሰት ይችላል። እያንዳንዳቸውን መረዳት ትፈልጊያለሽ?”

አለሚቱ፡- “አዎ! መምህር! ቢያስረዱኝ ደስ ይለኛል።”

መምህር፡- “በጣም ጥሩ። የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የመኖሪያ ቤት ግንባታ ፍላጎት ይጨምራል፤ የኢንዱስትሪዎች ግንባታ ይካሄዳል፤ የመሠረተልማት አውታሮች ይስፋፋሉ። እነዚህን የተያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባልም ደኖች ይመነጠራሉ። አካባቢው ይራቆታል፤ የአካባቢ ብክለትም ይፈጠራል። ከተለያዩ ፋብሪካዎች በካይ ጋዞች ይለቀቃሉ። በካይ ጋዞችና ኬሚካሎች ከንፁህ አየር ጋር ተቀላቅለው ንፁሁን አየር ከመበከላቸውም በተጨማሪ ርስበርሳቸው ኬሚካላዊ ውህድ ይፈጥራሉ።”

አለሚቱ፡- “እና ምን ጉዳት ያደርሳሉ መምህር?”

መምህር፡- “በእርግጥ የአየር ዝውውርና ነውጥ የአንዳንዶቹን በካዮች ኃይል ስለሚያደክም ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ግን ረጅም ርቀት በመጓዝ ከአካባቢ አየር ውስጥ ይቆያሉ። ከዚያም በጠጣር ወይም በፈሳሽ መልክ ከዝናብ ጋር ተዋህደው ወደመሬት ተመልሰው ብዙ ጉዳት ያደርሳሉ። አሁንስ ግልፅ ሆነልሽ?”

አለሚቱ፡- “መምህር! በጣም ግልፅ ነው። የአህጉራት መፈራቀቅ የሚባለው ነገር ምንድን ነው እንዴትስ ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይሆናል።”

መምህር፡- “አሁን ያሉት አህጉራት፣ ምድር ስትፈጠር ከነበራቸው አቀማመጥ የተለየ ነው። ከመቶ ሚሊዮኖች ዓመታት በፊት ደቡብና ሰሜን አሜሪካ፣ እስያ፣ አውስትሪሊያና አንታርቲካ አህጉራት አፍሪካን ማዕከል አድርገው አንድ ላይ የተገጣጠሙ ነበሩ። ቀስ በቀስ ግን በትልቁ አህጉር ውስጥ መፈራቀቅ እየተፈጠረ ትልልቅ የመሬት አካላት እየተገመሱና እየራቁ ሲሄዱ በመሀከላቸው ውቅያኖሶች ተፈጠሩ። ለምሳሌ ደቡብ አሜሪካና ሰሜን አሜሪካ ከአፍሪካና አውሮፓ ሲገነጠሉ፣ በመሃላቸው አትላንቲክ ውቅያኖስ ገባ።

አለሚቱ፡- “መምህር በኢትዮጵያ ላይ የተፈጠረ የመሬት መፈራቀቅ ካለ ምሳሌ ቢሰጡኝ?”

መምህር፡- “ልክ ብለሻል! አሁን በኢትዮጵያ የአፋርን ስምጥ ሸለቆ ይዞ የተከሰተው የመሬት መሰንጠቅና መፈራቀቅ አህጉሮችን ከፈጠረው ሂደት ጋር ተመሣሣይነት አለው። የአህጉራት የመፈራቀቅ እንቅስቃሴና የውቅያኖሶች አቀማመጥ ለውጥ የውቅያኖሶች ሙቀትና ርጥበት በመላው ዓለም የሚያሠራጨበትን የዝውውር ስርዓት ይቀይረዋል። ኢትዮጵያም የዓለም አንድ አካል ናት።”

አለሚቱ፡- “መምህር! የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንዴት ለከባቢ አየር ለውጥ መፈጠር መንስኤ ይሆናል?”

መምህር፡- “የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ በኹለት መንገድ ከባቢ አየርን ይለውጣል። አንደኛው፣ ከእሳት ጎሞራው ጋር የሚተፉ ብናኞች የፀሐይ ብርሃንን በመጋረድ ቅዝቃዜን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ሆኖም ብናኞቹ ከባቢ አየር ውስጥ ለረጅም አመታት ስለማይቆዩ ዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥን በማምጣት ላይ ያላቸው ሚና ውስን ነው። ኹለተኛው፣ እሳተገሞራ ካርቦንዳይኦክሳይድ ጋዝን በብዛት ስለሚለቅ ለዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል።”

አለሚቱ፡- “በጣም ግልፅ ሆኖልኛል መምህር! አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አለኝ። እሱም መጀመሪያ ላይ እንደነገሩኝ የፀሐይ መጠን መለዋወጥ ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እንደሆነ ነው። እስኪ ግልፅ ያድርጉልኝ።”

መምህር፡- “በጣም ጥሩ! ከፀሐይ የሚመነጨው የብርሃን መጠን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አይደለም። መጠኑ ይቀያየራል፤ ይጨምራል፤ ይቀንሳል” የፀሐይ ዑደት በመባል የሚታወቀውና በየአሥራ አንድ አመቱ የሚቀያየረው የፀሐይ ብርሃን ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይሆናል። ለምሳሌ ከ500 ዓመት በፊት ተከስቶ የነበረው የበረዶ ዘመን መንስኤው የፀሐይ ብርሃን መቀነስ እንደሆነ ታውቋል። አሁንም ቢሆን እየተከሰተ የመጣው የሙቀት መጨመር መንስኤው ከሰው ሠራሽ ችግር ይልቅ የፀሐይ ብርሃን መጨመር መሆኑን ሊቃውንት ያስረዳሉ።”

አለሚቱ፡- “ስለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎች ብዙ ቁም ነገሮችን ተረድቻለሁ መምህር። በጣም አመሰግናለሁ።

መምህር፡- ምንም አይደል ለወደፊትም እንዲብራራልሽ የምትፈልጊውን ጠይቂኝ። እኔም ለመረዳት ባደረግሽው ጥረት አመሰግንሻለሁ።”

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ 8ኛ ክፍል። (2007 ዓ.ም) በተለየ አቀራረብ ተሻሽሎ የተወሰደ።)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አለሚቱን ቃለመጠይቅ ለማካሄድ የገፋፋት ነገር ምንድን ነው?

ለ. የእሳተገሞራ ፍንዳታ የአካባቢ አየር የሚለወጥባቸውን ሹለት መንገዶች አስረዱ።

ሐ. ሰዎች “የዘንድሮስ ሙቀት አይጣል ነው!” ሲሉ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የሚያማርሩት ችግር መንስኤ ምን ይመስላችኋል?

መ. የሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችን በየአይነታቸው መድባችሁ ዘርዝሩ።

ሠ. መምህሮቻችሁን ወይም ባለሙያዎችን ጠይቃችሁ “የግሪን ሀውስ ክምችት” ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ።

ረ. የዓለም ሁሉ ማዕከል የትኛው አህጉር ነበር?

አቀላጥፎ ማንበብ

“አለሚቱና መምህሯ” በሚለው ምልልሳዊ ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

9.2.2 ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃለት ዐውዳዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

   ምሳሌ፦

   1. የውቅያኖስ <u>ጥልቀት</u> ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል።
   2. የእውቀት <u>ጥልቀትና</u> የሐሳብ ምጥቀት የሀገር ችግር ይፈታል።

ሀ. ውህድ	ሠ. መጠን	ቀ. ጠጣር	ነ. ዑደት
ለ. ነውጥ	ረ. ብክለት	በ. መፈራቀቅ	ኘ. ንብረት
ሐ. መንስኤ	ሰ. ይራቆታል	ተ. ብናኝ	
መ. ጎጂ	ሸ. ንፁህ	ቸ. ጋዝ	

2. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



መጻፍ

በ9.1.2 “ሰው ሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች” በሚል ርዕስ የጻፋችሁትን ድርሰት ከልሳችሁ ጻፉ።

9.2.3 መናገር

በቡድን ተመዳድባችሁ አንዱ ቡድን “ልጆችን ሥርአት አስይዞ ለማሳደግ ወሳኞች እናቶች ናቸው” የሚል ሐሳብ በመደገፍ፣ ሌላው ቡድን “ወሳኞች አባቶች ናቸው” የሚል ሐሳብ በመደገፍ ክርክር አካሂዱ።

ማስታወሻ

ክርክር ስታዘጋጁና ስታካሂዱ ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ስጡ።

- የምትደግፉትን ሐሳብ ምርጡ፣
- ለምትከራከሩበት ርዕስ በቂ መረጃ አሰባስቡ፣
- የመከራከሪያ ነጥቦችን ተራችሁን ጠብቃችሁ አቅርቡ፣
- ተከራካሪዎቻችሁን አክብሩ፣
- በተሰጠው የመከራከሪያ ጊዜ በአግባቡ ተጠቀሙ።

ሰዋስው

የሚከተሉትን ጥገኛ ሐረጎች ከሚስማሟቸው ነጠላ ዓረፍተነገሮች ጋር በማቀናጀት ድብልቅ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፦

ጥገኛ ሐረግ	ነጠላ ዓረፍተነገር	ድብልቅ ዓረፍተነገር
ሰው ሲከብር	ሞት ይፈራል	ሰው ሲከብር ሞት ይፈራል።

ጥገኛ ሐረጎች
1. መሬትን በአንድ ዘመን ቀዝቃዜ ሲያኮማትራት
2. የአየር ንብረት ከተለወጠ
3. አንዳንድ ነባር ዘሮች ከአዲስ የአየር ንብረት ጋር ለመስማማት የቅርፅና የይዘት ለውጥ ሲያደርጉ
4. በአንዳንድ አካባቢዎች የዉኃ መጥለቅለቅ ሲደርስ፣
5. በረዶ በመቅለጥ ከባሕር ከተቀላቀለ

ነጠላ ዓረፍተነገሮች
ሀ. በሌሎች አካባቢዎች ዝናብ በመቀነሱ ድርቅ ይከሰታል።
ለ. የጎርፍ ማጥለቅለቅን ያስከትላል።
ሐ. የተለያየ ጉዳት ያደርሳል።
መ. ሌሎች ነባር ዘሮች ግን ጠፍተዋል።
ሠ. በሌላ ዘመን መቀት ያነዳታል።

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “ለውጥ” የሚለው ቃል የሚቀየር ነገር መኖሩን ይጠቁማል። ከዚህ አንጻር። “የአየር ንብረት ለውጥ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል።

ለ. ኦዞን ምንድን ነው?

የአየር ንብረት ለውጥ



ሰዎች ለህልውናቸው ሲሉ በማያከናውኗቸው የማምረት ተግባራት የተለያዩ ጎጂ ነገሮች ይከሰታሉ። ለምሳሌ፦ ከፋብሪካ የሚወጡ ብናኞች፣ ዝቃጮችና ጋዞች ወደአየር ገብተው የአየር ብክለትን ይፈጥራሉ፤ የአየር ንብረት ለውጥም ያስከትላሉ። በተለይም ሰዎች ለአካባቢ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው፣ ለህልውናቸው አስጊ የሆነ አካባቢ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይጋረጡባቸዋል። ለእነዚህ ችግሮችም የግሪን ሀውስ ጋዞች መጨመርና የኦዞን ንጣፍ መሳሳት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

የግሪን ሀውስ ጋዞች የመሬት ሙቀትን ለመወሰን ያስችላሉ። በመሆኑም በስሬ ሀዋና በዝቂ ሀዋ ያለው የኬሚካሎች ይዘት የአየር ንብረትንና የመሬት አማካይ ሙቀት መጠንን ይወስናሉ። አነስተኛ መጠን ያለው ካርቦንዳይዶክሳይድና የዉኃ ቶን መጠን የመሬትን የሙቀት መጠን ይወስናሉ።

በተፈጥሮ ካርቦንዳይኦክሳይድ፣ የካርቦን ኡደት ተብሎ በሚታወቀው የካርቦን ቀለበታዊ የዝውውር ሂደት ውስጥ ይኖራል። በዚህ ዑደት ካርቦን የሚያመነጩና የሚያከማቹ ክስተቶች አሉ። ካርቦንን የሚያመነጩ እንደእሳተገሞራ ፍንዳታና የእፅዋትና እንስሳት አካል መበስበስ ናቸው። ካርቦንን የሚያከማቹት ደግሞ የምድር ላይና የባሕር ውስጥ እፅዋት፣ አፈር፣ የባሕር እንስሳትና የዉኃ አካላት ናቸው።

ካርቦንዳይኦክሳይድን በሰው ሠራሽነት የሚያመነጩ ሂደቶች አሉ። በድንጋይ ከሰልና በነዳጅ ዘይት የሚሠሩ ኃይል ማመንጫዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ እፅዋትን መቁረጥና ማቃጠል ይጠቀሳሉ። ከኃይል ማመንጫዎችና

ከተሽከርካሪዎች በጭስ መልክ የሚወጣው ካርቦንዳይኦክሰይዳ፣ ኃይል ለመፍጠር በሚከናወነው ኬሚካላዊ ሂደት የሚፈጠር ቆሻሻ ነው። በተጨማሪም በመጠኑ የሚገኙ ኦዞን፣ ሜቴን፣ ናይትረስኦክሳይድ፣ ክልሮፋሎሮ ካርቦን የሙቀት መጠንን ለመወሰን የሚያስችሉ የግሪን ሀውስ ጋዞች ናቸው። የፀሐይ ሙቀት በከባቢ አየር ውስጥ እነዚህን ጋዞች አልፎ ወደመሬት ይሰርጋል። ወደመሬት ከደረሰው የፀሐይ ሙቀት መካከል አብዛኛው በመሬት አማካይነት ወደሙቀት ይለወጥና ተመልሶ ወደላይ ይወጣል። ከፊሉ ወደጠፈር ሲወጣ ከፊሉ በግሪን ሀውስ ጋዞች ይዋጥና እንደገና ወደመሬት ይመለሳል።

የኦዞን ንጣፍ መሳሳት ለአየር ንብረት ለውጥ አንዱ ምክንያት ነው። ኦዞን ጋዝ ሲሆን ተግባሩም ሕይወት ላላቸው ነገሮች ጎጂ የሆነውን አልትራቫዮሌት የያዘውን የብርሃን ጨረር መከላከል ነው። የኦዞን ንጣፍ ከመሬት በላይ ከ19-48 ኪሎ ሜትር ርቀት ድረስ ይገኛል። ይህም ከፀሐይ የሚነሳውን አደገኛ ጨረርና ሙቀት በህይወታዊ ሀብት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ይከላከላል። በተጨማሪም የዝናብ ውኃን አጣርቶ ወደምድር በመላክ በአየር ውስጥ የሚገኙ ጎጂ ተሃዋሳያንን ያመክናል። ኦዞን በመሬት ላይ ቢሆን ኖሮ መርዛማ፣ በካይ፣ መጥፎ ጠረን ያለውን ለጤና ጠንቅ የሆነ ጋዝ ይሆን ነበር። ተፈጥሮ ይህንን ተቃርኖ ለማቻቻል ከመሬት 19 ኪሎ ሜትር በላይ እንዲገኝ አድርጋለች።

ከተሽከርካሪዎችና ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ናይትሮጅንኦክሳይድና ሌሎች ኦርጋኒክ ጋዞች በመዋሀድ ኦዞንን ይሠራሉ። ከዚያም ለመሬት ቅርበት ባለው የታችኛው የኦዞን ክፍል ላይ በመጠራቀም በሰውና በሌሎች እንስሳት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ።

በኦዞን ላይ ጥፋት ከሚያደርሱት ዋና ዋናዎቹ ክሎሮፍሎሮካርቦን፣ ብሮሚንሃይካርቦና ናይትሪስ ክሳይድ ናቸው። እነዚህን ለስፖንጅ፣ለማዳበሪያ፣ ለማቀዝቀዣ መስሪያዎች፣ ለሽቶና ለተባይ ማጥፊያ ማምረቻ በመጠቀም ወደከባቢ አየር እንዲገቡ ይደረጋል። ጋዞቹ ወደአየር ከገቡ በኋላ ከኦዞን ሞሉኪዩል ጋር መሳሳብን ይፈጥራሉ። በፍሎሮክሎሮካርቦን ውስጥ የሚለቀቁት እንደክሎሪን የመሳሰሉ ነገሮች በላይኛው የኦዞን ንጣፍ ከደረሱ አንድ ቅንጣት ብቻ ኦዞን ላይ ጉዳት ታደርሳለች። በዚህ ምክንያት የኦዞን መሳሳት ይፈጠራል።

በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ በተለያዩ መንገዶች ይከሰታል። በተለይ የሰው ልጆች ለመኖር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከሚሠሯቸው ተግባራት የሚወጡ ብናኞች፣ ኬሚካሎችና ጋዞች ወደአካባቢ አየር በመግባት ብክለት ይፈጥራሉ። በግሪን ሀውስ ጋዞች ክምችትና በኦዞን መሳሳት ምክንያት የሚፈጠረው የሙቀት መጠን መጨመር ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይሆናል።

(አማርኛ እንደአፍመፍቻ መጽሐፍ፣ 8ኛ ክፍል፣ ገጽ 194 ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አዞን የምን የምን ውህድ ነው?

ለ. ሰዎች ለህልውናቸው ብለው የሚሰሯቸው ተግባራት፣ በራሳቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ይመስላችኋል? እንዴት?

ሐ. የአዞን ንጣፍ መሳሳት ምንድን ነው? ለዓለማችን ያለው አንድምታ ምንድን ነው?

መ. የግሪን ሀውስ ጋዞች የሚባሉትን ዘርዝሩ።

ሠ. የግሪን ሀውስ ጋዞች የሚሞቁት ከፀሐይ በቀጥታ በሚመጣ ሙቀት ነው? እንዴት?

ረ. ስለተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ የካርቦን አመነጫጨት አስረዱ።

አቀላጥፎ ማንበብ

"የአየር ንብረት ለውጥ" በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ የማንበብ ፍጥነት ተለማመዱ።

9.3.2 ቃላት

1. በ"ሀ" ረድፍ ያሉትን ቃላት/ሐረጋት በ"ለ" ረድፍ ይበልጥ ከሚቀራረቡት ጋር አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ድንጋይ	ሀ. ንብረት
2. ነዳጅ	ለ. ዘይት
3. ክባቢ	ሐ. ንጣፍ
4. ሀይል	መ. አመንጪ
5. አደገኛ	ሠ. ጨረር
6. አዞን	ረ. ሙቀት
7. አየር	ሰ. ከሰል
	ሸ. አየር

2. ባለሙያ በመጠየቅ የሚከተሉትን ሐረጎች ይዘት አስረዱ።

   ሀ. የኦዞን ንጣፍ

   ለ. አማካይ ሙቀት

   ሐ. የአየር ንብረት

3. የሚከተሉትን ቃላት ቀጥሎ በተሰጠው ጽሑፍ ቁጥሮች ላይ በማስገባት ዐውዳዊ ፍቻቸውን አሳዩ።

ህልውናቸው	ኦዞን	ዝቃጭ	ዝቁ
ህዋ	ንጣፍ	ስሬ	ይሰርጋል
በካይ	መርዛማ	ብርሃን	

የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ይህም ሰዎች 1 ሲሉ የተለያዩ ፋብሪካዎችን ይከፍታሉ፤ ከተሽከርካሪዎች የሚወጡ 2 የሆኑ 3 ወደአየር ይቀላቀላሉ። በ 4 ላይ የሚለቀቀው ኬሚካል በ 5 እና 6 የሞለኪዩል ይዘት በአየር ንብረትና በመሬት አማካይ ሙቀት መጠንን ይወስናሉ። በዚህም 7 ጋዞች ወደአየር ከገቡ በኋላ የ 8 ሞለኪውሎች ጋር ይሳሰባሉ። በዚህም የኦዞን 9 መሣሣት ይፈጠራል። ይህ ደግሞ የፀሐይ 10 ጨረር ወደመሬት 11። በዚህ የአየር ንብረት ለውጥ መምጣት ምክንያት ይሆናል።

መጻፍ

በቡድን ተመዳድባችሁ በ9.2.3 “ሰውሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች” በሚል ርዕስ በግል የጻፋችሁትን ድርሰት በማሻሻል አንድ የቡድን ድርሰት ጻፉ።

9.3.3 መናገር

በሦስት ቡድን ተመዳደቡ። የአንዱ ቡድን አባላት “የልማት አምባሳደር” ፣ ኹለተኛው ቡድን “የሰላም አምባሳደር”፣ የሦስተኛው ቡድን አባላት ደግሞ “የባህል አምባሳደር” ይሁኑ። በመቀጠል የንግግር ጽሑፍ በማዘጋጀት በተሰጣችሁ ሀላፊነት ልማት፣ ሰላምና ባህል ለሀገርና ለሕዝብ ያላቸውን ጠቀሜታ በሚመለከት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

ሰዋስው

ጥገኛ ሐረጎችንና ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በማቀናጀት ዐምስት ድብልቅ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

ጥገኛ ሐረግ	→	ዛፍ ሲጠፋ
ነጠላ ዓረፍተነገር	→	እምባጮ አድባር ይሆናል።
ድብልቅ ዓረፍተነገር	→	ዛፍ ሲጠፋ እምባጮ አድባር ይሆናል።

ምዕራፍ 10 ድራማ

10.1.1 አንብቦ መረዳት

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 1)

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “የሠርጉ መዘገዝ” ከሚለው ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም “ገፀባሕርያት፣ መቼት፣ ድርጊት፣ ግጭት አላባውያን የሚባሉትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ።

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 1)

መጋረጃ ሲከፈት ሰፊው ሳሎን፣ ሶፋ፣ ኮሜዲኖና የመሳሰሉ ዕቃዎች አሟልቶ ይታያል። በስተቀኝ ከውጭ የሚያስገባ ሌላ በር አጠገብ በመጋረጃ የተሸፈነ መስኮት ይታያል። አቶ በላይሁን ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው፣ በጭንቀት ፊታቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ በያዙት የሂሳብ ማሽን ላይ አፍጥጠዋል። እስክርቢቶና ወረቀት ፊት ለፊታቸው አስቀምጠዋል። ሙሉ ልብስ ለብሰዋል። ክራባት አድርገዋል፤ ፀጉራቸው ነጭ ወረር ያደረገው ሆኖ ወደኋላ ተበጥሯል።

አቶ በላይሁን፡- (ሂሳብ ማሽኑን ቁጭ አድርገው እስክርቢቷቸውን ይይዛሉ። ወረቀት ላይ ከመዘገቡ በኋላ እንደገና ማሽኑን አንስተው ይነካካሉ። እጃቸውን አገጫቸው ላይ ያደርጉና ፊታቸውን በጭንቀት አጨፍግገው ይቆያሉ።) ውይ!... ውይ!... ውይ!... (ከተቀመጡበት ይነሳሉ።) ውይ!... ውይ!... ውይ!... (ቦታ ቀይረው ይቀመጣሉ። በሩ ተከፍቶ ወይዘሮ አየለች ይገባሉ። ደልደል ባለ ሰውነታቸው ላይ የሀገር ልብስ ለብሰው ፈካ ባለ ሻሽ ፀጉራቸውን ሸብ አድርገው በፈገግታ ተሞልተዋል።)

ወ/ሮ አየለች፡- ውይ! በላይዬ? ብቻህን ነህ እንዴ?

አቶ በላይሁን፡- ሄዱ'ኮ ሁሉም ሠርጌን፣ ድግሴን በልተው ሄዱ'ኮ... ማን ቀረ?

ወ/ሮ አየለች፡- እሱማ ያለ ነው፣... ሰው ለምዶ በአንዴ ቤቱ እንዲህ ጭር ሲል፣

አቶ በላይሁን፡- እንደሱ ማለቴ አይደለም፤ እኔና እዳዬ ብቻ ቀረን! ሰው ዓለሜን አይቶ ድግሴን በልቶ ሄደ፤ እኔ መከራዬን ላይ ነው... የሰው ዕዳ፣ ብድር መከራዬን ሊያሳየኝ ነው ማለቴ ነው፤ ይገባሻል?

ወ/ሮ አየለች፡- ጀመርክ እንግዲህ!

አቶ በላይሁን፡- ጀመረኝ!... ልጀምር እንጂ ...! ገና ቤት መልሱ ሳይደገስ... የሰርጉ ድግስ ሽታ ሳይጠፋ ጀመረኝ! ባለዕዳው ሁሉ በስልክ አጣደፈኝ... መቀመጫ አሳጣኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- ምናባታቸው ሊሆኑ? ኤዲያ...!

አቶ በላይሁን፡- ዕቃውን ካልመለሳችሁ፣ ሌላ ውል ፈፅሙ ነው የሚሉት! (በመቆጣት)

ወ/ሮ አየለች፡- ተዋዋል እንጂ! ታዲየ ሰው ምን ላይ ይቀመጣል?

አቶ በላይሁን፡- ለምን ይመጣል? ለምን ይቀመጣል? በቃ መልሱ ቢቀርስ?

ወ/ሮ አየለች፡- ምን? (በንዴት ጦፈው) በል አስበላኝ!... አስቦጭቀኝ! በል እንጂ!

አቶ በላይሁን፡- አልልም! ምን እምለው አለኝና? በቃ! (ያቀረቅራሉ)

ወ/ሮ አየለች፡- "ወይጉድ!... በፊት ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ" ... አሉ (ወደ ውስጥ እያገቡ)

አቶ በላይሁን፡- ፊቱን ይደቆስ ይደለዝ ያልሸው... አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው... ነው ነገሩ። (ስልክ ይጮሃል፣ከውጪ ደመና ይገባል፣ ከውስጥ መሠረት ትወጣለች። መሠረት የቤት ሠራተኛ ስትሆን፣ የለበሰችው ቀሚስ በዉኃ ረጥቧል። ደመና ራሰበራ፣ የተዝረከረከ አለባበስ ያለው ሸምገል ያለ የቤቱ ዘበኛ ነው።)

ደመና፡- (ሮጦ ስልኩን ያነሳና) ሀሎ...ሀሎ... ማንልበል? አሉ...! እሺ (ስልኩን ይዘጋል)

አቶ በላይሁን፡- ማን ነው የደወለው ደመና?

ደመና፡- በላቸው ነው።

አቶ በላይሁን፡- እሱ ደሞ ምን አለ?

ደመና፡- ከአርብ ጀምሮ ወንበሮችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጋዘኩበትን ሂሳብ ይስጡኝ ነው የሚለው።

አቶ በላይሁን፡- ምነው ጅብ ባጋዘኝ ዘንድሮ!?

ደመና፡- ቅድም እኮ! የሻውም ደውሎ ነበር።

አቶ በላይሁን፡- ምነው ደመና ባሳዝንህ!... ኧረ! እየራራህልኝ! ልፈንዳብህ ነው'ኮ...?

ደመና፡- ኧረ አዝኜ ነው ጋሽዬ! ከረር መረር ያሉትን ትቼ ነው።

አቶ በላይሁን፡- በማርያም አታዝንብብኝ፣ ውጣልኝ!

ደመና፡- እሺ....ኢ!... ይ (ያዝናል) ምነው ደምኜ በቀረሁ...ዋ! (ሊወጣ ሲል ወይዘሮ አየለች ከውስጥ ብቅ ይላሉ፤ ቆም ይላሉ። ከወደውስጥ መሠረት ብቅ ትላለች።)

መሠረት፡- እትዬ...እትዬ...ዓለም መጥታ ነበር...፤" መንቀሳቀሻዬን ቀምተው ምነው ዝም አሉኝ?" ብላለች።

ወ/ሮ አየለች፡- ኤዲያ! ይቺ ደግሞ! ሰለንዳቢስ!... (ይቀመጣሉ) አንቺ ደሞ ለኔ ከምትነግረኝ ለበላይ አትነግሪውም ታዲያ?

አቶ በላይሁን፡- እኔ ላይማ ዘነበብኝ! ያካፋብሽ ብላ ይሆናል!? ዳፋው እንዳይገለኝ!

ወ/ሮ አየለች፡- እኔ እምለው... ስንጋዎቹን አመጣህ ወይ...?

አቶ በላይሁን፡- (እንደቀረቀሩ) እኔ...እንጃ...

ወ/ሮ አየለች፡- ታዲያ መቼ ሊመጣ ነው? የምን ዳር ዳርታ ነው እቴ?

አቶ በላይሁን፡- ወይ መፈናፈኛ ማጣት! ወይ መጨናነቅ!

ወ/ሮ አየለች፡- እ... ህ...! (ፋታ) አንቺ መሠረት!... መሠረት! ኧረ መሠረት!

መሠረት፡- (ብቅ ትላለች) እመት እትዬ...

ወ/ሮ አየለች፡- ምሳ አቅርቢ፣ (አቶ በላይሁን ተነስተው ወደበሩ መራመድ ይጀምራሉ) ወዴት ነው? ምሳ ብላ እንጂ!

አቶ በላይሁን፡- አልበላም በቃኝ። (ወደበሩ ይወጣሉ)

ወ/ሮ አየለች፡- እኔም ስመለስ እበላለሁ። ወደሱቅ ልሂድና አንዳንድ ነገሮችን ልገዛ (ወደውጪ ይወጣሉ።)

መሠረት፡- በሠርግ መዘዝ የዕዳ ቁልልና መጨናነቅ ይገርማል...

ደመና፡- እኔን የሚገርመኝ፣ ወድዳው እሱ ቤት ከርማ የዓመት ልጅ ካደረሰች በኋላ እንደገና ሽማግሌ ላኩ፣ ከዚያ በኋላ "ወደናል... ከወደደች" አይበቃም ነበር?

መሠረት፡- ወግ ነዋ?

ደመና፡- ምን ይሄ ይገርማል። ሆሆይ...! እሁድ የሄደችውን፣ እንደገና ቤት መልስ ብለው ሊመልሱ አይደል እንዴ?

መሠረት፡- እምቢ ካሉ ወደቤት አስገብቶ ልጁን ማሳየት ነዋ! በቃ! (እየተሳሳቁ ሲያወሩ በር በኃይል ተበርግዶ አቶ በላይሁን ዘወር ሳይሉ በፍጥነት እየተራመዱ ወደውስጠኛው ክፍል ይገባሉ። መሠረትና ደመና ደንግጠው ወደውጭ ይወጣሉ። አቶ በላይሁን በክፍሉ ውስጥ ትንሽ ከተንጎራደዱ በኋላ ወደውጪ ሲወጡ ከወይዘሮ አየለች ጋር በመንገድ ላይ ይገናኙና ተፋጠው ይቆማሉ።) መጋረጃው ይዘጋል።

(አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ፣ 8ኛ ክፍል፣ 2007፣ ገፅ 219-222 የተወሰደ)

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

   ሀ. "ሳሎኑ ሶፋ፣ ኮሜዲኖ እቃዎች አሟልቷል።... አቶ በላይሁን ሙሉ ልብስና ከረባት አድርገው በጭንቀት ፊታቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ ከሂሳብ ማሽን ላይ አፍጠዋል። እስክርቢቶና ወረቀት ፊት ለፊታቸው አስቀምጠዋል።" የሚለው ገለጻ ዋና መልዕክቱ ምንድን ነው?

   ለ. "አቶ በላይሁን... በጭንቀት ፊታቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ ሂሳብ ማሽኑ ላይ አፍጥጠዋል... ወይዘሮ አየለች... የሀገር ልብስ ለብሰው ፈካ ባለ ሻሽ ፀጉራቸውን ሸፍነው በፈገግታ ተሞልተዋል" የሚለው አገላለጽ ስለተውኔቱ ምን የሚጠቁም ይመስላችኋል? ዋናዎች ገፀባሕርያት እነማን ናቸው?

   ሐ. በዋናዎቹ ገፀባሕርያት መካከል የተፈጠረ ግጭት ምንድን ነው? የግጭቱ መንስኤ ምን ይመስላችኋል?

   መ. ለመጀመሪያ ጊዜ ግጭት መፈጠሩን የሚጠቁመውን የገጸባህሪያት ምልልሶች ለይታችሁ ጻፉ።

ሠ. በተውኔቱ ግጭቱ እያደገ መሄዱን የማያሳዩ ምልልሶችን ለይታችሁ ጻፉ።

ረ. የአንድ ተውኔት ታሪክ የመጀመሪያ፣ የመካከልና የመጨረሻ ክፍልን እንዴት መለየት ይቻላል? ለይቶ ማወቅ ምን ጠቀሜታ አለው?

2. በታሪኩ መጀመሪያ የተካተቱትን አላባውያን በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

መጀመሪያ		መካከል		መጨረሻ	
አላባውያን	ዝርዝር	አላባውያን	ዝርዝር	አላባውያን	ዝርዝር
ገፀባሕርያት		የድርጊት ማደግ መወሳሰብ			
መቼት					
ችግር		ጡዘት			

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሠርጉ መዘዝ (ትዕይንት 1)” በሚለው ተውኔት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

10.1.2 ቃላት

1. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላት/ሐረግ ከምንባቡ ውስጥና ውጭ ያላቸውን ፍቺ ስጡ።

ሀ. <u>መንቀሳቀሻዬን</u> ቀምተው ምነው ዝም አሉኝ?

ለ. ፀጉራቸው ሸበት <u>የወረረው</u> ሆኖ ወደኋላ ተበጥሯል።

ሐ. ዕቃውን ካልመለሳችሁ ሌላ <u>ውል</u> ፈርሙ ነው የሚሉት።

መ. እኔ ላይማ <u>ዘነበብኝ</u>! ያካፋብሽ ብሎ ነዋ!

ሠ. አቶ በላይሁን እንደገና <u>ሸማግሌ ላከ</u>።

ረ. አበዳሪዎቹ ገንዘባችንን መልሱ በማለት አቶ በላይሁንን <u>መፈናፈኛ</u> አሳጧቸው።

2. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍቻቸው ዓረፍተነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- ደልደል ያለ → ወፈር ያለ → ተመሳሳይ ፍቺ

ወይዘሮ አየለች ወፈር ባለ ሰውነታቸው የሀገር ልብስ ለብሰዋል።

ደልደል ያለ → ከሳ ያለ → ተቃራኒ ፍቺ

ወይዘሮ ዓለምነሽ ከሳ ባለ ሰውነታቸው ላይ የለበሱት ቀሚስ ያምራል።

ሀ. ማጋዝ ሐ. ተሸፈነ ሠ. አጣደፈኝ

ለ. ቁልል መ. ተበጥሯል ረ. እንዳቀረቀሩ

መጻፍ

ሀ. አንድ የተውኔት ርዕስ መርጣችሁ የተውኔቱን የመጀመሪያውን ክፍል ጻፉ።

ለ. በጻፋችሁት ተውኔት የመጀመሪያ ክፍል ያሉትን አላባውያን በሚከተለው ሠንጠረዥ "መጀመሪያ" በሚለው አምድ ሥር ዘርዝራችሁ ጻፉ።

መጀመሪያ		መካከል		መጨረሻ	
አላባውያን	ዝርዝር	አለባውያን	ዝርዝር	አላባውያን	ዝርዝር
ገፀባሕርያት		የድርጊት ማደግ መወሳሰብ			
መቼት					
ችግር		ጡዘት			

10.1.3 ማዳመጥ

ያልተፈረደባት ነፍስ

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዛሬ የምታዳምጡት "ያልተፈረደባት ነፍስ" በሚል ርዕስ የተጻፈ ተውኔት ነው። ከርዕሱ ተነስታችሁ ተውኔቱ ስለምን እንደተጻፈ ገምቱ።

ለ. "ያልተፈረደባት ነፍስ" የሚለውን ሐረግ ፍቺ ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ከአሁን በፊት በሬዲዮ ካዳመጣችኋቸው ወይም በቴሌቪዥን ከተመለከታችኋቸው ድራማዎች የምታስታውሷቸውን ገፀባሕርያት በመጥቀስ ስለባህሪያቸው ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ተውኔት መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. “የሰው ልጅ ለመተዋወቅ አንድ ቀን ይበቃዋል” በሚለው የመስፍን ሐሳብ ትስማማለችሁ? ለምን?

ለ. “መስፍን እስከመቼ በድብብቆሽ እንኖራለን” ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

ሐ. አቶ ክንፈ፣ ሃይማኖት ከመስፍን ጋር ቶሎ ግንኙነት እንድትፈፅም የፈለጉት ለምን ይመስላችኋል?

መ. ሃይማኖት መስፍንን የማትወደው ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. እናንተ ሃይማኖትን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ረ. በተውኔቱ በጣም ያንጓጓችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ሰ. መስፍን፣ ብዙዬ በኤች. አይ. ቪ ኤድስ መያዟን ስትነግረው ያስደነገጠው ምንድን ነው?

ሸ. ብዙዬና ሃይማኖት እህትማማቾች መሆናቸውን መስፍን ያላወቀው ለምን ይመስላችኋል?

ቀ. ከተውኔቱ ምን ተረዳችሁ?

ሰዋስው

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ጥገኛ ሐረጎች ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- “እኔ ላይ ሲዘንብብኝ፣ አንቺ ላይ ያካፋል” በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ

“እኔ ላይ ሲዘንብብኝ” የሚለው ጥገኛ ሐረግ ነው።

ሀ. አቶ በላይሁን በጭንቀት ተውጠው የሂሳብ ማሽን ላይ አፍጥጠዋል።

ለ. ሰው አለሜን አይቶ እኔ መከራዬን ላይ ነው።

ሐ. እቃውን ካልመለሳችሁ ሌላ ውል ፈጽሙ።

መ. የሀገር ልብስ ለብሰው ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቷል።

ሠ. መሠረት የቤት ሠራተኛ ስትሆን ልብሷ በውኃ ረጥቧል።

ረ. ደመና ሸምገል ያለ የቤት ዘበኛ ነው።

ሰ. ወንበሮችና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጋዘኩበትን ሂሳብ ይስጡኝ።

ሸ. አቶ በላይነህ ተነስተው ወደበሩ መራመድ ይጀምራሉ።

ቀ. እኔ ስመለስ ምሳ እበላለሁ።

በ. የዓመት ልጅ ካደረሰች በኋላ ሽማግሌ ላክ።

10.2.1 አንብቦ መረዳት

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 2)

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስለተወኔት አጻጻፍ የምታውቁትን ተናገሩ።

ለ. በተውኔት ጽሑፍና በሌላ ጽሑፍ መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 2)

አቶ በላይሁንና ወ/ሮ አየለች ተከታትለው እንደወጡ ምሕረት ወደቤት ይገባል። ጠቆር ያለ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ ወጣት ነው። ቆም ብሎ ከአቶ በላይሁን ጋር ላፍታ ከተያየ በኋላ ቅሬታ እየተነበበት አልፏቸው ይገባል። አቶ በላይሁን መለስ ብለው ከገረመሙት በኋላ ትተውት ከቤት ይወጣሉ።

መሠረት፡- ምሳ ላቅርብልህ?

ምሕረት፡- አይ! አልበላም። (ስልክ ይጮሀል፤ መሠረትና ደመና ከጓዳ መጥተው ስልኩን ለማንሳት ሲተያዩ ምሕረት ስልኩን ያነሳዋል።) ስልኩን ዘግቶ ወይ ጉድ! እስቲ በሠርግ መዘገዝ የዕዳ ቁልል... (ይተነፍሳል፤ ወዲያውኑ አቶ በላይሁን በጣም እየተናደዱ ከውጭ ወደቤት ገብተው እሶፋው ላይ ዝም ብለው ይቀመጣሉ።)

አቶ በላይሁን፡- (ራሳቸውን በጣታቸው በንዴት መታ መታ ያደርጋሉ።) "ውይ! ውይ! ውይ! ማነህ ምሕረት!? በዚህ ቁጥር ደውልልኝ" በማለት ቁጥር ይነግሩታል። ፈጠን በል! ፈጠን በል! እናትህ እናቴ ላይ ሳትወጣ ደውልልኝ! (ይደውለል)

ምሕረት፡- ሃሎ! ቆይ አንድ ጊዜ...፤ ምን? (አባቱን ያያል)

አቶ በላይሁን፡- "መልሱ አልቀረም፤... ወንበሮቹ እስከመልሱ ይቆያሉ፤ ብሏል በላይ" በለው።

ምሕረት፡- (የተባለውን ይላል። ስልኩን ይዘጋል)

አቶ በላይሁን፡- ያው!... ነፍስሽ መለስ ትበል...አዎ! የኔ ነፍስ ግን በዕዳ ተጨፍልቃ ተጨማልቃ ወይ በአፌ... ወይ በጆሮዬ ዱብ ትልልሻለች። ወይኔ በላይሁን! (ረዥም ዝምታ)

ምሕረት፡- ኦ...አባባ!

አቶ በላይሁን፡- ምነው? አስተምረኝ ልትል ነው እንደልማድህ?

ምሕረት፡- በዚህ ስዓት አንተ ከዕዳ የምትወጣበት፣ ከጭንቀት የምትድንበት እንጂ፣ የኔ መማር አላሳሰበኝም።

አቶ በላይሁን፡- ጎሽ!... የኔ ልጅ! እሽ ለምን ጠራኸኝ?

ምሕረት፡- ቪዲዮ ቀራጩ ደውሎ ነበር።

አቶ በላይሁን፡- ፊልሙን የቀረጸው ነው አይደል?

ምሕረት፡- አዎ!

ወ/ሮ አየለች፡- እግዜር ይስጠው... ሠርጉን ሠርግ ያስመሰለው እሱ ነው።

አቶ በላይሁን፡- አቤት!... አቤት! አዳሜ ቀበቶውን እያላላ ድግሴን ሲበላ... በሶፍት ግንባሩን እየጠረገ ሲያገሳ... ወንበር ላይ ቆሞ ባውዛ እያበራ ስለዞረ ነው? ወይኔ በላይ! መሠረት ያቺን የምጠጣትን አምጭልኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- ኧረ እህሉን ብላ ቀድመህ?

አቶ በላይሁን፡- የለም! የለም! አልበላም፤ አሞኛል። (መሠረት የታዘዘችውን ይዛ ትገባለች) ለመሆኑ ስንት ነው አለ?

ምሕረት፡- 600 ብር

አቶ በላይሁን፡- (ባለቤታቸውን) እንዲህ ነው እንዴ የተነጋገርሽው አንቺ? ባንድ ሰው አንድ ብር?

ወ/ሮ አየለች፡- በሀገር ዋጋ ትሠራለህ ነው ያልኩት።

አቶ በላይሁን፡- አገሬውን ታስከፍይ እንደሆነ አያለሁ። ወይ! ወይ! (መሠረት አረቂውን በመለኪያ ትቀዳላቸዋለች።)

ምሕረት፡- እና እስከኢዲቲንጉ አንድ ሺህ ብር... የመልሱን ቪዲዮ ቀረፃ ከሠራ ደግሞ....

አቶ በላይሁን፡- ምነው የበላሁት በተመለሰ?... እሺ?

ምሕረት፡- አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር።

አቶ በላይሁን፡- (ዝም ብለው እየጠጡ) ስማ ኢዲቲንጉን ይተወው።

ወ/ሮ አየለች፡- እኮ ለምን?

አቶ በላይሁን፡- መጀመሪያ እኔ ያለብኝ ዕዳ ኦዲት ይደረግ።

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴት! እንዴት! የመልሱ ዕለት ቤተዘመድ የሚያይ መስሎኝ?

አቶ በላይሁን፡- እዩ ካላልን በግድ እንይ አይል ቤተዘመድ? (እየጨሱ ዝም ብለው ቀድተው ይጠጣሉ) እሺ!... መልሱ እንዳይቀረፅ! አይጠቅምም።

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴት አይጠቅምም?

አቶ በላይሁን፡- ድግግሞሽ ነዋ! የሠርጉ ዕለት ይበሉ ከነበሩት ገሚሶቹ በድጋሚ ሲበሉ ነው የሚታየው። የገበታ መዓት ምን ይሠራል?

ወ/ሮ አየለች፡- አይሆንም!

አቶ በላይሁን፡- (ከተቀመጡበት ተነስተው እያዞረባቸው ወደኋላቸው ተራምደው ቆም እንዳሉ ደመና ዘው ብሎ ይገባል)

ደመና፡- ጋሽዬ!

አቶ በላይሁን፡- አቤት! (ያቀረቅራሉ)

ደመና፡- እ...! (ወ/ሮ አየለች አፉን ጥርቅም አድርገው ዝም ካደረጉት በኋላ በጀርባው ወለሉ ላይ ይጥሉታል። አቶ በላይሁን እንዳቀረቀሩ ወደበሩ ተንደርድረው ደመናን ረግጠው ሲወጡ ባለቤታቸውም ተከታትለው ይወጣሉ። ምሕረትና መሠረት በደመና ሁኔታ ይሳሳቃሉ። ደመና እንደተኛ በጎኑ ገልበጥ ብሎ እጁን ይደገፋል) መሠረት አረቂ ትቀዳለታለች።

መሠረት፡- (ጠርሙስ አምጥታ እየሳቀች በመለኪያ ትቀዳለታለች) ተዘረርክ አይደል?

ደመና፡- ኧረ ጅዶ? አንዳንዴ ሌሊት አረቄ ጭንቅላቴ ላይ ወጥቶ የዘለልኩትን ጉድጓድ ጧት ሳዬው ይገርመኛል። እሜቴም'ኮ ሐሳብና ጭንቀት አናታቸው ላይ ወጥቶ እንጂ፣ በደህናው ቀን አይዘርሩኝም ነበር።

ምሕረት፡- (ለራሱ) እስኪ! ቢቀርስ?

ደመና፡- ምን ያድርጉት!?... ወግ ነው... የማህበረሰቡ ልማድ

ምሕረት፡- እንዴት?

ደመና፡- ህዝቡ ታልበላ! እውቅና አይሰጥማ!... ደግሰህ ካልዳርክ!... ልጅህ ጋለሞታ፣ የልጅ ልጅህ ደግሞ ዲቃላ ነው የሚባሉት። ከደገስክ ደሞ በደንብ ነው። ካለዚያ ሠርግህ ቦጭቧጫ... አንተ ደግሞ ቆጥቋጣ ትባላለህ።

ምሕረት፡- ይገርማል!

ደመና፡- ለልቅሶም ቢሆን ይኸው ነው። ለሞት አርባ፣ ለሙት ዓመት... እየደገስክ ሐውልት ሠርተህ ካላስመረቅክ እርም በላ እየተባልክ በየቦታው ትቦጨቃለህ።

መሠረት፡- ከሌለኝስ?

ደመና፡- ነይ ቅጂ! (ትቀዳለች) ትዘጋጃለሽ! አሁን የኔ አባት... መብራት፣ ዉኃ እሚከፍለው እያጣ ይቆረጣል እንጂ... የፈለገ ቢሆንም የዕድር ክፍያ አያቋርጥም ነበር። "ሂድ ዕድር ክፈል" ይለኝ ነበር። እውነትም ሲሞት... ድንኳን ተጣለ፤ ተበላ፤ ዕድሩ በሰጠን ገንዘብ ሐውልት ተሠራ፤... ተመረቀ።

ምሕረት፡- እና አባትህ ምን ተጠቀሙ?

ደመና፡- በአባቴ መቀለዴ እንዳይመስልህ... ቀስቅሼ ብጠይቀው ደስ ይለኝ ነበር። ታሞ...፣ ጠያቂ ጠፍቶ፣ መታከሚያ አጥቶ ሲሞት ሰው ሲተራመስ፣ እህል ተርፎ ሲፈስ፣ በኋላ እኛ የምንበላው አጣን፣ እባካችሁ ተውኝ። (ድንገት ወ/ሮ አየለችና አቶ በላይሁን እንደተኮራረፉ ወደቤት ይገባሉ) መጋረጃ ይዘጋል።

(አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ፤ 2007፣ ገፅ 231-233- የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "የገበታ መዓት ምን ይሠራል?" የሚለውን አገላለፅ አብራሩ።

ለ. ደመና ዕድርን በተመለከተ ከተናገረው ምን ተረዳችሁ?

ሐ. የተውኔቱ ግጭት በዋናነት የተፈጠረው በየትኞቹ ገፀባሕርያት መካከል ነው? የግጭታቸውስ መንስኤ ምን ይመስላችኋል?

መ. አቶ በላይሁንና ወይዘሮ አየለች የምህረትን አስተምሩኝ ጥያቄ ትተው ሠርግ በመደገስ ከፍተኛ ዕዳ ውስጥ መዘፈቃቸው ምንን ያሳያል?

ሠ. አቶ በላይሁን እንደማንኛውም ወላጅ ሠርገው የዳሯትን ልጅ ምላሽ መጥራት የማይፈልጉ ለምን ይመስላችኋል?

ረ. በተውኔቱ አንደኛ ክፍል የተውኔቱን መጀመሪያ የሚያሳዩ አላባውያንን ሠንጠረዥ ላይ አስፍራችኋል። አሁን ደግሞ የተውኔቱን "የመካከለኛ ክፍል" የሚያሳዩ አላባውያንን ቀጥሎ ባለው የቢጋር ሠንጠረዡ አስፍሩ።

መጀመሪያ		መካከል		መጨረሻ	
አላባውያን	ዝርዝር	አለባውያን	ዝርዝር	አላባውያን	ዝርዝር
ገፀባሕርያት		የድርጊት ማደግ መወሳሰብ			
መቼት					
ችግር	ጡዘት				

አቀላጥፎ ማንበብ

በቡድን በቡድን ሆናችሁ የሚከተለውን ዝርዝር መስፈርት(ሩብሪክ) በመጠቀም "የተገቢ አገላለጽ" ንባባችሁን እየመዘናችሁ፣ የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት 2 ተውኔትን አንብቡ።

የአገላለጽ ንባብ መመዘኛ

ደረጃ 4፡- (እጅግ በጣም ጥሩ)

- ሙሉ በሙሉ ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ ማንበብ፣
- ሙሉ በሙሉ የገፀባሕርያትን ንግግር አስመስሎ ማንበብ፣
- ሙሉ በሙሉ ሳይቆሙ ቃላትን በትክክል በመጥራት ማንበብ።

ደረጃ 3፡- (በጣም ጥሩ)

- በአብዛኛው ሥርዓተነጥቦችን ጠብቆ ማንበብ፣
- ጥቂት ሥርዓተነጥቦችን ጠብቆ አለማንበብ፣
- በአብዛኛው የገፀባሕርያትን ንግግር አስመስሎ ማንበብ፣

- ጥቂት ገፀባሕርያት አስመስሎ አለማንበብ፣
- በአብዛኛው ሳይቆሙ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣
- ጥቂት መቆምና ቃላትን በትክክል አለመጥራት።

ደረጃ 2፡- (ጥሩ ወይም ደህና መሻሻል ያለበት)

- በከፊል ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ ማንበብ፣
- በከፊል ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ አለማንበብ፣
- በከፊል የገፀባሕርያትን ንግግር ማስመሰልና በከፊል አለማስመሰል፣
- በመጠኑ በየመካከሉ መቆም፣
- ቃላትን በትክክል አለመጥራት።

ደረጃ 1፡- (ጀማሪ ብዙ መሻሻል ያለበት)

- በብዛት ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ አለማንበብ፣
- የገፀባሕርያትን ንግግር አስመስሎ አለማንበብ፣
- በብዛት በየመካከሉ መቆም፣
- ቃላትን በትክክል አለመጥራት /አለማንበብ።

10.2.2 ቃላት

1. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. አዳሜ ቀበቶውን እያላላ ድግሴን ሲበላ... ወንበር ላይ ቆሞ ባውላ እያበራ ስለዞረ ነው?

   ለ. ኧረ እህሉን ብላ ቀድመህ?

   ሐ. በሀገር ዋጋ ትሠራለህ ነው ያልኩት።

   መ. መጀመሪያ እኔ ያለብኝ ዕዳ አዲት ይደረግ።

   ሠ. እየጨሱ ዝም ብለው ቀድተው ይጠጣሉ።

   ረ. የሠርጉ ዕለት ይበሉ ከነበሩት ገሚሶቹ በድጋሜ ሲበሉ ነው የሚታየው።

   ሰ. የገበታ መዓት ምን ይሠራል?

   ሸ. በደህና ቀን አይዘርሩኝም ነበር።

ቀ. ደግሰህ ካልዳርክ!... ልጅህ ጋለሞታ የልጅ ልጅህ ደግሞ ዲቃላ ነው የሚባሉት።

በ. ከደገስክ ደግሞ በደንብ ነው፣ ካለበለዚያ ሠርግህ ቦጭቧጫ... አንተ ደግሞ ቆጥቋጣ ትባላለህ።

2. በሚከተሉት ቃላት በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍቻቸው ዓረፍተነገር መስርቱ።

ሀ. ገረመሙት

መ. ተራምደው

ለ. ይጥሉታል

ሠ. ጓዳ

ሐ. ላፍታ

መጻፍ

ሀ. የጀመራችሁትን ተውኔት የመካከል ክፍል ጻፉ።

ለ. የተውኔቱን "የመካከል ክፍል የሚያሳዩ አላባውያንን ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

መጀመሪያ		መካከል		መጨረሻ	
አላባውያን	ዝርዝር	አለባውያን	ዝርዝር	አላባውያን	ዝርዝር
ገፀባሕርያት		የድርጊት ማደግ መወሳሰብ			
መቼት					
ችግር		ጡዘት			

10.2.3 መናገር

በ"የሠርጉ መዘገጃ" ትዕይንት 2 ተውኔት" የወንዶችን ገፀባሕርያት ወንዶች፣ የሴቶችን ገፀባሕርይ ሴቶች፣ ንግግራቸውን አስመስላችሁ በክፍል ውስጥ በቃላችሁ ተናገሩ።

ሰዋስው

ሀ. አያያገሮችን በመጠቀም ኹለት ተዛማጅ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

አቶ በላይሁን በመልሱ ጉዳይ በጣም ተጨንቀዋል፣ ይሁን እንጂ ከባለቤታቸው ጋር ገና አልተነጋገሩበትም።

ለ. መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ኹለት ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፦

1. የመልሱ ድግስ ቀርቷል እንዴ?
2. ምሳ በላሽ ወይ?

10.3.1 አንብቦ መረዳት

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 3)

ቅደመንባብ

የሚከተሉትን የቅደመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በትዕይንት "1" ና በትዕይንት "2" የመጀመሪያና የመካከለኛ ክፍል ከሚገኙት አላባውያን መካከል ለመለየት ያስቸገሯችሁ የትኞቹ ናቸው?

ለ. "የሠርጉ መዘገዝ ትዕይንት 3" ተውኔት የትኛውን የተውኔት ክፍል የሚያካትት ይመስላችኋል? በዚህ ክፍል የሚጠቃለሉት አላባውያን ምን ምን ይመስሏችኋል?

የሠርጉ መዘገዝ (ትዕይንት 3)

በሰፊው ሳሎን ውስጥ አቶ በላይሁን በጭንቀት ከሶፋው ላይ ሲነሱ ሲቀመጡ ሲቅበጠበጡ ይቆዩና ተመልሰው ሶፋው ላይ እረፍ ይላሉ። እንደገና ተነስተው ወንበር ላይ ይቀመጣሉ። ከዚያም ከግድግዳው ጥግ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁጢጥ ብለው ዓይናቸውን ከወዲያ ወዲህ ያንከራትታሉ። ስልክ ይደውላሉ። ስልኩ ሲጣራ እየገላመጡ ዝም ይላሉ። መሠረት ከውስጥ ብቅ ብላ ወደስልኩ ስታመራ ይተያያሉ።

አቶ በላይሁን፦ (በምልክት ጭምር) የ.ለ.ሁ.ም!

መሠረት፦ (ታነሳለች) ሃሎ...! አዎ...! የሉም...! ወጣ አሉ... እኔ'ነኝ!... እሺ በቃ... እነግራለሁ። (ትዘጋለች) ጋሼ!

አቶ በላይሁን፦ ተይው፤ ሰምቻለሁ ግቢ።

መሠረት፦ (ፈራ ተባ እያለች) ጋሼ! ...(ያቋርጧታል) ትገባለች። (ረጅም ዝምታ! በድጋሜ ስልክ ይጠራል። መሠረት አልመጣችም... ደመና ተንደርድሮ ገብቶ ያነሳል። አላያቸውም።)

ደመና፦ ሃሎ!... የሉም!... አዎ የሉም፤ ...አይ... አልነግርም፤ እረሳለሁ። አይ! አልተማርኩም፤... አልጽፍም! (ይዘጋል)

መሠረት፡- (ተንደርድራ እየገባች) ውይ... አሉ አልክ?

ደመና፡- መሠረት የሉም ’ኮ!... ቢኖሩስ ምን አሉ? አሉ ይባላል እንዴ አሁን? ያን መሳይ ኩሩ ሰው ቆሌያቸው ተገፎ...! ይቺን አክለው...! የገቡት ዕዳ ሳያልቅ? ልሙትልሽ! አሁን ደግሞ ከዳጃፍ ቆመው ወደገበያ የሚያልፈውን ኩበትና እንጨት የጫነ አርሶ አደር ሁሉ እያስቆሙ ይገባያዩና” ሂሳቡን ሌላውን ሸጣችሁ ስትመለሱ ትወስዳላችሁ፤ አንተ ደመና! ይህን ኩበት... ይህን እንጨት አራግፉና አህዮቹን እሰር” (በእሳቸው ድምፅ አስመስሎ ሲናገር መሠረት እየሳቀች፣ አቶ በላይሁን ዓይናቸውን አፍጥጠው ሲመለከቱት ከቆዩ በኋላ ድንገት እመር ብለው ይነሳሉ።)

አቶ በላይሁን፡- እ...ንዴ?

ደመና፡- (ደንግጧል) ውይ! ጋሽዬ አሉ’ንዴ?

አቶ በላይሁን፡- አለሁ! ባልኖርም አለሁ! ግን ምን አለች ነው ያልከው? ይከፈላል፣ አራግፍና እሰር...?

ደመና፡- ኧረ! አዎ ጌታዬ...! ሳራግፍ፣ ሳሥር ዋልኩ፣ ከእንግዲህ እጎረቤት ካላሰርኩ ስፍራም አይበቃም።

አቶ በላይሁን፡- ትሰማለህ ደመና? ከሰማኸኝ ... ከወደድከኝ...

ደመና፡- ምን ላርግ? ግራ ገባኝ...

አቶ በላይሁን፡- እኔ አልቻልኩም፤ ከፈለግክ አህዮቹን ፍታና ራሷን አያሉን እሠራት!...ላንድ አርሶአደር የምከፍለው ገንዘብ የለኝም።

ደመና፡- አ...ይ! እማይሆነውን ጋሼ!

አቶ በላይሁን፡- እሺ! ምናባቱ ልሁን ደመና? ም...ን...ልሁን?

ደመና፡- (ያዝናል) እንደኔ እንደኔ ጋሽዬ...! የወዳጅነቴን ካልተቀየሙኝ...፣ እንግዲያው አህዮችንም እትዬንም ሳይሆን ሙሽሮችን ነበር እንዳይመለሱ ማሰር፣ (ስልክ ይጠራል)

አቶ በላይሁን፡- የለሁም፤ ደመና አንሳው።

ደመና፡- (ያነሳል)ሃሎ...! አዎ...! የሉም...! ምን? (ደንግጧል) ማነህ አንተ? አሀ!... ቆይ እንጂ አንተ (ስልኩን እንደያዘ) ኧረ ፋከራ! እንዴ? (ያስቀምጣል ስልኩን) ኧረ ዛቻ!

አቶ በላይሁን፡- ማነው ደመና?

ደመና፡- የሙሽሮቹን መቀመጫ መድረክ መሥሪያ የሚሆን ያጋዘው።

አቶ በላይሁን፡- (ሳያስቡት በመጮህ) እ...ንዴ!... እያሉ...(ይጣራሉ) አንቺ አያሉ! ጥራት ደመና ፍጠን። (ደመና ሊወጣ ሲል ወ/ሮ አየለች በመግባታቸው ይመለሳል) በዪ እንጂ! ቆይ...ቆይ...የዚያን ቀን ቢያመኝስ? በዪ እንጂ? የሰሞኑ ጭንቀት ...ሐሳብ ጨንራ ስኳር...? ግጥም ብልስ?

ወ/ሮ አየለች፡- የምን መዓት ነው ሰውዬ...? ይህን ለምን ትላለህ?

አቶ በላይሁን፡- ለምን አልልም? በያ! ቆይ... ለምን...ለምን አሁን እያየሽኝ! (በቤቱ ዙሪያ አንዳች ነገር እየፈለጉ) እርር...ኩምትር አልልም... እንደምጣድ ቂጣ... እ...! ቆይ... ለምን ጢል...አልልም...!?

(ጠረጴዛው ላይ ይወጡና ክራባታቸውን ወደኮርኔሱ እየጎተቱ) ለምን እንደቋንጣ... ተንጠልጥዬ...

ወ/ሮ አየለች፡- አበድክ እንዴ?

ደመና፡- (ደንግጦ ተንደርድሮ) እንዴ ጋሽዬ! ኧረ አይሆንም! (በእግራቸው መሃል አንገቱን አሾልኮ... በኹለት እጆቹ እግራቸውን አንቆ ይይዛል) በቤሳይቷ የኔ ጌታ! (ምሕረት ይገባል፤ ያየዋል) ቶሎ በል አንተ ባልቦላ ኮረንቲ አጥፋ!... ጋሽዬ...!

ምሕረት፡- ምንድነው እሱ? (ይደነግጣል)

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴ!... ኧረ እባክህ አንተ ሰው? ምኑን አመጣብህ ...? እንዴ ምን መጣ?

አቶ በላይሁን፡- ከዚህ በላይ ምን ይምጣ? ውይ! ውይ! ውይ!... ይወርዳሉ።

(ደመና አንገቱን እያሻሸ ይቆማል)

ምሕረት፡- ያው በዛው በፈረደበት የድግስ ጣጣ ነው?

አቶ በላይሁን፡- (ቅስማቸው ስብር ብሎ ሶፋው ላይ በሐዘን ተውጠው ይመጣሉ። ረጅም ዝምታ) እሺ! መልሱ ይደገስ፤ ሰውም ይጠራ፤ ምናልባት ከሞት ብተርፍም፤ በዛ ቀን አልገኝም፤ ህዝቡንም ሙሽሮቹንም ይቅርታ ጠይቁልኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- የት ልትሄድ...አንተ?

አቶ በላይሁን፡- ሁሉም የተበደርካቸው፤ ዱቤ የወሰድከባቸው፤ ያሳስሩኛል። ምሕረት፤ የጥሪ ወረቀቱን በተንክ... ለመልሱ?

ምሕረት፡- አልበተንኩም?

አቶ በላይሁን፡- ም... ነው... አልክ?

ምሕረት፡- በአጉል ልማድና በይሉኝታ ታጥረን፣... እቤታችን ይህ ሁሉ ጉድ እያለ፣... ላይላዩን መልስ ጠርተን መጨፈራችን አልገባኝም። ለመጨረሻ ጊዜ ብናስብበት ብዬ አዘገየሁት። እማማ!... ውሳኔው የእናንተ ነው።

ወ/ሮ አየለች፡- አ...ይ...! ይደገስስ ቢባል ማን ቆይቶ ምሕረት? እኔም አባትህ ተበረታ ተስፋ እንዳላስቆርጠው ብዬ ትር ትር እላለሁ እንጂ ተሱ ብሻለሁኮ! ጨልሞብኛል።

ደመና፡- መቼስ አብረን ኖረናል... ባንዛመድ ያንጀት ወዳጅ ነኝ... ምን አገባህ ባትሉኝ ጋሽዬ! ሰው ያለውን ይበል... ቤታችን አይፍረስ፤ መልሱ ይቅር።

ወ/ሮ አየለች፡- እንዲያው የሰውስ ይቅር...! ላንድ ሰሞን ቡና መጠጫ አርጎ ይተወኛል...ልጄስ ምን ትል ይሆን?

ምሕረት፡- ደውዬ ነገርኳት።

አቶ በላይሁን፡- ምኑን ምሕረት?

ምሕረት፡- በሠርጉ ድግስ ጣጣ ቤት... ማጀታችን መራቆቱን! በዕዳ ቤት ንብረታችን ሊሸጥ እንደሚችል... በግልፅ ነገርኳት።

ወ/ሮ አየለች፡- ምነው?... ለምን?... መልሱ ቀረ አልካት...?

ምሕረት፡- ደውላ ልታስቀረው... አባባን ልታስገዝተው ወስና ነበር፤ አትጥራ ያለችኝ እሷ ነች።

አቶ በላይሁን፡- እንዴት? ይቅር ብላ ነው?

ምሕረት፡- አዎ አባባ! "ለኔ ሠርግ ያደረገው ዓለሜ ሳይሆን ሞቱ ነው። የጠፋው ጠፋ፤ ግን መልሱን ደግሶ ከጠራኝ...ቤተሰቡንም እኔንም እንደገደለኝ ይቁጠረው" ብላለች።

አቶ በላይሁን፡- አውቅ ነበር...ነበር፤ እንኳን መልሡ ሠርጉ ቢቀር አይከፋኝም ነበር።

ወ/ሮ አየለች፡- እኔ የሷ መቼ አሳስበኝ፤ የወጉ የልማዱ እንዳይቀር..." ከሰው እንዳላንስ ነበር እንጂ..." አለሜ ሳይሆን ሞቱ ነው" አለች? እውነቷን ነው፤ ቢቀርስ...(ይተክዛሉ)

አቶ በላይሁን፡- ጎሽ! (ይተነፍሳሉ) ማነህ ደመና... ያችን የምጠጣትን አምጣትማ! (አረቂውን አምጥቶ ይቀዳላቸዋል)

ወ/ሮ አየለች፡- ወይ ጣጣ! የስንቱ ቤት ሲታመስ ኖሯል?

ምሕረት፡- (ኹለቱንም ተራበተራ እያየ) መልስ አለመደገሳችን አቅማችንን ማወቃችን እንጂ የሚያሳማን አይሆንም። እንዲያውም በተንዛዛ ድግስ ሃብት ንብረቱን ለሚያባክነው ማህበረሰብ ምሳሌ እንሆናለን።

መጋረጃ ይዘጋል።

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ 8ኛ ክፍል 2007 ዓ.ም. ከገጽ 239 - 243 የተወሰደ)

ድኅረንባብ

"በሠርጉ መዘዝ ትዕይንት "3" ተውኔት መሠረት ከሀ-ረ ያሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ፣ የቀሩትን በጽሐፍ መልሱ።

ሀ. ከአቶ በላይሁን ከሶፋ ወደወንበር መውረድ፣ ከወንበር ወርዶ መሬት ላይ ቁጢጥ ማለት ምን ትረዳላችሁ?

ለ. አቶ በላይሁን፡- (በምልክት ጭምር) "የ.ለ.ሁ.ም!" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ከዚህ ምን ትረዳላችሁ?

ሐ. "... አህዮቹንም እትዬንም ሳይሆን ሙሽሮቹን ነበር እንዳይመለሱ ማሰር" የሚለውን የደመና ንግግር መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ።

መ. "በአጉል ልማድና በይሉኝታ ታጥረን..." የሚለውን የምህረት ንግግር ሰፋ አድርጋችሁ አብራሩ።

ሠ. ቤተሰቦች ዕዳ ውስጥ የሚዘፈቁት ልጆቻቸው "ሠርጋችሁ ዳሩን" በማለት ስለሚያስገድዷቸው ነው" በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ? በተውኔቱ መልዕክት /ዐውድ/ መሠረት መልሱ።

ረ. "ሃሎ...የሉም...አዎ የሉም...አይ! አልነግርም እረሳለሁ። አያይ! አልተማርኩም... አልጽፍም...የሚለውን የደመና ንግግር አብራሩ። ... መልዕክት መናገር አይችልም፤ ይረሳል መጻፍም አይችልም፤ ማለት ነው?

ሰ. የተውኔቱን መልዕክት በአጭሩ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

ሸ. በተውኔቱ የመጨረሻ ክፍል የተካተቱትን አላባውያን በቢጋር ሠንጠረዥ አስፍሩ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሠርጉ መዘገዘ” ትዕይንት 3፤ ተውኔት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

	ደረጃ 1	ደረጃ 2	ደረጃ 3	ደረጃ 4
ስርዓተነጥብ ጠብቆ ማንበብ				
የገፀባሕርያት ንግግር ማስመሰል				
ሳይቆሙ/ሳይደግሙ ማንበብ				

10.3.2 ቃላት

1. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ይህን ኩበት... ይህን እንጨት አራግፍና አህዮቹን እሰር።

   ለ. ሁሉም የተበደርኳቸው፣ ዱቤ የወሰድኩባቸው ያሳስሩኛል።

   ሐ. አቶ በላይሁን ከግድግዳው ጥግ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁጢጥ ብለው ተቀምጠዋል።

   መ. እንደኔ እንደኔ ጋሽዬ... የወዳጅነቴን ካልተቀየሙኝ ልናገር።

   ሠ. ...ማጀታችን መራቆቱን! በዕዳ ቤት ንብረታችን ሊሸጥ እንደሚችል በግልጽ ነገርኳት።

2. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ በሰጣችኋቸው ፍቺዎች ዓረፍተነገር መስርቱ።

   ሀ. እመር

   ለ. ልታስገዝተው

   ሐ. ያንጀት

   መ. ሲታመስ

   ሠ. ፈራ ተባ

   ረ. ያጋዘው

   ሰ. ተንጠልጥሎ

   ሸ. የማያሳማን

መጻፍ

ሀ. የጀመራችሁትን ተውኔት የመጨረሻ ክፍል በመጻፍ አጠናቁ።

ለ. በጻፋችሁት ተውኔት የመጨረሻ ክፍል የሚካተቱ አላባውያንን በቢጋር ሠንጠረዥ አስፍሩ።

ሐ. ከዚህ በፊት በተውኔቱ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ያስፈራችኋቸውን አላባውያን በአንድ የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር አጠቃላችሁ አስፍሩ።

10.3.3 መናገር

“የሠርጉ መዘዝ” በሚል ርዕስ በሦስት ትዕይንቶች ተከፋፍሎ የቀረበውን ተውኔት መሠረት አድርጋችሁ ሀሳባችሁን በሚከተለው የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር አደራጅታችሁ ንግግር አድርጉ።



ሰዋስው

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ፣ ጥገኛ ሐረጎችን፣ ነጠላ ዓረፍተነገሮችንና እንደመሙያ ያገለገሉ ሰማዊ ሐረጎችን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. የሂሳብ ማሽኑን ሲነካኩ ጭንቀታቸው ይጨምራል።

ለ. እቃውን መልሱ ወይም ሌላ ውል ፈጽሙ።

ሐ. ወይዘሮ አየለች ጠንካራ ሴት ናቸው።

መ. አቶ በላይሁን ኩሩ ሰው ነበሩ?

ሠ. ወይዘሮ አየለች ሲመጡ መሠረት ወደውስጥ ገባች።

ረ. ሴትዮዋ ጭንቅላቴ ላይ ብትወጣም ወንበሮቹ እስከ ምላሹ ይቆያሉ።

ሰ. አንዳንድ ሰዎች በመልሱ ጊዜ ስጦታ ያመጣሉና አስተናጋጆች በደንብ ይቀበሏቸው።

ሸ. መልሱ በቪዲዩ ሊቀረጽ ነበር።

ቀ. መሠረትና ደመና ታማኝ ሠራተኞች ናቸው?

በ. ሰው እንደልማዱ ይማ እንጂ የመልሱ ድግስ ይቅር።

ዋቢዎች

ማረው አለሙ። (2005።) *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ረሺድ ጀማል። (2001።) *"ባለዳስ ዕዳዎች።"* በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባ/አስ/ተቁ/ጥ/ል/አጠቃቀም የሥራ ሂደት። *መቅረዝ።* አዲስ አበባ፤ (ልዩ እትም) ቁጥር 7፣ ከገጽ 341-377

ባየ ይማም። (2002።) *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጎሩይ ወልደሥላሴ (ብላቴን ጌታ)። (2000።) *ወዳጀ ልቤና ሌሎችም።* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕረስ።

ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና አብክመ ትምህርት ቢሮ። (2007 ዓ.ም)። *አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ፤* ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት

ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴርና አብክመ ትምህርት ቢሮ። (2007)። *አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ 8ኛ ክፍል የመምህር መምሪያ መጽሐፍ።*

ከበደ እንግዳሰው(የለም)። *ነገር በምሳሌ።* አጫጭር ታሪኮች።

ዘሪሁን አስፋው። (1992።) *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ። (1996)። *አማርኛ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ። (2007 ዓ.ም)። *መስህብ፤ መጽሔት፤ቅ/ቁ/6 2007ዓ.ም*

ዳንኤል ክብረት። (2005።) *የኔ ጀግናና ሌሎች።* አዲስ አበባ፤ አጊዮስ ጎተመትና ጠቅላላ ንግድ ኃ.የተ.የግል ማህበር።

ዳኛቸው ወርቁ። (1988።) *የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ።

ጌታሁን አማረ። (1989።) *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጎህ መጽሔት። (1968 ዓ.ም)። *ቱሉ ፎራሳ፣ ደራሲው አይታወቅም*

የአማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት (2011 ዓ.ም)። *የአማራ ክልል የአየር ንብረት።*

Damtew Tessema. (2017).The effect of small scale irrigation on household food security in Bonga woreda, Sidama, Zon, South Ethiopia, Thesis \

Islamiccasion.2005htt//www.islamiccasions.com. 100 moral stories. March, 20,2005

Th New Times/Ruanda/ (2012). The Selfish man. April25,2012. Ruanda Loading daily.